# በትራንስፖርት ሚኒስቴር
# የትራንስፖርት ባለሥልጣን

6

## የተሻሻለ
## የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት
## ብቃት ማረጋገጫና ሥምሪት የሥራ ሂደት
## የሥምሪት አፈፃፀም መመሪያ

676/2013

መጋቢት 2005 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## መግቢያ

ትራንስፖርት ለአንድ አገር ኢኮኖሚ የደም ሥር የሆነ ድንበር-የለሽና የማያቋርጥ እንቅስቃሴ ያለው የአገልግሎት ዓይነት ነው፡፡ በመሆኑም እስካሁን በአገራችን ያለው የትራንስፖርት አገልግሎት ዕድገት የተጠበቀውን ያህል ባለመሆኑ መንግሥት ይህንኑ ሁኔታ በመገንዘብ መሠረታዊ የአሠራር ለውጥ በማድረግ ተጠቃሚው ሕብረተሰብ በአገልግሎት ዕርካታ እንዲያገኝና አገልግሎት ሰጪውም ለሚሰጠው አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት ላይ ይገኛል፡፡

በአገራችን እየተሰጠ ያለው የንግድ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ዘላቂነት ያለውና የኅብረተሰቡን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ፣ ኢንቨስትመንትንና ጤናማ ውድድርን የሚያበረታታ፣ የሕዝቡን የመክፈል አቅም ያገናዘበና አቅርቦትን የሚያሳድግ ወጥ የሆነ አሠራርና አተገባበርን የሚከተል ሆኖ መከናወን ይኖርበታል፡፡

ስለሆነም በፌደራልና በክልሎች የተደረጉ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሥምሪትና አደረጃጀት ወቅታዊ፣ ወጥና አገራዊ ይዘት እንዲኖራቸው ሆኖ እንዲተገበሩ ማድረግ በማስፈለጉ የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት ቀልጣፋ፣ ወጪ ቆጣቢ፣ ፍትሃዊና የተጠቃሚውን የመክፈል አቅም ያገናዘበ እንዲሆን ታስቦ ሥምሪቱ በሥራ መርሀ-ግብር በተደገፈ አደረጃጀቱም ተጠያቂነትን ባረጋገጠና በውድድር ላይ የተመሠረተ አሠራር በመላው አገሪቱ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ሆኗል፡፡

በመሆኑም የህዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጡን በአግባቡ ለመምራትና ለመከታተል የትራንስፖርት ባለሥልጣን በአዋጅ 468/97 ክፍል ሁለት አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1.ረ በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት ይህን የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት አደረጃጀት ብቃት ማረጋገጫና ሥምሪት የአፈፃፀም መመሪያ አውጥቷል፡፡

676/2013

## ***ክፍል አንድ***

## **ጠቅላላ**

### 1.1 ርዕስ

ይህ መመሪያ "የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት አደረጃጀት ብቃት ማረጋገጫና ምምሪት የሥራ ሂደት የአፈጻጸም መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 1.2 ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ

**ሀ. *"ባለሥልጣን"* ማለት**

በአዋጅ ቁጥር 468/97 የተቋቋመው የፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ነው፡፡

**ለ. *"የክልል ትራንስፖርት ባለሥልጣን/ቢሮዎች"* ማለት**

በአዋጅ ቁጥር 41/84 እንዲሁም በየክልሉ በወጡ የማቋቋሚያ አዋጆች መሠረት የተቋቋሙ የክልል ትራንስፖርት ባለሥልጣን (ቢሮዎች) ናቸው፡፡

**ሐ. *"ቅ/ጽ/ቤቶች"* ማለት**

የፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ወይም የክልል ትራንስፖርት ባለሥልጣን (ቢሮዎች) ያቋቋማቸው የዞን ትራንስፖርት ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ ባለሥልጣኑ (በቢሮዎች) የሚቋቋሙ የትራንስፖርት ቅ/ጽ/ቤቶች ማለት ነው፡፡

***መ. "ኦፕሬተር" ማለት***

የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ለመስጠት ተመዝግቦ የሙያ ብቃት የተሰጠው የተሽከርካሪ ባለንብረት፣ ወይ ድርጅት ሲሆን ሾፌር፣ ገንዘብ ተቀባይና ረሠራተኞችን ያካትታል፡፡

**ሠ. *"የሙያ ወይም ብቃት ማረጋገጫ"* ማለት**

በአዋጁ መሠረት በፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ወይም በክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት የሕዝብ የንግድ የመንገድ
ማመላለሻ መስጠት ለሚፈልጉና በሥራ ላይ ለሚሰማሩ

ሰተሽከርካሪ ባለንብረቶች፣ ማኅበራት፣ ድርጅቶች፣ ሾፌሮች፣ ገንዘብ ተቀባዮችና ረዳቶች የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ነው፡፡

ረ. ***"ሥምሪት" ማለት*** የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ለመስጠት በመደበኛ 1፣2 እና 3 እንዲሁም በልዩ ትራንስፖርት አገልግሎት በተመዘገቡ ተሽከርካሪዎች አማካኝነት የሚደረግ ጉዞ (እንቅስቃሴ) ነው፡፡

ሰ. ***"ነፃ ሥምሪት" ማለት*** ኦፕሬተሮች በወሰዱት ፈቃድ መሠረት በሥራ መርሐ ግብር በታገዘ ነፃ በሆነና በጤናማ ውድድር የሚሠሩበት አካሄድ ነው፡፡

ሸ. ***"ፍራንቻይዚንግ" ማለት*** የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ለመስጠት በተወሰነ የኮንትራንት ጊዜ፣ የአገልግሎት ክፍያ፣ የሥምሪት ብዛትና የአገልግሎት ጥራት መሠረት በተለዩና በተገደቡ የጉዞ መሥመሮች ላይ በፌሬዳል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ወይም እንዳግባቡ በክልል ትራንስፖርት ባለሥልጣን (ቢሮዎች) እና በኦፕሬተሮች መካከል የሚፈጸም የአገልግሎት ውል ወይም ውክልና ማለት ነው፡፡

ቀ. ***"ልዩ" ማለት*** በመደበኛ ሥምሪት መሥመርችም ሆነ በሴሎች በተጓዡና በአገልግሎት ሰጪው ኦፕሬተር መካከል በሚደረግ ስምምነት የሚሰጥ የትራንስፖርት አገልግሎት ነው፡፡

በ. ***"ውድድር" ማለት*** በደረጃዎች መካከልና ከአንድ ደረጃ በላይ የሆኑ ኦፕሬተሮች በሚሰጡት የአገልግሎት ዓይነት በዋጋ፣ በምቾትና የደኅንነት መሣሪያዎችን መሠረት በማድረግ ተገልጋዩ የራሱን ምርጫ በመወሰን የሚገለገልበት የሥምሪተ አፈፃፀምና የተሽከርካሪ አቅርቦት ሥርዓት ነው፡፡

ተ. ***"ደረጃ" ማለት*** በዚህ መመሪያ በተዘጋጀው መሥፈርት መሠረት በንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ለሚሠማሩ ተሽከርካሪዎች በመመ ሪያው በተካተቱ መሥፈርቶች መሠረት የሚሰጥ ደረጃ ነው፡፡

ቸ. ***"የሥራ መርሀ -ግብር" ማለት*** ኦፕሬተሮች በሚንቀሳቀሱበት መሥመር፣ የሚያስከፍሉት ክፍያ ታሪፍ የሚመደቡት የተሽከርካሪ ብዛት፣ ዓይነት፣ መነሻና መድረሻ ሰዓትና የሥምሪት መሥመርችን የያዘ የወር፣ የ15 ቀን፣ የ3 ወር ወይም የ6 ወር እንደ አስፈላጊነቱ የዓመትና ከዚያ በላይ በጊዜ የተገደበ የሥራ እንቅስቃሴ ዕቅድ ነው፡፡

***ኀ."ሚኒባስ" ማለት*** መንገደኞችን ለማመላለስ የሚያገለግል የመቀመጫ ልኩ አሽከርካሪውን ጨምሮ ከ11-17 ሰው ያልበለጠ መያዝ የሚችል ተሽከርካሪ ነው፡፡

***ነ."ማኅበር" ማለት*** *የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የወሰዱ ባለንብረቶች ወይም ኦፕሬተሮች የሚያቋቁሙት ማኅበር ነው፡፡*

***ኘ.የማኅበር ፈቃድ" ማለት*** *በማኅበር ተደራጅተው የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ለመስጠት ጥያቄ የሚያቀርቡና የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ለወሰዱ ባለሀብቶች የሚሰጥ የማኅበር ምዝገባ ፈቃድ ነው፡፡*

## 1.3 ዓላማ

የአፈጻጸም መመሪያው ዓላማዎች፡-

በዘርፉ ጤናማና ውጤት ማምጣት የሚያስችል ግልጽ የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመሳሰሻ አገልግሎት ምቾቱና ደኅንነቱ የተጠበቀ፣ ቀልጣፋና አስተማማኝ የሆነ ቀጣይነት ያለው የተገልጋዩን ኅብረተሰብ የመክፈል አቅምና ፍላጎት ያገናዘበ በፌዴራልና በሁሉም ክልሎች ሊተገበር የሚችል እንዲሆን ለማድረግ፣

በዘርፉ ለተሠማሩ የተሽከርካሪ ባለንብረቶችና ድርጅቶች ድጋፍና ዕገዛ በመስጠት ለማበረታታትና አዳዲስ ባለሀብቶች ወደ ዘርፉ የሚገቡበትን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የሕዝብ ትራንስፖርት ዘርፍ ለኢንቨስትመንት ሳቢና ማራኪ ለማድረግ፣

በአገር አቀፍ ደረጃ ያለውን ውሱን የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት በማሳደግ በውድድር ላይ የተመሠረተ የተገልጋዩን ኅብረተሰብ የመክፈል አቅምና ፍላጎት መሠረት ያደረገ አገልግሎት እንዲኖር ለማስቻል፤

## 1.4 የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ የአፈጻጸም መመሪያ በፌዴራል እና በክልሎች አገር አቋራጭ አነስተኛ መለስተኛ በሆኑ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በሚሰጡ ተሽከርካሪዎች፣ ማኅበራትና ኦፕሬተሮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ አገልግሎት ሙያ ብቃት ማረጋገጫና አደረጃጀት

### 2.1. የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ስለመውሰድ

2.1.1. በንግድ የመንገድ የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት መሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ግለሰብ፣ አክስዮን ማኀበር፣ /ኃላ/የተ/የግል ማህበር/ ፒኤልሲ ወይም ድርጅት

ሀ. በአዋጅ 468/97 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2-ለ መሠረት ከፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን፣ የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይወስዳል፣

ለ. በክልሎች ውስጥ የሚሠራ ከሆነም በክልል ትራንስፖርት ባለሥልጣን፣ ወይም ትራንስፖርት ቢሮዎች ወይም ውክልና ከተሰጠው የዞን ቅ/ጽ/ቤቶች በአዋጅ በተሰጣቸው የሥልጣን ገደብ ክልል ውስጥ የሚሰጠውን የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መውሰድ ይኖርበታል።

2.1.2. በዘርፉ የተሰማሩ ወይም የሚሠማሩ ሠራተኞች አስፈላጊውን ሥልጠና ከወሰዱ በኋላ የሙያ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ምሥክር ወረቀት ሊኖራቸው ይገባል፣

2.1.3. በሕዝብ ማመላለሻ በአሽከርካሪነት የሚቀጠሩ ሠራተኞች በአዋጅ ቁጥር 468/97 7.2-ለ መሠረት ተገቢው የብቃት ማረጋገጫ ሥልጠና መውሰድ ይኖርባቸዋል፤

## 2.2. አደረጃጀት

### 2.2.1. በማኅበር ስለማደራጀት

ሀ. በአዋጅ 468/97 ክፍል 3 አንቀጽ 13/1 መሠረት በማኅበር በመደራጀት የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት መስጠት የሚፈልጉ ኦፕሬተሮች በደረጃ አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት ወይም በልዩ የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ውስጥ አንዱን ብቻ መርጠው መደራጀት ይችላሉ። አገልግሎት የሚሰጡትም በተደራጁበት ደረጃና በዚያው ውስጥ ብቻ ይሆናል።

ሆኖም አንድ ተሽከርካሪ በሕሰው ደረጃ ለመሥራት ማኅበር ያልተደራጀ ያልተመሠረተ ከሆነ ተሽከርካሪው ያለ ሥራ መቆም ስለሌለበት የተሽከርካሪው ባለንብረት ከተደራጁ ማኅበራተ ውስጥ አንዱን መርጠው የሥምሪት አገልገሎት በጊዜያዊነት እንዲያገኙ ይደረጋል።

ለ. በአንቀጽ 2.2. በፊደል ሀ በተጠቀሰው መሠረት በማኅበር የሚታቀፉ የአባል ተሽከርካሪዎች ብዛት፡

ቀደም ሲል ለሁሉም ትራንስፖርት ማሕበራትና ድርጅቶች ተቀምጦ የነበረው የአደረጃጀት መስፈርት በአገር አቋራጭ፣ መለስተኛና አነስተኛ ሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ተለይቶ ከዚህ ቀጥሎ በተዘረዘረው መሰረት እንዲተገበር ተደርጓል።

## ሀ. ስመለስተኛና አነስተኛ ትራንስፖርት ማሕበራት፣

| ተ.ቁ | የማሕበር ምዝገባ ፈቃድ መስፈርት |
|---|---|

| ተ.ቁ | የማሕበር ምዝገባ ፈቃድ መስፈርት |
|---|---|
| 1 | ደረጃ 1 ዝቅተኛ 15 ጣሪያው 100 |
| 2 | ደረጃ 2 ዝቅተኛው 30 ጣሪያው 180 |
| 3 | ደረጃ 3 ዝቅተኛው 40 ጣሪያው 250 |

## ሰ. ለአገር አቋራጭ ሕዝብ ማመላለሻ ማሕበራትና ድርጅቶች፣

| ተ.ቁ | በፊት የነበረው | አሁን የተሻሻለው | የተሻሻለበት ምክንያት |
|---|---|---|---|
| 1 | ልዩ ዝቅተኛ 15 ጣሪያው 50 | ✓ ዝቅተኛው 10 ጣሪያው 50 | ✓ ከፍተኛ ካፒታል ኢንቨስትመንት የሚጠይቅ በመሆኑ፣<br>✓ ሥራውንም ለመምራትና ለማደራጀት ተመሳሳይ አቅም ስለሚሻ፣ አበረታች ሁኔታ ለመፍጠር ነው፡፡ |
| 2 | ደረጃ 1 ዝቅተኛ 15 ጣሪያው 100 | ዝቅተኛው 50 ጣሪያው 200 | ✓ አደረጃጀቱ እንዲጠናከርና የተሻለ አቅም እንዲፈጠር ለማድረግ፣<br>✓ በቀጣይም ለተሻለ ዕድገት በብቃት የስራ አቅም እንዲፈጠርና፣<br>✓ በሙያተኛ አቅም ጠንካራ ሥራ እንዲኖር ለማድረግ ነው፡፡ |
| 3 | ደረጃ 2 ዝቅተኛው 30 ጣሪያው 180 | ዝቅተኛው 50 ጣሪያው 200 | ✓ አደረጃጀቱ እንዲጠናከርና የተሻለ አቅም እንዲፈጠር ለማድረግ፣<br>✓ በቀጣይም ለተሻለ ዕድገት በብቃት የስራ አቅም እንዲፈጠር፣<br>✓ በተበታተነ ሁኔታ የሚስተዋሉ አደረጃጀቶች በዘርፉ ዕድገት ላይ የሚሳድሩትን ጫና ለመቀነስ፣<br>✓ በሙያተኛ አቅም ጠንካራ ሥራ እንዲኖር ለማድረግ ነው፡፡ |
| 4 | ደረጃ 3 ዝቅተኛው 40 ጣሪያው 250 | ✓ ዝቅተኛው 50 ጣሪያው 250 | ✓ አደረጃጀቱ እንዲጠናከርና የተሻለ አቅም እንዲፈጠር ለማድረግ፣<br>✓ በቀጣይም ለተሻለ ዕድገት በብቃት የስራ አቅም እንዲፈጠር፣<br>✓ በተበታተነ ሁኔታ የሚስተዋሉ አደረጃጀቶች በዘርፉ ዕድገት ላይ የሚሳድሩትን ጫና ለመቀነስ፣<br>✓ በሙያተኛ አቅም ጠንካራ ሥራ እንዲኖር ለማድረግ ነው፡፡ |

ሐ. በማኅበር ተደራጅተው የሕዝብ ትራንስፖርት ማመሳሰሻ አገልግሎት የሚሰጡ ኦኘሬተሮች በአዋጅ 468/97 አንቀጽ 15 መሠረት በህግ የተሰጣቸውን መብት ተፈጻሚ ለማድረግ የመመሥረቻ ጽሑፋቸውንና መተዳደሪያ ደንባቸውን በማቅረብና እያንዳንዱ ኦኘሬተር የተስማማ መሆኑን ለማረጋገጥ በፌዴራል ወይም በክልል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ወይም ቢሮዎች በግንባር በመገኘት በመፈረም የምዝገባ ፈቃዳቸውን ይወስዳሉ።

መ. የምዝገባ ፈቃድ በየዓመቱ መታደስ አለበት።

2.2.2. <u>በግል ወይም በድርጅት አገልግሎት ስለመስጠት፣</u>

ሀ. በአዋጅ 468/97 ክፍል 3 አንቀጽ 12/2 መሠረት በግለሰብ ወይም በድርጅት በአክስዮን ማኅበርና /ኃላ/የተ/የግል ማህበር/ በፒኤልሲ የሕዝብ ማመሳሰሻ አገልግሎት መስጠት የሚፈልጉ ኦኘሬተሮች በልዩ ወይም በመደበኛ ደረጃ 1፣2፣3 ወይም በሁሉም የደረጃዎች አይነት ተሽከርካሪዎችን በማቅረብ የህዝብ የንግድ የመንገድ ማመሳሰሻ ሥራ ማካሄድና አገልግሎት መስጠት ይችላሉ።

ለ. በግል ወይም በድርጅት የህዝብ ማመሳሰሻ አገልግሎት ለመስጠት የሚመዘገቡ ኦኘሬተሮች የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር (ሊብሬ) በመያዝ በግንባር በመቅረብ የሙያ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የኦኘሬተርነት ፈቃድ መውሰድ ይኖርባቸዋል።

ሐ. የብቃት ማረጋገጫ ፍቃዱ በየዓመቱ መታደስ አለበት።

መ. በግል፣ በድርጅትና /ኩባንያ/ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚቀርቡ አውቶብሶች ብዛት ገደብ የለውም። ሆኖም አሠራሩ ወደ ምናፓሊ እንዳያመራ ተገቢው ክትትል ይደረግበታል።



# ***<u>ክፍል ሦስት</u>***

## 3. <u>የኦኘሬተርነት ፈቃድ ዓይነቶች የደረጃ መመዘኛ መሥፈርቶች</u>

በሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሠማሩ ሰዎችና ድርጅቶች ለአገልግሎት እንደሚያቀርቧቸው ተሽከርካሪዎች ሁኔታ እና እንደሚመርጡት የትራንስፖርት አገልግሎት ዓይነት የተለያዩ የኦኘሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህም መሠረት በዚህ መመሪያ በተዘጋጀው መሥፈርት የተለዩ ደረጃዎችን መሠረት አድርጐ አራት ዓይነት የኦኘሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፡፡ እነሱም፡

1. የልዩ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ኦኘሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ
2. የመደበኛ ደረጃ አንድ የመንገድ ትራንስፖርት ኦኘሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ
3. የመደበኛ ደረጃ 2 " " " " " ፈቃድ
4. የመደበኛ ደረጃ 3 " " " " " ፈቃድ ናቸው፡፡

### 3.1. <u>የልዩ የሕዝብ የመንገድ ትራንስፖርት ኦኘሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ የደረጃ መመዘኛ መሥፈርቶች</u>

3.1.1. ልዩ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የብቃት ማረጋገጫ የሚጠይቁ ኦኘሬተሮች ለሚሰጡት አገልግሎት የሚያስከፍሉት ክፍያ ታሪፍ፣ ተመን፣ የመነሻ መድረሻ ቦታዎች ዝርዝር የተሽከርካሪዎች የጥራት ደረጃ ሁኔታ ከመደበኛ ደረጃ 1፣ 2፣ 3 ትራንስፖርት አገልግሎት የሚለይ ሲሆን፣ ኦኘሬተሮች በታወቁ የሥምሪት መሥመሮች እና በነብረተሰቡ የተለመዱ ቦታዎች መንገደኞችን ለማጓጓዝ ወይም ሌሎች ሁኔታዎች በተጓዡና በአጓጓዡ መካከል በሚፈፀም ስምምነት ተሣፋሪዎች የሚፈለጉበት ቦታ በመረጡት መንገድ ላይ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥበት አሠራር ነው፡፡

የልዩ ትራንስፖርት ኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት ኦፕሬተሩ በቅድሚያ እንዲያሟላቸው ከሚጠየቁ ቅድመ ሁኔታዎችና ለደረጃ በመሥፈርትነት የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆኖ የልዩ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ደረጃ የሚሰጠው ተሽከርካሪ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መሥፈርቶች ሙሉ በሙሉ ማሟላት ይኖርበታል፤

ሀ. የአገልግሎት ዘመን ከተመረተበት ጊዜ ጀምሮ ከ7 ዓመት ያልበለጠ፤

ለ. የአንድ ተሣፋሪ መቀመጫ የወንበር ስፋት ቢያንስ 450×450 ሚ.ሚ.፤

ሐ. ከፊትና ከኋላ ባሉት ወንበሮች መካከል ያለው ስፋት/ከፍተት ቢያንስ 880 ሚ.ሚ፤

መ. ከግራና ቀኝ ባሉት ወንበሮች መካከል የሰው መተላለፊያ ኮሪደር/ከፍተት ቢያንስ 550 ሚ.ሚ መሆን አለበት፤

ሠ. ወንበሮች ታጣፊ የእጅ መደገፊያ ያላቸውና እንዲሁም የሚዘረጋና የሚታጠፍ የምግብ ጠረጴዛ ያለው፤

ረ. ሁሉም መቀመጫዎች ምቾት ያላቸውና ቀዳ ወይም ዘመናዊ ጨርቅ የለበሱ ከጐኑ ያለውን መቀመጫ ሳይነካ ወደፊትና ወደኋላ በተፈለገው መጠን መንቀሳቀስ የሚችል (Reclining seat) መሆን ይኖርበታል፤

ሰ. የአየር መቆጣጠሪያ AC ያለው፤

ሸ. የመልዕክት ማስተላለፊያ መሣሪያ የተገጠመለት፤ እንዲሁም የተሟላ የመጀመሪያ ዕርዳታ ሕክምና መስጫ ያለው፤

ቀ. በአደጋ ጊዜ መውጫ ምቹ የሆነ፤ የጐን መስኮት ያለው፤ እንዲሁም መስታወቶቹ አደጋ የማያስከትሉ (Safety glasses) መሆን አለባቸው፤

በ. የአውቶቡስ ወለል የማያንሸራትትና ምንጣፍ የተደረገለት፤ ጥራት ያለው የፀሐይ ብርሃን የሚከላከል መጋረጃ ያለው፤

ተ. ቴሌቪዥን (TV) DVD ሲስተም ያለው፤

ቸ. አገልግሎት በሚሰጥባቸው ከተሞች የትኬት ቢሮዎች ያመቻችና የቅድመ-ጉዞ ትኬት አገልግሎት የሚሰጥ፤

ኀ. ከተሽከርካሪው የውስጥ ገድገዳ ጋር የተያያዘ በወንበሮች መካከል የተተከለ እንዲሁም ከፊት ለፊት ባሉት መቀመጫዎች ላይ በእጅ የሚጨበጡ መያዣዎች (Handling)፣ እንዲሁም ለሁሉም ተሣፋሪዎች የደኅንነት ቀበቶ ያለው፤

ከ. ቀላል ምግቦችንና ለስላሳ መጠጦች ማቀዝቀዣ ያለው፣

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Transport
Authority No. 1

## 3.2. በደረጃ 1፣ 2፣ 3 የሚሰጥ የትራንስፖርት አገልግሎት

3.2.1. በመደበኛ ደረጃ 1፣ 2 እና 3 የብቃት ማረጋገጫ ደረጃ ተሰጥቷቸው አገልግሎት የሚሰጡ ኦፕሬተሮች በቀረቡት መርሐ ግብር መሠረት በሚሠማሩበት የሥምሪት መሥመር በተመጣጣኝ ታሪፍና የአገልግሎት ጥራት ለኀብረተሰቡ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣሉ:: በተጨማሪም በሚሠሩበት የሥምሪት መሥመር ባሉ ከተሞች ተሣፋሪዎችን የመጫንና የማንንዝ በተፈቀደው ቦታ የማውረድ አገልግሎት ይሰጣሉ::

በደረጃ 1፣ 2፣ 3 የሚሰጥ የተሣፋሪ ማንንዝ አገልግሎት ክፍያ ታሪፍ በመንግሥት የተወሰነ ይሆናል::

ሀ. በደረጃ 1 የሚመደቡ ተሽከርካሪዎች በመሥፈርቱ መሠረት ተመዝነው ከ80-100 ነጥብ ያስመዘገቡ::

ለ. የደረጃ ሁለት ምድብ የሚሰጣቸው ተሽከርካሪዎች ከ65-79.99 ነጥብ::

ሐ. በደረጃ ሦስት የሚመደቡ ከ50-64.99 ነጥብ ያገኙ ናቸው፣

መ. በመስፈርቱ መሠረት ከደረጃ በታች የሆኑ አውተብሶች ጉድለቱ ተስተካክሎሲመጡ እንዲያሟሉ የተነገሬቸውን ስለማሟላታቸው እየተረጋገጠ ደረጃ 3 እንዲሰጣቸውና የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል::

## 3.3. የመመዘኛ መሥፈርት

3.3.1. በልዩ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት የሚቻለው በክፍል 3 ተራ ቁጥር 3.1.1 ከፊደል ሀ-ከ የተዘረዘሩት መሥፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው::

3.3.2. በደረጃ 1,2,3 የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የብቃት ማረጋገጫ የሚጠይቁ ኦፕሬተሮች ተሽከርካሪዎቻቸውን በማቅረብ ቀጥሎ በተዘረዘረው መሥፈርት መሠረት ደረጃ ይሰጣቸዋል::

3.3.3. <u>የደረጃ 1፣ 2 እና 3 ኦፕሬተርነት ደረጃ መስፈርት ማብራሪያዎች</u>

የደረጃ 1፣ 2 እና 3 የትራንስፖርት ኦኘሬተርነት ማረጋገጫ ለማግኘት ኦኘሬተሩ ከሚጠየቁት ዋና ዋና መመዘኛዎች መካከል የተሽከርካሪ የአገልግሎት ዘመን፣ የሕዝብ ማመሳለሻ ተሽከርካሪዎች ያላቸው ምቾት፣ የቴክኒክ ብቃትና ደኅንነት እንደተሽከርካሪዎቹ ሞዴልና ዓይነት የሚለያይ ነው፡፡

አሁን በሥራ ላይ ያሉትና ወደፊት የሚገቡት የሕዝብ ማመሳለሻ የተሽከርካሪዎች ደረጃና ሥምሪት ለመወሰን በሀገራችን ውስጥ ያሉትን ኦኘሬተሮች ለሕዝብ ማመሳለሻ የሚያቀርቧቸው ተሽከርካሪዎች ጥራት ደረጃ በመመዘኛው መሠረት ግምገማ የሚደረግ ሲሆን፣ ለመመዘኛዎቹ እንደ ክብደታቸውም ነጥብ ተሰጥቷል፡፡

በተጨማሪም አዲስ ሞተርና ካምቢዮ ገዝቶ ያስገጠመ ለዚህም አዲስ መሆኑንና ምንም አገልግሎት ያልሰጠ ስለመሆኑ ከአምራቹ ኩባንያ ማስረጃና፣ ቀረጥ ስለመከፈሉም ከጉምሩክ መረጃ ማቅረብ የሚችል ተሽከርካሪ በምዘና ካገኘው አጠቃላይ ውጤት ተጨማሪ የሚሆንለት 10 (አስር) ነጥብ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡ ይሁንና ካምቢዮ ብቻ ቀይሮ ከቀረበ የሚያገኘው ተጨማሪ ነጥብ አይኖርም፡፡ በዚህ የነጥብ አሰጣጥም ሞተርና ካምቢዮ ቀይሮ ለቀረበ ባለንብረት የተሰጠው ተጨማሪ ነጥብ ከፍተኛ ዕድሜ 10 (አስር) ዓመት ሆኖ በየዓመቱ 1(አንድ) ነጥብ በመቀነስ የተገጠመው አዲስ ሞተር ከ10 (አስር) ዓመት በኋላ ተመልሶ ዜሮ ይሆናል፡፡ የዚህ ዓላማ ዋነኛ ምክንያት የተሽከርካሪ ባለንብረቶች በተሽከርካሪዎቻቸው ላይ አገልግሎት ለመስጠት የሚያወጡትን ወጪ ታሳቢ በማድረግ ሚሰጡት አገልግሎት ለማበረታታት ነው፡፡በሚል ተሻሽሏል፡፡

## 3.3.4. የአገልግሎት ዘመን

ተሽከርካሪዎች እንደማንኛውም መሣሪያ የአገልግሎት ጊዜያቸው እየጨመረ በሄደ ቁጥር አገልግሎት የመስጠት ብቃታቸው (Performance) እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ የአገልግሎት ዘመን በተሽከርካሪው ፍጥነት፣ የሞተሩ ጉልበት፣ የነዳጅ ፍጆታ፣ የአካባቢ ብክለት፣ ወዘተ ላይ አሉታዊ ተፅእና ያሣድራል፡፡ ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት አንዳንድ የሀገራችን ትራንስፖርት ድርጅቶችና ማኅበራት ተሽከርካሪያቸው የተወሰነ ዓመታት ከተጠቀሙ በኋላ በአዳዲስ ሌሎች ተሽከርካሪዎች የመተካት ሁኔታ አይታይም፡፡ ይህም ድርጅቱ ለጥገና የሚያወጣው

ወጪና ጊዜ እንዲጨመር ስለሚያደርገው ለኪሣራ የመዳረግ አስተዋጽ ከፍተኛ ነው፡፡

በመሆኑም የተሽከርካሪ አገልግሎት ዘመን የኦፕሬተርነት ደረጃ ለመወሰን ከምንጠቀምባቸው መመዘኛዎች አንዱ ነው፡፡ ኦፕሬተሩ ያቀረበው ተሽከርካሪ አዲስና በመጀመሪያው ዓመት ላይ የማገኝ ከሆነ ከፍተኛውን "30%" ነጥብ ያገኛል፡፡

የተሽከርካሪው አገልግሎት ዘመን እየጨመረ በሄደ ቁጥር እንደአገልግሎት ዘመኑ ደረጃው እየተሠሳ ነጥብ ይሰጠዋል፡፡ የነጥብ አሰጣጥ ሥሌት ለማስላት የተሽከርካሪው ውጤታማ የአገልግሎት ዘመን ከፍተኛው 20 ዓመት ተደርጐ ተወስዷል፡፡

## 3.3.5. የምቾት ደህንነት እና የፋሲሊቲዎች ሁኔታ

ተሣፋሪያዎች ወደ መናኸሪያ ሲመጡ ደህንነትና ምቾታቸው መጠበቅ ያለበት ከመሆኑም በላይ፣ የሚጓዙበት ተሽከርካሪ ፋሲሊቲዎችን ያሟላ መሆን ስለሚገባውና ደህንነቱም አስተማማኝ መሆን ስላለበት አንዱ የደረጃ መስኪያ ሆኖ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡

## 3.3.6. የደኅንነት ሁኔታ

ለሕዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የቀረበው ተሽከርካሪ ላይ ያሉት መሣሪያዎች የተጓዡ ደኅንነት (Safety) ሁኔታ የኢንሹራንስ ዋስትና ውስጥ በማስገባት መስካት ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም በተሽከርካሪው ላይ የሚገኙት የደኅንነት መሣሪያዎች ሁኔታና ኢንሹራንስ እንደ ዋና የደረጃ መመዘኛ መሥፈርት ተካተዋል፡፡

## 3.3.7. የሥራ ደረጃ ፈቃድን ስለመቆጣጠር፣

በሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ ለመሰማራት የሚቀርቡ ተሽከርካሪዎች በምዝና መስፈርቱ መሰረት ባገኙት የሥራ ደረጃ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ

መሰረት ስስመስራታቸው በአገልግሎት መስጫ መናኻሪያዎች ተገቢው ቁጥጥር ይደረጋል፡፡



### 3.3.8. <u>የሥራ ደረጃ ፈቃድ መስፈርቶች፣</u>

የካቲት 2003 በተዘጋጀውና ሥራ ላይ በዋለው የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫና ሥምሪት ሥራ ሂደት አፈጻጸም መመሪያ ስተሽከርካሪዎች የሥራ ደረጃ ስመስጠት የተቀመጠው የምዘናና ብቃት ማረጋገጫ ነጥብ አሰጣጥ መስፈርቱ አንድ ወጥ መሆን ስአሰራር አመቺነት ስለሌለው በአገልግሎት ሰጪ ተሽከርካሪዎች አይነትና የሥራ ደረጃ :

- ✓ ስአገር አቋራጭ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶብሶች፣
- ✓ ስመለስተኛ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች፣
- ✓ ስአነስተኛ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች፣መስፈርቱ ስየብቻቸው ተለይቶ እንዲሰራበት ከዚህ ቀጥሎ ተዘጋጅቷል፡፡

## በባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት በመጋቢት 2005 ዓ.ም ለአገር አቋራጭ ሕዝብ ማመላለሻ አውቶብሶች የሥራ ደረጃ የምዘና ነጥብ የተዘጋጀ መሥፈርት፤

| ተ.ቁ | በመጋቢት 2005 ዓ.ም አዲስ ተሻሽሎ የቀረበ የተሽከርካሪዎች ሥራ ደረጃ መስፈርት | የተሰጠ ነጥብ ከ100 | የተቀመጠ ልዩ ሁኔታ |
|---|---|---|---|
| 1 | 1. የተሽከርካሪ አገልግሎት ዘመን/ ከ0-20 /ዓመት ባለው አድሜ የሚሰጥ፤ | 30 | |
| 2 | **ደሕንነት** | 33 | |
| 2.1 | የኢንሹራንስ ሁኔታ፡-<br>ለተሽከርካሪው አጠቃላይ ኢንሹራንስ የተገባለት ሆኖ ከቀረበ (ለመኪናው፤ ሠራተኞች፤ ተሣፋሪውና ለተሽከርካሪው) | 15 | |
| 2.2 | **ጥገና ጋራዥ (Maintenance) በተመለከተ፡-** | 5 | የራሳቸው ጋራዥ ከፍተው ለሚጠቀሙ ትራንስፖርት ማሕበራትና ድርጅቶች ደበልጥ እንዲበረቱ 100% ጥማሪ ወይም 5(አምስት) ነጥብ በቦነስ መልክ ይሰጣል፡፡ |
| | 2.2.1 በተደራጀበት ትራንስፖርት ማኅበር (ድርጅት) ሕጋዊ የጥገና ተቋም ያለውና በዚሁ መገልገል ከቻለ፤ | | |
| | 2.2.2 የብቃት ማረጋገጫ ካለውና ትራንስፖርት መ፤ሕበራቱ ለአባሎቻቸው የጥገና አገልግሎት እንዲያገኙ ከውልና ማስረጃ የተረጋገጠ የሥምምነት ሰነድ ማቅረብ የሚችሉ ስለመጠገኑም መስሪያ ቤቱ ሲጠይቅ ማስረጃ የሚያቀርቡ ከሆነ፤ | 2.5 | |
| 2.3 | **2.3 የደኅንነት ቀበቶ** | 5 | |
| | 2.3.1 ለሁሉም ተሣፋሪዎች የተሟላ የደህንነት ቀበቶ ያለው ከሆነ፤ | 5 | |
| | 2.3.2 ከሾፌሩ በስተቀኝ ጎኑና ከጋባው ባሉ ሦስት ተጓዥ መንገደኞች ብቻ የሚያገለግል የደህንነት ቀበቶ ካለው፤ | 3 | |
| | 3.3.3 ከሾፌሩ በስተቀኝ ጎኑና ከጋባው ባሉ ሁለት ተጓዥ መንገደኞች ብቻ የሚያገለግል የደህንነት ቀበቶ ካለው፤ | 2 | |

| ተ.ቁ | በመጋቢት 2005 ዓ.ም አዲስ ተሻሽሎ የቀረበ የተሽከርካሪዎች ሥራ ደረጃ መስፈርት | | የተሰጠ ነጥብ ከ100 | የተቀመጠ ልዩ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|
| 2.4 | የአደጋ ጊዜ መውጫን በተመለከተ:- | | 5 | |
| | 2.4.1 | ሙሉ መስኮቶቹ ተሰባሪ መስታወት ያለውና የተሟላ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ፣ | 5 | |
| | 2.4.2 | አንድ ወጥ የሆነ የአደጋ ጊዜ መውጫ መስኮት ያለውና መስታወቱም ተሰባሪ ከሆነ፣ | 3 | |
| | 2.4.3 | መስኮቱ በግማሽ መጠን ሆኖ መስታወቱ ተሰባሪ የሆነና ለአደጋ ጊዜ መውጫነት የሚያገለግል ካለው፣ | 1 | |
| 2.5 | የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ዝግጅትን በተመለከተ:-<br>✓ መጠኑ 25 ሣ.ሜ X በ20 ሣ.ሜ X 30 ሣ.ሜ የሆነ የመጀመሪያ ሕክምና መስጫ ሣጥን፣<br>✓ (መቀስ ብዛት 2 (ሁለት)፣ ፋሻ በዓይነት፣ ጓንት፣ አልኮል፣ ጥጥ፣ የኦፕሬሽን ቢላ፣ የጣት እና የቀስል ፕላስተር፣ አነስተኛ ፎጣ፣ የኒኬል ጉድጓዳ ሣህን ዲያሜትሩ 15 ሣ.ሜትር የሆነ መርጃ ተሟልቶ መያዝ አለበት::) | | 1 | ለሁሉም የስራ ደረጃዎች አስገዳጅ የሆነና ካልተሟላ ፈቃድ የማያሰጥ ነው ፣ |
| 2.6 | ከሾፌሩ መቀመጫ ፊት ለፊት ባለው መስታወት በስተግራ በኩል የፀሐይ መከለያ ካለው፣ | | 1 | |
| 2.7 | የእሳት አደጋ ማጥፊያ መጠኑ 3 ኪሎ ግራም የሚመዝን ስጉዞ የሚጠቀም ከሆነና ማረጋገጫ ካቀረበ፣ | | 1 | |
| 3 | ምቾትን በተመለከተ፤ | | 29 | |
| 3.1. | ቦታ | | 12 | |
| | 3.1.1 | የአንድ ተሣፋሪ የመቀመጫ ወንበር ስፋቱ 400 X 400 ሚ.ሜ አሟልቶ መቅረብ አለበት::፣ | 5 | ለሁሉም የስራ ደረጃዎች አስገዳጅ የሆነና ካልተሟላ ፈቃድ የማያሰጥ ነው |
| | 3.1.2 | በሚጓጓዘው መንገደኛ መቀመጫ ወንበር መካከል መኖር ስለሚገባው የቦታ ስፋትን በተመለከተ | 4 | |
| | ሀ. | የመንገደኛ መቀመጫ ወንበር ከፊትና ኋላ ያለው የቦታ ስፋት 750 ሚ.ሜ ከሆነ ፣ | 4 | |
| | ለ. | የመንገደኛ መቀመጫ ወንበር ከፊትና ኋላ ያለው የቦታ ስፋት 740 ሚ.ሜ ከሆነ ፣ | 3 | |
| | ሐ. | የመንገደኛ መቀመጫ ወንበር ከፊትና ኋላ ያለው የቦታ ስፋት 730 ሚ.ሜ ከሆነ ፣ | 2 | ለሁሉም የስራ ደረጃዎች አስገዳጅ የሆነና ካልተሟላ ፈቃድ የማያሰጥ |

| ተ.ቁ | በመጋቢት 2005 ዓ.ም አዲስ ተሻሽሎ የቀረበ የተሽከርካሪዎች ሥራ ደረጃ መስፈርት | የተሰጠ ነጥብ ከ100 | የተቀመጠ ልዩ ሁኔታ |
|---|---|---|---|
| | 3.1.3 ከገራና ቀኝ በወንበሮች መካከል ስለሚኖር የመተላለፊያ ቦታ ስፋት | 3 | |
| | ሀ. በወንበሮች መካከል የሚኖር መተላለፊያ ቦታ ስፋት 370 ሚ.ሜ ከሆነ፣ | 3 | |
| | ለ. በወንበሮች መካከል የሚኖር መተላለፊያ ቦታ ስፋት 360 ሚ.ሜ ከሆነ፣ | 2 | |
| | ሐ. በወንበሮች መካከል የሚኖር መተላለፊያ ቦታ ስፋት 350 ሚ.ሜ ከሆነ፣ | 1.5 | ለሁሉም ደረጃዎች አስገዳጅ የሆነና ካልተሟላ ፈቃድ የማያሰጥ ነው ፣ |
| 3.2 | **የመቀመጫ ወንበር ልብስን በተመለከተ፣** | 3 | |
| | 3.2.1 የወንበር ልብስ | | |
| | ሀ- የመቀመጫ ወንበር ልብስ አዲስና ከቆዳ መሰል የተሰራ ከሆነ፣ | 3 | |
| | ለ- የመቀመጫ ወንበር ልብስ አዲስና ከቆዳ መሰል የተሰራ አዲስ ባይሆንም ያልተቀዳደና ያልተጫጫረ አሟልቶ ከቀረበ፣ | 2 | |
| | ሐ- የመቀመጫ ወንበር ልብስ አዲስና ከጥጥ ጨርቅ የተሰራ አዲስ ከሆነ፣ | 1.5 | |
| | መ- የመቀመጫ ወንበር ልብስ ከጨርቅ የተሰራና አዲስም ባይሆን ያልተቀዳደና ፅዳቱ የተጠበቀ ከሆነ፣ | 1 | |
| 3.3 | የወንበሮች ምቹነት በተመለከተ፡- | 3 | |
| | 3.3.1 ወንበሮች የእጅ መደገፊያ ያለውና ለተንዡም መቀመጫ የእጅ መያዣና ምቾት ያለው ከሆነ፣ | 3 | |
| | 3.3.2 ወንበሮች ከተንዡም መቀመጫ ፊት ለፊት የእጅ መያዣ ያለውና ምቾት ያለው ከሆነ፣ | 2 | |
| | 3.3.3 ወንበሮች የእጅ መያዣና መደገፊያ ባይኖረውም ለተገልጋዩ ምቾት ያለው ከሆነ፣ | 1 | |
| 3.4 | 3.4 **የአየር መቆጣጠሪያ** (AirConditioner Ventilator & Manual)፣ | 3 | |
| | 3.4.1 ለሁሉም ተንዥ መንገደኛ የሚያገለግል AC ያለው ከሆነ፣ | 3 | |
| | 3.4.2 ደረጃውን የጠበቀ 2 ወይም 3 ቦታ ላይ የተዘጋጀ በኤሌክትሪክ የሚሰራ ፋን (Ventilator) ያለው ከሆነ፣ | 2 | |
| | 3.4.3 በመኪናው የመሐል ጣሪያ በእጅ (Manual) የሚከፈት የአየር ማስገቢያ ያለው ከሆነ፣ | 1 | |

| ተ.ቁ | በመጋቢት 2005 ዓ.ም አዲስ ተሻሽሎ የቀረበ የተሽከርካሪዎች ሥራ ደረጃ መስፈርት | የተሰጠ ነጥብ ከ100 | የተቀመጠ ልዩ ሁኔታ |
|---|---|---|---|
| 3.5. | **የተሽከርካሪ ወለል** | 3 | |
| | 3.5.1 የተሽከርካሪው ወለል ከአልሙኒየም ሻካርድ የለበሰ ከሆነ፣ | 3 | |
| | 3.5.2 የተሽከርካሪው ወለል ባለ ሳንቲም ፕላስቲክ | 2 | ለሁሉም የሥራ ደረጃዎች አስገዳጅ የሆነና ካልተሟላ ፈቃድ የማያሰጥ ነው ፤ |
| 3.6. | **የመጋረጃ ይዘትና ጥራት ሁኔታ፤-** | 2 | |
| | 3.6.1 ከፋብሪካ ሲወጣ የነበረውን መጋረጃ በጥሩ ሁኔታ ያሟላ ከሆነ፣ | 2 | |
| | 3.6.2 ከሐር ጨርቅ የተዘጋጀ አዲስ መጋረጃ አሟልቶ ከቀረበ፣ | 1.5 | |
| | 3.6.3 ከጥጥ ጨርቆች አይነት የተሰራና በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኝ መጋረጃ ያሟላ ከሆነ ፤ | 1 | ለሁሉም የሥራ ደረጃዎች አስገዳጅ የሆነና ካልተሟላ ፈቃድ የማያሰጥ ነው ፤ |
| 3.7. | **መስተንግዶ፤-** | 3 | |
| | 3.7.1 ለተጓዥ መንገደኞች አንባሻ (ኩኪስ) በነፃ የሚያቀርብ፣ ለስላሣ መጠጥ እና የታሸገ ውሃ በፋብሪካው ዋጋ የሚያቀርብ፣ | 1 | ለደረጃ 1ና2 አስገዳጅ የሆነና ካልተሟላ ፈቃድ የማያሰጥ ነው ፤ |
| | 3.7.2 ደረጃውን የጠበቀ ማቀዝቀዣ ፍሪጅ ያሟላ ከሆነ፣ | 2 | |
| 4 | **የቅድመ ጉዞ ዝግጅትና ፋሲሊቲዎች** | 5 | |
| | 4.1 በማህበሩ ወይም በድርጅቱ ስሚሰጥ አገልግሎት የሚውል ከመናኸሪያ ውጪ በእያንዳንዱ ማሕበር በተናጥል 1 (አንድ) የራሱ የሆነ የትኬት ቢሮ ከፍቶ አገልግሎት ከሰጠና ለተገልጋዩ ሕዝብም ወደ መናኸሪያ የሚደርስበት የሰርቪስ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ፣ | 5 | ለደረጃ 1 እና 2 አስገዳጅ የሆነና ደህ ካልተሟላ ፈቃድ የማያሰጥ ነው ፤ |
| | 4.2 ለተገልጋዩ ሕዝብም ከመናኸሪያ ውጪ በአምስቱም የጉዞ መውጫ በሮች በአማካይ ቦታዎች ማሕበራት በጋራ 16 (አስራ ስድስት) የትኬት መሸጫ ቢሮ ከፍተው አገልግሎት ከሰጡና ተገልጋዩንም ሕዝብ በሌሊት ወደ መናኸሪያ የሚጓጓዝበት የሰርቪስ አገልግሎት ካቀረቡና አገልግሎት የሚሰጡ ከሆነ ፤ | 5 | |
| 5 | **ሌሎች** | 3 | |
| | 5.1 ለመንገደኞች በጉዞ ወቅት ዘና እንዲሉ የሚያግዝ የDVD,Tape እና 15 ኢንችና በላይ በሆነ TV (ሶስቱንም አሟልቶ) ከቀረበ፣ | 3 | ለደረጃ 1 እና 2 አስገዳጅ የሆነና ደህ ካልተሟላ ፈቃድ የማያሰጥ ነው ፤ |



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

ተሽከርካሪው ያገኘው አጠቃላይ ነጥብ ______ የተሰጠው የሥራ ደረጃ ______

**መግለጫ:*-**

ቀደም ሲል በመመሪያው ክፍል ሁለት አንቀጽ 3 (የኦፕሬተርነት ፈቃድ አይነቶችና የደረጃ መስፈርት) በሚል ርዕስ በንኡስ አንቀጽ 3.3 በተራ ቁጥር 3.3.3 (የደረጃ 1፣2 እና 3 ኦፕሬተርነት ደረጃ መስፈርት ማብራሪያዎች) የተቀመጠው መስፈርትና የነጥብ አሰጣጥ የተገለጸው በተጨማሪም አዲስ ሞተርና ካምቢዮ ገዝቶ ያስገጠመ ስለሆነም አዲስ መሆኑንና ምንም አገልግሎት ያልሰጠ ስለመሆኑ ከአምራቹ ኩባንያ ማስረጃና፣ ቀረጥ ስለመከፈሉም ከጉምሩክ መረጃ ማቅረብ የሚችል ተሽከርካሪ በምዘና ካገኘው አጠቃላይ ውጤት ተጨማሪ የሚሆንለት 10 (አስር) ነጥብ እንዲያገኝ ይደረጋል:: ይሁንና ካምቢዮ ብቻ ቀይሮ ከቀረበ የሚያገኘው ተጨማሪ ነጥብ አይኖርም:: በዚህ የነጥብ አሰጣጥም ሞተርና ካምቢዮ ቀይሮ ለቀረበ ባለንብረት የተሰጠው ተጨማሪ ነጥብ ከፍተኛ ዕድሜ 10 (አስር) ዓመት ሆኖ በየዓመቱ 1(አንድ) ነጥብ በመቀነስ የተገጠመው አዲስ ሞተር ከ10 (አስር) ዓመት በኋላ ተመልሶ ዜሮ ይሆናል:: የዚህ ዓላማ ዋነኛ ምክንያት የተሽከርካሪ ባለንብረቶች በተሽከርካሪዎቻቸው ላይ አገልግሎት ለመስጠት የሚያወጡትን ወጪ ታሳቢ በማድረግ የሚያደርጉትን ጥረት ነው:: :በሚል ተሻሽሏል::

## የአገር አቋራጭ ሕዝብ ማመላለሻ አውቶብሶች የሥራ ደረጃ አሰጣጥ

## የምዘና ነጥብ መስጫ መሥፈርት የነጥብ ማጠቃለያ

| ተ.ቁ | መደበኛ ደረጃ | ማለፊያ ነጥብ ከመቶ % |
|---|---|---|
| 1. | አንድ | 80-100 |
| 2. | ሁለት | 65-79.99 |
| 3. | ሦስት | 50-64.99 |

| ተ.ቁ | አይነት | ነጥብ |
|---|---|---|
| 1. | የተሽከርካሪ ዕድሜ | 30 |
| 2. | ደህንነት | 33 |
| 3. | ምቾት | 29 |
| 4. | ቅድመ ጉዞ ዝግጅትና ፋሲሊቲዎች | 5 |
| 5. | ሌሎች | 3 |
| | ድምር | 100% |

## መጋቢት 2005 ዓ.ም. አዲስ የተሻሻለው የመለስተኛ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶብሶች

## የሥራደረጃ አሰጣጥ የምዘና ነጥብ መስጫ መሥፈርት

| ተ.ቁ | የመሥፈርት ዝርዝር | ልዩ ሁኔታ | የተሻሻለው ነጥብ ከ100 | ያገኘው ነጥብ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የተሽከርካሪ አገልግሎት ዘመን/ ከ0-20 /ዓመት ባለው እድሜ የሚሰጥ፣ | | 30 | |
| 2. | ደኅንነት | | 34 | |
| 2.1 | የኢንሹራንስ ሁኔታ፡-<br>ለተሽከርካሪው አጠቃላይ ኢንሹራንስ የተገባለት ሆና ከቀረበ | | 15 | |

| ተ.ቁ | የመሥፈርት ዝርዝር | ልዩ ሁኔታ | የተሻሻለው ነጥብ ከ100 | ያገኘው ነጥብ |
|---|---|---|---|---|
| | ( ስመኪናው ሠራተኞች፣ ስተሣፋሪውና ስተሸከርካሪው ) | | | |
| 2.2 | **ጥገና ጋራዥ (Maintenance) በተመለከተ:-**<br><br>2.2.1 በተደራጀበት ትራንስፖርት ማኅበር (ድርጅት) ሕጋዊ የጥገና ተቋም ያለውና በዚሁ መገልገል ከቻለ፣ | የራሳቸው ጋራዥ ለከፈቱና ለሚጠቀሙ ትራንስፖርት ማሕበራትና ድርጅቶች 100 % ጥማሪ ወይም 5 (አምስት) ነጥብ በቦነስ መልክ ይሰጣል:: | 5 | |
| | 2.2.2 የብቃት ማረጋገጫ ካለውና ትራንስፖርት መ፣ሕበሬቱ ለአባሎቻቸው የጥገና አገልግሎት እንዲያገኙ ከውልና ማስረጃ የተረጋገጠ የሥምምነት ሰነድ ማቅረብ የሚችሉ ስለመጠገኑም መሰሬያ ቤቱ ሲጠይቅ ማስረጃ የሚያቀርቡ ከሆነ፤ | | 2.5 | |
| 2.3 | **የደኅንነት ቀበቶ** | | 5 | |
| | 2.3.1 ለሁሉም ተሣፋሪዎች የተሟላ የደህንነት ቀበቶ ያለው ከሆነ፣ | | 5 | |
| | 2.3.2 ከሾፌሩ በስተቀኝ ጎኑና ከኃላው ላሉ ሦስት ተጓዥ መንገደኞች ብቻ የሚያገለግል የደህንነት ቀበቶ ካለው፣ | | 3 | |
| | 2.3.3 ከሾፌሩ በስተቀኝ ጎኑና ከኃላው ላሉ ሁለት ተጓዥ መንገደኞች ብቻ የሚያገለግል የደህንነት ቀበቶ ካለው፤ | | 2 | |
| 2.4 | የአደጋ ጊዜ መውጫን በተመለከተ:- | | 5 | |
| | 2.4.1 ሙሉ መስኮቶቹ ተሰባሪ መስታወት ያለውና የተሟላ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ፣ | | 5 | |
| | 2.4.2 አንድ ወጥ የሆነ የአደጋ ጊዜ መውጫ መስኮት ያለውና መስታወቱም ተሰባሪ ከሆነ፣ | | 3 | |
| | 2.4.3 መስኮቱ በግማሽ መጠን ሆኖ መስታወቱ ተሰባሪ የሆነና ለአደጋ ጊዜ መውጫነት የሚያገለግል ካለው፣ | | 1.5 | |
| 2.5 | የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ዝግጅትን በተመለከተ:-<br><br>✓ መጠኑ 25 ሣ.ሜ X በ20 ሣ.ሜ X 30 ሣ.ሜ የሆነ የመጀመሪያ ሕክምና መስጫ ሣጥን፣<br><br>✓ (መቀስ ብዛት 2 (ሁለት)፣ ፋሻ በዓይነት፣ ጂቪ፣ አልኮል፣ ጥጥ፣ የኦንሬሽን ቢላ፣ የጣት እና የቁስል ፕላስተር፣ አነስተኛ ፎጣ፣ የኒኬል ጉድጓዳ ሣህን ዲያሜትሩ 15 ሣ.ሜትር የሆነ መርጃ | ለሁሉም የስራ ደረጃዎች አስገዳጅ የሆነና ካልተሟላ ፈቃድ የማያሰጥ ነው ፣ | 2 | |

| ተ.ቁ | የመሥፈርት ዝርዝር | ልዩ ሁኔታ | የተሻሸለው ነጥብ ከ100 | ያገኘው ነጥብ |
|---|---|---|---|---|
| | ተሚልተ መያዝ አለበት።) | | | |
| 2.6 | ከሾፌሩ መቀመጫ ፊት ለፊት ባለው መስታወት በስተግራ በኩል በየአቅጣጫው ሲዛዛር የሚችል የፀሐይ መከለያ ካለው፤ | | 2 | |
| 3 | ምቾትን በተመለከተ፤ | | 34 | |
| 3.1 | ቦታ | | 12 | |
| | 3.1.1 የአንድ ተሣፋሪ የመቀመጫ ወንበር ስፋቱ 400 X 400 ሚ.ሜ አሚልቶ መቅረብ አለበት።፤ | ለሁሉም የስራ ደረጃዎች አስገዳጅ የሆነና ካልተሚሳ ፈቃድ የማያሰጥ ነው ፤ | 5 | |
| | 3.1.2 በሚጓጓዘው መንገደኛ መቀመጫ ወንበር መካከል መኖር ስለሚገባው የቦታ ስፋትን በተመለከተ | | 4 | |
| | ሀ. የመንገደኛ መቀመጫ ወንበር ከፊትና ኋላ ያለው የቦታ ስፋት 750 ሚ.ሜ ከሆነ ፤ | | 4 | |
| | ለ. የመንገደኛ መቀመጫ ወንበር ከፊትና ኋላ ያለው የቦታ ስፋት 740 ሚ.ሜ ከሆነ ፤ | | 3 | |
| | ሐ. የመንገደኛ መቀመጫ ወንበር ከፊትና ኋላ ያለው የቦታ ስፋት 730 ሚ.ሜ ከሆነ ፤ | ለሁሉም የስራ ደረጃዎች አስገዳጅ የሆነና ካልተሚሳ ፈቃድ የማያሰጥነው | 2 | |
| | 3.1.3 ከግራና ቀኝ በወንበሮች መካከል ስለሚኖር የመተሳለፊያ ቦታ ስፋት፤ | | 3 | |
| | ሀ. በወንበሮች መካከል የሚኖር መተሳለፊያ ቦታ ስፋት 370 ሚ.ሜ ከሆነ፤ | | 3 | |

| ተ.ቁ | የመሥፈርት ዝርዝር | ልዩ ሁኔታ | የተሻሻለው ነጥብ ከ100 | ያገኘው ነጥብ |
|---|---|---|---|---|
| | ለ. በወንበሮች መካከል የሚኖር መተላለፊያ ቦታ ስፋት 360 ሚ.ሜ ከሆነ፣ | | 2 | |
| | ሐ. በወንበሮች መካከል የሚኖር መተላለፊያ ቦታ ስፋት 350 ሚ.ሜ ከሆነ፣ | ለሁሉም ደረጃዎች አስገዳጅ የሆነና ካልተሟላ ፈቃድ የማያሰጥ ነው ፡ | 1.5 | |
| 3.2 | የመቀመጫ ወንበር ልብስ በተመለከተ፡- | | 4 | |
| | ሀ. የመቀመጫ ወንበር ልብስ አዲስና ከቆዳ መሠል የተሠራ ከሆነ፣ | | 4 | |
| | ለ. የመቀመጫ ወንበር ልብስ አዲስና ከቆዳ መሠል የተሠራ አዲስ ባይሆንም ያልተቀደደና ያልተጫጫረ አሚልት ከቀረበ፣ | | 2 | |
| | ሐ. የመቀመጫ ወንበር ልብስ አዲስና ከጥጥ ጨርቅ የተሠራ አዲስ ከሆነ፣ | | 1.5 | |
| | መ. የመቀመጫ ወንበር ልብስ ከጨርቅ የተሠራና አዲስም ባይሆን ያልተቀደደና ፅዳቱ የተጠበቀ ከሆነ፣ | | 1 | |
| 3.3 | የወንበሮች ምቹነት በተመለከተ፡- | | 3 | |
| | 3.3.1 ወንበሮች የእጅ መደገፊያ ያለውና ለተጓዡም መቀመጫ የእጅ መያዣና ምቾት ያለው ከሆነ፣ | | 3 | |
| | 3.3.2 ወንበሮች ከተጓዡም መቀመጫ ፊት ለፊት የእጅ መያዣ ያለውና ምቾት ያለው ከሆነ፣ | | 2 | |
| | 3.3.3 ወንበሮች የእጅ መያዣና መደገፊያ ባይኖረውም ለተገልጋዩ ምቾት ያለው ከሆነ፣ | | 1 | |
| 3.4 | **የአየር መቆጣጠሪያ** (AirConditioner Ventilator & Manual)፣ | | 4 | |
| | 3.4.1 ለሁሉም ተጓዥ መንገደኛ የሚያገለግል AC ያለው ከሆነ፣ | | 4 | |
| | 3.4.2 ደረጃውን የጠበቀ 2 ወይም 3 ቦታ ላይ የተዘጋጀ በኤሌክትሪክ የሚሰራ ፋን (Ventilator) ያለው ከሆነ፣ | | 2.5 | |
| | 3.4.3 በመኪናው የመሐል ጣሪያ በእጅ (Manual) የሚከፈት የአየር ማስገቢያ ያለው ከሆነ፣ | | 1.5 | |
| 3.5 | የእሳት አደጋ ማጥፊያ መጠኑ 3 ኪሎ ግራም የሚመዝን ለጉዞ የሚጠቀም ከሆነና ማረጋገጫ ካቀረበ፣ | | 2 | |

| ተ.ቁ | የመሥፈርት ዝርዝር | ልዩ ሁኔታ | የተሻሻለው ነጥብ ከ100 | ያገኘው ነጥብ |
|---|---|---|---|---|
| 3.6 | የተሽከርካሪ ወለልን በተመለከተ፡- | | 3 | |
| | 3.6.1 የተሽከርካሪው ወለል ሙሉ ለሙሉ የአልሙኒየም ሻካርድ የለበሰ ከሆነ፤ | | 3 | |
| | 3.6.2 የተሽከርካሪው ወለል ሙሉ ለሙሉ ባለሳንቲም ኘላስቲክ የለበሰ ከሆነ፤ | ለሁሉም የሥራ ደረጃዎች አስገዳጅ የሆነና ካልተሟላ ፈቃድ የማያሰጥ ነው ፤ | 2 | |
| 3.7 | የመጋረጃ ይዘትና ጥራት ሁኔታ፡- | | 2 | |
| | 3.7.1 ከፋብሪካ ሲወጣ የነበረውን መጋረጃ በጥሩ ሁኔታ ያሟላ ከሆነ፤ | | 2 | |
| | 3.7.2 ከሐር ጨርቅ የተዘጋጀ አዲስ መጋረጃ አሟልቶ ከቀረበ፤ | | 1.5 | |
| | 3.7.3 ከጥጥ ጨርቆች አይነት የተሰራና በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኝ መጋረጃ ያሟላ ከሆነ ፤ | ለሁሉም የሥራ ደረጃዎች አስገዳጅ የሆነና ካልተሟላ ፈቃድ የማያሰጥ ነው ፤ | 1 | |
| 3.8 | **መስተንግዶ፡-** | | 4 | |
| | 3.8.1 ለተጓዥ መንገደኞች አንባሻ (ኩኪስ) በነፃ የሚያቀርብ፤ ለለሳሣ መጠጥ እና የታሸገ ውሃ በፋብሪካው ዋጋ የሚያቀርብ፤ | ለደረጃ 1፣2 አስገዳጅ የሆነና ካልተሟላ ፈቃድ የማያሰጥ ነው ፤ | 2 | |
| | 3.8.2 ደረጃውን የጠበቀ ማቀዝቀዣ ፍሪጅ ያሟላ ከሆነ፤ | | 3 | |
| 4 | ሌሎች | | 4 | |
| | 4.1 ለመንገደኞችበጉዞ ወቅት ዘና እንዲሉ የሚያገዝ የDVD,Tape እና 15 ኢንችና በላይ በሆነ TV (ሶስቱንም አሟልቶ) ከቀረበ፤ | ለደረጃ 1 እና 2 አስገዳጅ የሆነ ደህ ካልተሟላ ፈቃድ የማያሰጥ ነው ፤ | 4 | |

*ተሽከርካሪው ያገኘው አጠቃላይ ነጥብ ________________ ደረጃ________*

***መግለጫ:*-***

ቀደም ሲል በመመሪያው ክፍል ሁለት አንቀጽ 3 (የኦፕሬተርነት ፈቃድ አይነቶችና የደረጃ መስፈርት) በሚል ርዕስ በንኡስ አንቀጽ 3.3 በተራ ቁጥር 3.3.3 (የደረጃ 1፣2 እና 3 ኦፕሬተርነት ደረጃ መስፈርት ማብራሪያዎች) የተቀመጠው መስፈርትና የነጥብ አሰጣጥ የተገለጸው በተጨማሪም አዲስ ሞተርና ካምቢዮ

ገዝቶ ያስገጠመ ለዚህም አዲስ መሆኑንና ምንም አገልግሎት ያልሰጠ ስለመሆኑ ከአምራቹ ኩባንያ ማስረጃና ቀረጥ ስለመከፈሉም ከጉምሩክ መረጃ ማቅረብ የሚችል ተሽከርካሪ በምዘና ካገኘው አጠቃላይ ውጤት ተጨማሪ የሚሆንለት 10 (አስር) ነጥብ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡ ይሁንና ካምቢዮ ብቻ ቀይር ከቀረበ የሚያገኘው ተጨማሪ ነጥብ አይኖርም፡፡ በዚህ የነጥብ አሰጣጥም ሞተርና ካምቢዮ ቀይር ለቀረበ ባለንብረት የተሰጠው ተጨማሪ ነጥብ ከፍተኛ ዕድሜ 10 (አስር) ዓመት ሆኖ በየዓመቱ 1(አንድ) ነጥብ በመቀነስ የተገጠመው አዲስ ሞተር ከ10 (አስር) ዓመት በኋላ ተመልሶ ዜሮ ይሆናል፡፡ የዚህ ዓላማ ዋነኛ ምክንያት የተሽከርካሪ ባለንብረቶች በተሽከርካሪዎቻቸው ላይ አገልግሎት ለመስጠት የሚያወጡትን ወጪ ታሣቢ በማድረግ ሚሰጡት አገልግሎት ለማበረታታት ነው፡፡በሚል ተሻሽሏል፡፡

# *የመለስተኛ ሕዝብ ማመላለሻ አውቶብሶች የሥራ ደረጃ አሰጣጥ*

## *የምዘና ነጥብ መስጫ መሥፈርት የነጥብ ማጠቃለያ*

### *የነጥብ ማጠቃለያ*

| ተ.ቁ | መደበኛ ደረጃ | ማስፈያ ነጥብ ከመቶ % |
|---|---|---|
| 1. | አንድ | 80-100 |
| 2. | ሁለት | 65-79.99 |
| 3. | ሦስት | 50-64.99 |

| *ተ.ቁ* | *አይነት* | *ነጥብ* |
|---|---|---|
| 1. | የተሽከርካሪ ዕድሜ | 30 |

| | | |
|---|---|---|
| 2. | ደህንነት | 34 |
| 3. | ምቾት | 32 |
| 5. | ሌሎች | 4 |
| | ድምር | 100% |

## <u>*መጋቢት 2005 ዓ.ም. አዲስ የተዘጋጀ የአነስተኛ ሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች*</u>

## <u>*የሥራደረጃ አሰጣጥ የምዘና ነጥብ መስጫ መሥፈርት*</u>

| *ተ.ቁ* | *የመሥፈርት ዝርዝር* | *ልዩ ሁኔታ* | *የተሰጠው ነጥብ ከ100* | *ያገኘው ነጥብ* |
|---|---|---|---|---|
| 1. | **የተሽከርካሪ አገልግሎት ዘመን/ ከ0-20 /ዓመት ባለው እድሜ የሚሰጥ፣** | | 30 | |
| 2. | **ደኅንነት** | | 30 | |
| 2.1 | **የኢንሹራንስ ሁኔታ፡-**<br>**ለተሽከርካሪው አጠቃላይ ኢንሹራንስ የተገባለት ሆኖ ከ ቀረበ**<br>**( ለመኪናው ሠራተኞች፣ ለተሣፋሪውና ለተሽከርካሪው)** | | 15 | |
| | **ጥገና ጋራዥ (Maintenance) በተመለከተ፡-** | | 5 | የራሳቸው ጋራዥ ለከፍተኛ ለሚጠቀሙ ትራንስፖርት ማሕበራትና ድርጅቶች 100 % ጥማሪ ወይም 5 (አምስት) ነጥብ |

| ተ.ቁ | የመሥፈርት ዝርዝር | ልዩ ሁኔታ | የተሻሻለው ነጥብ ከ100 | ያገኘው ነጥብ |
|---|---|---|---|---|
| | | | | በቦነስ መልክ ይሰጣል፡፡ |
| | 2.2.1 በተደራጀበት ትራንስፖርት ማኅበር (ድርጅት) ሕጋዊ የጥገና ተቋም ያለውና በዚሁ መገልገል ከቻለ፣ | | 5 | |
| | 2.2.2 የብቃት ማረጋገጫ ካለውና ትራንስፖርት መ፣ሕበራቱ ለአባሎቻቸው የጥገና አገልግሎት እንዲያገኙ ከውልና ማስረጃ የተረጋገጠ የምምምነት ሰነድ ማቅረብ የሚችሉ ስለመጠንም መስሪያ ቤቱ ሲጠይቅ ማስረጃ የሚያቀርቡ ከሆነ፣ | | 2.5 | |
| 2.3 | **የደኅንነት ቀበቶ** | | 7 | |
| | 2.3.1 ለሁሉም ተሣፋሪዎች የተሟላ የደህንነት ቀበቶ ያለው ከሆነ፣ | | 7 | |
| | 2.3.2 ከሾፌሩ በስተቀኝ ጎኑና ከኃላው ባሉ ሦስት ተጓዥ መንገደኞች ብቻ የሚያገለግል የደህንነት ቀበቶ ካለው፣ | | 5 | |
| | 2.3.3 ከሾፌሩ በስተቀኝ ጎኑና ከኃላው ባሉ ሁለት ተጓዥ መንገደኞች ብቻ የሚያገለግል የደህንነት ቀበቶ ካለው፣ | | 3 | |
| 2.4 | የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ዝግጅትን በተመለከተ፡-<br>✓ መጠኑ 25 ሣ.ሜ X በ20 ሣ.ሜ X 30 ሣ.ሜ የሆነ የመጀመሪያ ሕክምና መስጫ ሣጥን፣<br>✓ (መቀስ ብዛት 2 (ሁለት)፣ ፋሻ በዓይነት፣ ጂቪ፣ አልኮል፣ ጥጥ፣ የኦክሲጅን ቢላ፣ የጣት እና የቀስል ንባስተር፣ እነስተኛ ፎጣ፣ የኒኬል ጉድጓዳ ሣህን ዲያሜትሩ 15 ሣ.ሜትር የሆነ መርጃ ተሟልቶ መያዝ አለበት፡፡) | ለሁሉም የስራ ደረጃዎች አስገዳጅ የሆነና ካልተሟላ ፈቃድ የማያሰጥ ነው ፣ | 2 | |
| 3 | **ምቾትን በተመለከተ፤** | | 38 | |
| 3.1 | ቦታ | | 18 | |
| | 3.1.1 የአንድ ተሣፋሪ የመቀመጫ ወንበር ስፋቱ 400 X 400 ሚ.ሜ አሟልቶ መቅረብ አለበት፡፡፣ | ለሁሉም የስራ ደረጃዎች አስገዳጅ የሆነና ካልተሟላ ፈቃድ የማያሰጥ ነው ፣ | 6 | |
| | 3.1.2 በሚጓጓዘው መንገደኛ መቀመጫ ወንበር መካከል መኖር ስለሚገባው የቦታ ስፋትን በተመለከተ | | 6 | |
| | ሀ. የመንገደኛ መቀመጫ ወንበር ከፊትና ኋላ ያለው የቦታ ስፋት 750 ሚ.ሜ ከሆነ ፣ | | 6 | |

| ተ.ቁ | የመሥፈርት ዝርዝር | ልዩ ሁኔታ | የተሰጠው ነጥብ ከ100 | ያገኘው ነጥብ |
|---|---|---|---|---|
| | ለ. የመንገደኛ መቀመጫ ወንበር ከፊትና ኋላ ያለው የቦታ ስፋት 740 ሚ.ሜ ከሆነ ፤ | | 3 | |
| | ሐ. የመንገደኛ መቀመጫ ወንበር ከፊትና ኋላ ያለው የቦታ ስፋት 730 ሚ.ሜ ከሆነ ፤ | ለሁሉም የስራ ደረጃዎች እስገዳጅ የሆነና ካልተሟላ ፈቃድ የማያሰጥነው፡ | 1.5 | |
| | 3.1.3 ከገሬና ቀኝ በወንበሮች መካከል ስለሚኖር የመተላለፊያ ቦታ ስፋት | | 6 | |
| | ሀ. በወንበሮች መካከል የሚኖር መተላለፊያ ቦታ ስፋት 370 ሚ.ሜ ከሆነ፤ | | 6 | |
| | ለ. በወንበሮች መካከል የሚኖር መተላለፊያ ቦታ ስፋት 360 ሚ.ሜ ከሆነ፤ | | 4 | |
| | ሐ. በወንበሮች መካከል የሚኖር መተላለፊያ ቦታ ስፋት 350 ሚ.ሜ ከሆነ፤ | ለሁሉም ደረጃዎች እስገዳጅ የሆነና ካልተሟላ ፈቃድ የማያሰጥ ነው ፤ | 2 | |
| 3.2 | የመቀመጫ ወንበር ልብስ በተመለከተ፡- | | 4 | |
| | ሀ. የመቀመጫ ወንበር ልብስ አዲስና ከቆዳ መሠል የተሠራ ከሆነ፤ | | 4 | |
| | ለ. የመቀመጫ ወንበር ልብስ አዲስና ከቆዳ መሠል የተሠራ አዲስ ባይሆንም ያልተቀደደና ያልተጫጫረ አሟልቶ ከቀረበ፤ | | 2.5 | |
| | ሐ. የመቀመጫ ወንበር ልብስ አዲስና ከጠንካራ ጨርቅ የተሠራ አዲስ ከሆነ፤ | | 1 | |
| | መ. የመቀመጫ ወንበር ልብስ ከጨርቅ የተሠራና አዲስም ባይሆን ያልተቀደደና ፅዳቱ የተጠበቀ ከሆነ፤ | | 0.5 | |
| 3.3 | የወንበሮች ምቹነት በተመለከተ፡- | | 3 | |
| | 3.3.1 ወንበሮች የእጅ መደገፊያ ያለውና ለተንዥም መቀመጫ የእጅ መያዣና ምቾት ያለው ከሆነ፤ | | 3 | |
| | 3.3.2 ወንበሮች ከተንዥም መቀመጫ ፊት ለፊት የእጅ መያዣ ያለውና ምቾት ያለው ከሆነ፤ | | 2 | |
| | 3.3.3 ወንበሮች የእጅ መያዣና መደገፊያ ባይኖረውም ለተገልጋዩ ምቾት ያለው ከሆነ፤ | | 1 | |
| 3.4 | **የአየር መቆጣጠሪያ** (AirConditioner Ventilator & Manual)፤ | | 3 | |

| ተ.ቁ | የመሥፈርት ዝርዝር | ልዩ ሁኔታ | የተሻሻለው ነጥብ ከ100 | ያገኘው ነጥብ |
|---|---|---|---|---|
| | 3.4.1 ለሁሉም ተንዥ መንገደኛ የሚያገለግል AC ያለው ከሆነ፣ | | 3 | |
| | 3.4.2 ደረጃውን የጠበቀ 2 ወይም 3 ቦታ ላይ የተዘጋጀ በኤሌክትሪክ የሚሰራ ፋን (Ventilator) ያለው ከሆነ፣ | | 2 | |
| | 3.4.3 በመኪናው የመሐል ጣሪያ በእጅ (Manual) የሚከፈት የአየር ማስገቢያ ያለው ከሆነ፣ | | 1 | |
| 3.5 | የእሳት አደጋ ማጥፊያ መጠኑ 2 ኪሎ ግራም የሚመዝን ስጉዞ የሚጠቀም ከሆነና ማረጋገጫ ካቀረበ፣ | | 2 | |
| 3.6 | የተሽከርካሪ ወለልን በተመለከተ:- | | 3 | |
| | 3.6.1 የተሽከርካሪው ወለል ሙሉ ለሙሉ የአልሙኒየም ሻካርድ የለበሰ ከሆነ፣ | | 3 | |
| | 3.6.2 የተሽከርካሪው ወለል ሙሉ ለሙሉ ባለሳንቲም ፕላስቲክ የለበሰ ከሆነ፣ | ለሁሉም የሥራ ደረጃዎች አስገዳጅ የሆነና ካልተሟላ ፈቃድ የማያሰጥ ነው ፣ | 2 | |
| 3.7 | የመጋረጃ ይዘትና ጥራት ሁኔታ፡- | | 5 | |
| | 3.7.1 ከፋብሪካ ሲወጣ የነበረውን መጋረጃ በጥሩ ሁኔታ ያሟላ ከሆነ፣ | | 5 | |
| | 3.7.2 ከሐር ጨርቅ የተዘጋጀ አዲስ መጋረጃ አሟልቶ ከቀረበ፣ | | 3 | |
| | 3.7.3 ከጥጥ ጨርቆች አይነት የተሰራና በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኝ መጋረጃ ያሟላ ከሆነ ፣ | ለሁሉም የሥራ ደረጃዎች አስገዳጅ የሆነና ካልተሟላ ፈቃድ የማያሰጥ ነው ፣ | 2 | |
| 4 | **ሌሎች** | | 3 | |
| | 4.1 ለመንገደኞች በጉዞ ወቅት ዜና እንዲሉ የሚያገዝ የDVD ወይም Tape አሟልቶ ከቀረበ፣ | ለደረጃ 1 እና 2 አስገዳጅ የሆነና ይህ ካልተሟላ ፈቃድ የማያሰጥ ነው ፣ | 3 | |

*ተሽከርካሪው ያገኘው አጠቃላይ ነጥብ ________________ ደረጃ _________*

***መገለጫ:*-***

ቀደም ሲል በመመሪያው ክፍል ሁለት አንቀጽ 3 (የኦፕሬተርነት ፈቃድ አይነቶችና የደረጃ መስፈርት) በሚል ርዕስ በንኡስ አንቀጽ 3.3 በተራ ቁጥር 3.3.3 (የደረጃ 1፣2 እና 3 ኦፕሬተርነት ደረጃ መስፈርት ማብራሪያዎች) የተቀመጠው መስፈርትና የነጥብ አሰጣጥ የተገለጸው በተጨማሪም አዲስ ሞተርና ካምቢዮ ገዝቶ ያስገጠመ ለዚህም አዲስ መሆኑንና ምንም አገልገሎት ያልሰጠ ስለመሆኑ ከአምራቹ ኩባንያ ማስረጃና፣ ቀረጥ ስለመከፈሉም ከጉምሩክ መረጃ ማቅረብ የሚችል ተሽከርካሪ በምዘና ካገኘው አጠቃላይ ውጤት ተጨማሪ የሚሆንለት 10 (አስር) ነጥብ እንዲያገኝ ይደረጋል። ይሁንና ካምቢዮ ብቻ ቀይሮ ከቀረበ የሚያገኘው ተጨማሪ ነጥብ አይኖርም። በዚህ የነጥብ አሰጣጥም ሞተርና ካምቢዮ ቀይሮ ለቀረበ ባለንብረት የተሰጠው ተጨማሪ ነጥብ ከፍተኛ ዕድሜ 10 (አስር) ዓመት ሆኖ በየዓመቱ 1(አንድ) ነጥብ በመቀነስ የተገጠመው አዲስ ሞተር ከ10 (አስር) ዓመት በኋላ ተመልሶ ዜሮ ይሆናል። የዚህ ዓላማ ዋነኛ ምክንያት የተሽከርካሪ ባለንብረቶች በተሽከርካሪዎቻቸው ላይ አገልግሎት ለመስጠት የሚያወጡትን ወጪ ታሣቢ በማድረግ ሚሰጡት አገልግሎት ለማበረታታት ነው።በሚል ተሻሽሏል።

## ***የሕዝብ ማመላለሻ አውቶብሶች የሥራ ደረጃ አሰጣጥ***

## ***<u>የምዘና ነጥብ መስጫ መሥፈርት የነጥብ ማጠቃለያ</u>***

***የነጥብ ማጠቃለያ***

| ተ.ቁ | መደበኛ ደረጃ | ማስፈያ ነጥብ ከመቶ % |
|---|---|---|
| 1. | አንድ | 80-100 |
| 2. | ሁለት | 65-79.99 |
| 3. | ሦስ-ት | 50-64.99 |

| ተ.ቁ | አይነት | ነጥብ |
|---|---|---|
| 1. | የተሽከርካሪ ሰድሚ | 30 |
| 2. | ደህንነት | 29 |
| 3. | ምቾት | 38 |
| 5. | ሌሎች | 3 |
| | ድምር | 100% |

## ***ክፍል አራት***

### 4. በልዩ፣ በመደበኛ ደረጃ 1፣ ደረጃ 2 እና ደረጃ 3 የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰማገኘት መሟላት የሚገባቸው ዋና ዋና ቅድመ-ሁኔታዎች

1. በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመሳሰሻ አገልግሎት ለመሠማራት የሚፈልጉ ግለሰቦችና ድርጅቶች የተሽከርካሪ ባለንብረቶች ወይም ሕጋዊ ወክልና ያላቸውና ሥራ አስኪያጆች ስሚመለከተው የፌዴራል ወይም የክልል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ወይም ቢሮዎች በዚህ መመሪያ መሠረት ማመልከቻ ማቅረብ ይኖርባቸዋል::

2. ተሽከርካሪው ዓመታዊ የቴክኒክ ደኅንነት ምርመራ ወይም ተመሳሳይ ምርመራ በሚገባ ያለፈ ስለመሆኑ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ፣ የባለቤትነት መታወቂያ ወይም ሊብሬ መቅረብ ይኖርበታል::

3. በግል በድርጅትና በኩባንያ ለሚሠሩና በመደበኛ የሕዝብ ትራንስፖርት ለሚደራጁ ማኅበራት የሚያስፈልግ የሠራተኞች የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃን በተመለከተ:-

- የትምህርት ደረጃ:-
  - የሥራ አስኪያጅ ዲግሪና ከዚያ በላይ፣
  - የኦንሬሽን ኃላፊ ዲኘሎማና ከዚያ በላይ፣
  - መረጃና ትራፊክ ደኅንነት ዲኘሎማና ከዚያ በላይ

    የሰው ኃይል ገንዘብና ንብረት አስተዳደር ቢያንስ ዲኘሎማ ያለው፣
  - በማኅበር ተደራጅተው ለሚሠሩ የማኅበሩ የቦርድ ሰብሳቢ 10ኛ ክፍል ያጠናቀቀ ቢቻል ከዚያ በላይ የሆነ

4. ስከትትል እንዲያመች ኦፕሬተሩ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ስማግኘት የቀጠረው አሽከርካሪ ቀደም ሲል አሽከርካሪው በትራፊክ አደጋ ያለውን ሪከርድ የሚያስረዳ የፖሊስ ማስረጃ ማያያዝ ይኖርበታል::

5. ኦፕሬተሩ ፈቃዱን በሚወስድበት የትራንስፖርት አገልግሎት ዓይነት ላይ እንዴት መሥራት እንደሚችል የሥራ መርሀ-ግብር አዘጋጅቶ ሞልቶ ያቀርባል::

6. የሥምሪት ፈቃድ ጥያቄ የቀረበባቸው የሥምሪት መሥመሮች በበቂ ተሽከርካሪ የተሸፈኑ ወይም ያልተሸፈነ ከሆነ የሥምሪት ሽፋንን ፍትሐዊነት ለማረጋገጥ ሲባል መርሀ-ግብሩ ላይ አስፈላጊ ማስተካከያ ወይም ለውጥ ቢደረግ የሚቀበል ነገር ግን የቀረበው የሥምሪት አሠራር መርሐ-ግብር ለውጥ ሲደረግበት በበቂ ምክንያት የተደገፈና በሥራ ሂደቱ ባለቤት የፀደቀ ይሆናል::

7. ኦፕሬተሩ በግል፣ በድርጅት ወይም በማኅበር እንዲሠራ ሲፈቀድለት የራሱ የሆነ መለያ ስምና ዓርማ አዘጋጅቶ ሥራ ላይ ማዋል አለበት፡፡ እንዲሁም በአደረጃጀቱ ውስጥ የሴፍቲ ዩኒት ማቋቋም አለበት፡፡

8. የዕቃ ማስጫኛና መለያ ታግ፣ የጉዞ ትኬትና ደረሰኞች ማዘጋጀትና በተገቢው ጥቅም ላይ ያውላል፡፡

9. አውቶብሱ በመመሪያው መሠረት ለደረጃው የተፈቀደውን ቀለም የተቀባ ንጽሕናው የተጠበቀ እና ሙሉ የመስታወት መጋረጃ ያለው ይሆናል፡፡

10. ለረዳት፣ ለአሽከርካሪ፣ ለገንዘብ ተቀባይ በዚህ መመሪያ በተገለጸው ዓይነትና ቀለም መሠረት ዩኒፎርም ያዘጋጃል ሥራ ላይ ያውላል፡፡

11. የመደበኛ ደረጃ 1,2,3 ለሚሰጡት የትራንስፖርት አገልግሎት መንግሥት በሚወስነው የክፍያ ታሪፍ መሠረት አገልግሎት ይሰጣል፡፡

12. ከመናኸሪያ ውጪ የቅድሚያ ትኬት አገልግሎት መስጫ ቢሮ እና በመናኸሪያ ውስጥ የሥምሪት መስጫ ቢሮዎች ማዘጋጀት አለበት፡፡

ከፍ ብሎ የተዘረዘሩት መሥፈርቶችና መሟላት የሚገባቸው ነጥቦች በየደረጃው በተቋቋሙ የፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ወይም በክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች የሥራ ኃላፊዎች እየተረጋገጡ ሥራ ላይ እንዲውሉ መደረግ አለበት፡፡



## ክፍል አምስት

## 5 የኦፕሬተሩ መብትና ግዴታዎች

በልዩ፣ በመደበኛ ደረጃ1፣ ደረጃ 2 እና ደረጃ 3 የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጡ የተፈቀደላቸው ኦፕሬተሮች ቀጥሎ የተዘረዘሩት መብትና ግዴታዎች አሏቸው፡፡

### 5.1. መብት

ሀ. አንድ ግለሰብ፣ ማኅበር ወይም ድርጅት በአዋጅ 468/97 እና በዚህ መመሪያ መሠረት መመዘኛዎችን አሟልቶ እስከተገኘ ድረስ የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የማግኘት፣

ለ. በተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድና የሥምሪት መሥመር መሠረት የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት የመስጠት፣

ሐ. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ወይም ከክልል ትራንስፖርት ባለሥልጣን (ቢሮዎች) ሙያዊ ድጋፍ የማግኘት ወጪን በተጋራ ሁኔታ የሥልጠና ዕድሎች ላይ የመሣተፍ፣

መ. የመናኸሪያ አገልግሎት የማግኘት፣

ሠ. ያቀረበውን የሥራ መርሀ-ግብር የማሻሻልና የመቀየር፣

ረ. ስለትራንስፖርትና ትራንስፖርት ነክ አገልግሎት መረጃ የማግኘት ናቸው፤

### 5.2. የሥምሪት አፈፃፀምና ግዴታዎች

ሀ. ማንኛውም ኦፕሬተር በተሰጠው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ መሠረት በተሽከርካሪዎቹ ላይ በሁለቱም ጎኖች መስመር እና የጎን ቁጥር እንዲሁም የተሽከርካሪውን ደረጃ የሚያሳይ በሁለቱም ጎኖች 20cmX60cm እና ከፊትና ከኋላ 20cmX30cm በሆነ በስቲከር እንዲለጠፍ ያደርጋል፡፡

ለ. የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ኮፒው ወይም ቅጅው አገልግሎት በሚሰጥበት በተሽከርካሪው ውስጥ ሊኖር ይገባል፣ በፌዴራልና የክልል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ወይም ቢሮዎች እንዲሁም አግባብነት ባላቸው የሕግ አስከባሪ ሲጠየቅም ፈቃዱን ያሳያል፡፡

ሐ. ኦፕሬተሩ ቀጥሮ ለሚያሠራቸው ሠራተኞች የሙያና የሥነ-ምግባር ሥልጠና መስጠት፣ ሕጋዊ መታወቂያ፣ የደረት ባጅ፣ ለአሽከርካሪዎች፣ ለረዳቶችና ለዕቃ

ጫኝና አውራጅ እንዲሁም ሌሎች ከምሥሪት ጋር አግባብነት ሳላቸው ሠራተኞች በዚህ መመሪያ ክፍል 5 አንቀጽ 5.4 ቁጥር 10 ላይ በተቀመጠው የቀለም ዓይነት መሠረት የደንብ ልብስ ወይም ዩኒፎርም አዘጋጅቶ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡ እንዲሁም በክፍል 5 አንቀጽ 5.3 መሠረት በየደረጃው የተመደቡ አውቶብሶች በቀለም የተለዩ ይሆናሉ፡፡

መ. ማንኛውም የሕዝብ ማመላለሻ ኦንሬተርነት ፈቃድ የወሰዱ ግለሰብ፣ ድርጅት ወይም ኩባንያ ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ ማንቀሣቀስ የሚችለው ከሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ከሚሰጥ ሕጋዊ መናኸሪያ ፈቃድ ሲይዝ ብቻ ነው፡፡

ሠ. ከመናኸሪያ የሚሰጥ የመውጫ ሰነድ ይዘት እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ የተለያዩ መሥፈርቶችን መያዝ የሚችል ሲሆን፣ ቢያንስ የተሽከርካሪው የመነሻና የመድረሻ ቦታ፣ የመነሻ ቀንና ሰዓት፣ የመጫን ችሎታ፣ ከፍያ ታሪፍ የአሽከርካሪው ስም እና የፈቃድ ሰጪ አካል ስም፣ ፊርማና ሕጋዊ ማኅተም ያካተተ ይሆናል፡፡ ይህም በህትመት መልክ ሲዘጋጅ ይችላል፡፡

ረ. ከላይ በ "ሠ" የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ፣ የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ለመስጠት የተደራጁ ኩባንያዎች (አክሲዮን እና ፒ.ኤል.ሲ) የራሳቸው የምሥሪት መውጫ ፈቃድ በማዘጋጀት አገልግሎት መስጠት ይችላሉ፡፡

ሰ. ማንኛውም አሽከርካሪ ወይም ረዳት ሥራውን ለመቀጠል ከመነሻ መናኸሪያ የተረከበውን የምሥሪት መውጫ ፈቃድ ለመድረሻ መናኸሪያ የኦፕሬሽን ሠራተኞች በማሳየት ስለቀጣይ እንቅስቃሴ መግለጫ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

ሸ. ማንኛውም የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ወደ ሕጋዊ መናኸሪያ በመግባት አገልግሎት መስጠት በማይችሉባቸው አስገዳጅ ጉዳዮች ወይም የኀብረተሰቡ ማኅበራዊ፣ ባሕላዊና የጉብኝት፣ የሠርቪስ ጉዞዎች ወዘተ... ከተለያዩ ሕጋዊ አካላት ማለት ዕድሮች፣ ክበባት፣ ቀበሌ አስተዳደር፣ ት/ቤት፣ የመንግሥት መ/ቤት፣ ሲቪክ ማኅበራት፣ ወዘተ... ሕጋዊ የድጋፍ ደብዳቤ ይዘው በመቅረብ ለመደበኛ ተሽከርካሪዎች የተቀመጠውን የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል የኮንትራት የምሥሪት መውጫ ፈቃድ በመውሰድመሰማራት ይገባቸዋል፡፡

ቀ. ማንኛውም የሕዝብ ማመላለሻ ባለንብረት የራሱን ተሽከርካሪ እንቅስቃሴ የሚያሳይ መርሐ ግብር ተዘጋጅቶ ለትራንስፖርት ባለሥልጣን ወይም ለክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች ከ15 ቀን በፊት በማሳወቅ ትራንስፖርት አገልግሎት

መስጠት ይችላል፡፡ የቀረበው ተሽከርካሪ መርሐ ግብር እንደየአመጣጡ ቅደም ተከተል እየተመዘገበ ይስተናገዳል፡፡

በ. የቀረበው የሥምሪት መርሀ-ግብር በኦፕሬተሩ የሚቀየር ከሆነ ይህንኑ ቢያንስ ከ15 ቀን በፊት ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ አለበት፡፡

ተ. ኦፕሬተሩ በተሽከርካሪው ላይ የተሣፈሪውን ዕቃ የሚጭንበት በቂ ቦታ/ፖርቶ መጋላ፣ ኪስ . . . ወዘተ/ማዘጋጀትና የመጫንና የማውረድ አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡ ሆኖም የሚጫነው ዕቃ በሕግ የተወሰነውን ከፍታ መጠበቅ ይኖርበታል፡፡

ቸ. ኦፕሬተሩ የተሰጠው ፈቃድ ለአንድ ዓመት የሚያገለግል ሲሆን፣ በየዓመቱ ማሳደስ አለበት የአፈፃፀም ሪፖርትም ያቀርባል፡፡

ኀ. በሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪው ላይ አደጋ ከደረሰ ኦፕሬተሩ ማኅበሩ፣ ድርጅቱ ወይም ግለሰቡ ወዲያውኑ ሥምሪት ከወሰደበት መናኸሪያና ለትራፊክ ፖሊስ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡ እንዲሁም የአደጋው መጠን ለመቀነስ በተዘጋጀው ፎርም የአደጋውን መጠንና ሁኔታ ለፈቃድ ሰጪው አካል በአንድ ሣምንት ጊዜ ውስጥ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ነ. በችግር ምክንያት ተሽከርካሪው ሥራ ላይ የማይውል ከሆነ አሽከርካሪው ወዲያውኑ ተለዋጭ ተሽከርካሪ እንዲቀርብ ለሚሠራበት ማኅበርና ድርጅት በግል የሚንቀሳቀስ ከሆነም ለባለንብረቱ ማሳወቅ አለበት ባለንብረቱም ተሽከርካሪው በአገልግሎት ላይ የሌለ መሆኑን ለመናኸሪያው አስተዳደር የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

ኘ. ኦፕሬተሮች ወይም ማኅበራት ለተገልጋዩ ቅርብ በሆኑ ቦታዎች ላይ ትኬት ኦፊስ በመክፈት የቅድመ ጉዞ ትኬት አገልግሎት መስጠት አለባቸው፡፡ ይህም በደረጃ መስፈርቱ መሠረት ተፈጻሚ ይደረጋል፡፡

አ. ማንኛውም ኦፕሬተር በዕቅዱ መሠረት ተሽከርካሪውን መናኸሪያ ውስጥ በተመደበለት ቦታ አቁሞ አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡

ከ. ተሽከርካሪውን ለመጫን መናኸሪያ ውስጥ ማቆየት የሚቻለው እንቅስቃሴ ባለባቸው በፌዴራል ወይም ክልል ከተሞች እስከ 45 ደቂቃ፣ በዞን ከተሞች እና በወረዳ ከተሞች እስከ 1 ሰዓት ድረስ ብቻ ነው፡፡ ሆኖም ተሽከርካሪው ከመነሻው ቢያንስ መጫን ከሚገባው 50% ተሣፋሪ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

ሠ. ተሽከርካሪውን መናኸሪያ ውስጥ ማጠብ፣ ጐማ መቀየር እና ነዳጅ መሙላተ ወዘተ . . . የተከለከለ ስለሆነ ይሄው ተግባራዊ ማድረግ አለበት:: ነገር ግን ድንገተኛ በሆነ አጋጣሚ ተሽከርካሪው መናኸሪያ ውስጥ እንደቆመ ጐማ ተንፍሶ ቢገኝ ጐማ ቀይር መውጣት ይችላል::

ሰ. ፈቃድ የተሰጠው ግለሰብ፣ ማኅበር ወይም የትራንስፖርት ድርጅት የመናኸሪያ አገልግሎት መጠቀም የሚችለው በተፈቀደለት የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ መናኸሪያ ውስጥ ብቻ ሲሆን፣ አስቀድሞ በፀደቀው የሥምሪት መርሀ-ግብር መሠረት ተግባራዊ ያደርጋል::

ዘ. መናኸሪያው የሚያስተናግደው አቅም መሠረት ተሽከርካሪዎቹን እንደ ሥምሪት ቅደም ተከተላቸው መናኸሪያ ውስጥ በማስገባት አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋል::

ዠ. ማንኛውም ኦፕሬተር የተሽከርካሪውን ቀስም በመመሪያው በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ አስተካክሎ ማቅረብ ይኖርበታል::

የ. ማንኛውም ግለሰብ፣ ማኅበር፣ የትራንስፖርት ድርጅት ከተፈቀደለት የተሽከርካሪ ዝርዝርና ብዛት ውጭ ተባባሪ በሚል ሌሎች ተሽከርካሪዎችን በጊዜያዊነትም ሆነ በቋሚነት ማሠማራት የለበትም::

ደ. ማንኛውም ኦፕሬተር ተሣፋሪዎች በወንበር ቁጥር እንዲቀመጡ፣ በቂ መረጃ እንዲያገኙ ዕቃቸው ታግ ታስሮበት እንዲጫን የማድረግ ኃላፊነት የሚወጡ ብቁ ሠራተኞችን ማዘጋጀት አለበት::

ጀ. ኦፕሬተሩ የተሣፋሪዎቹ ጓዝ መጫኑን ካረጋገጠ በኋላ ተገልጋዮችን ወደ ተሽከርካሪው እንዲገቡና በያዙት ትኬት ቁጥር ቅደም ተከተል በወንበር ቁጥራቸው እንዲቀመጡ ያስታውቃል:: በዚህ አሠራር ሂደት ተፈፃሚ መደረግ ይኖርበታል:: አጠቃላይ ሂደቱ ከ60 ደቂቃ በላይ መውሰድ የለበትም::

## <u>የተሽከርካሪ ቀለም ዓይነቶች</u>

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. | ልዩ | - | መደቡ ቀይ በነጭ ስትራይኘ (Stripe) |
| ለ. | ደረጃ አንድ | - | መደቡ ነጭ ከወገብ በላይ አረንጓዴ |
| ሐ. | ደረጃ ሁለት | - | መደቡ ነጭ ከወገብ በላይ ሰማያዊ |
| መ. | ደረጃ ሦስት | - | መደቡ ነጭ ከወገብ በላይ ቢጫ |

- የልዩ ደረጃ ባለቸው አውቶብሶች ላይ የሚደረገው የአንድ ስትራይፓ ስፋት መጠን በአማካኝ 15 ሳ.ሜ ስፋት ያለው ይሆናል።

- ለእየንዳንዱ አውቶብስ የተሰጠው ደረጃ በአውቶብሱ ጉንና ጉን እንዲሁም ፊትና ኋላ ላይ በጉልህ መጻፍ ይኖርበታል።

- እያንዳንዱ የተሽከርካሪ የቀለም ቅብ ለደረጃዎች የተሰጠው የቀለም ዓይነት እንደተጠበቀ ሆኖ የዕቃ መጫኛው የላይኛው ክፍል በሚፈልጉት ዓይነት ቀለም ማስቀባት ይችላሉ።

## 5.3 የደንብ ልብስ (ዩኒፎርም)

5.3.1 ለልዩ - ለሹፌር ሙሉ ጥቁር ሰማያዊ ኮትና ሱሪ ከውሃ ሰማያዊ ሸሚዝ ጋር በከራቫት፣

5.3.2 ለደረጃ አንድ - ጥቁር ቡኒ ጃኬትና ሱሪ በውሃ ሰማያዊ ሸሚዝ ኬኘና ከራቫትጋር፣

5.3.3 ለደረጃ ሁለት-ቀለሙ ወኃ ሰማያዊ ጃኬት፣ ሱሪ ሸሚዝና ኬኘ ከሰማያዊ ከራቫት ጋር፣

5.3.4 ለደረጃ ሦስት ቀለሙ አረንጓዴ የሆነ ጃኬትና ሱሪ ከ ውሃ ሰማያዊ ሸሚዝ ጋር በአረንጓዴ ክረቫት ሲሆን፣ ከደረጃ 1-3 ለሹፌር ሙሉ ዩኒፎርም ለገንዘብ ተቀባይ ጋዋን ለረዳት ቱታ ነው፣ ኬኘ ለሁሉም ሠራተኞች መሟላት አለበት፡፡

## 5.4 የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሥምሪት ዓይነትና አፈፃፀም

ብቃታቸው ተረጋግጦ የሕዝብ ማመሳለሻ አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች ከዚህ በታች በተገለፀው የሥምሪት ዓይነት መሠረት አገልግሎት ይሠጣሉ፡፡

ሀ. በመርሀ-ግብር በታገዘ የነፃ ሥምሪት፣

ለ. በፍራንቻይዚንግ ወይም የጨረታ ውድድር ላይ በተመሠረተ አሠራር ይሆናል፣

ሐ. በነፃ ሥምሪት ወይም በጨረታ አግባብ የማይሸፈኑ የሥምሪት መሥመሮች ሲያጋጥም የፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ወይም የክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች በእጣ፣ በረሾ /Ratio/ ወይም ሌሎች አመቺ የሆኑ አሠራሮችን በመጠቀም ያልተሸፈኑ መስመሮች እንዲሸፈኑና ተገልጋዩ ሕዝብ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲያገኝ ያደርጋሉ፡፡

መ. እያንዳንዱ ኦፕሬተር/ግለሰብ፣ የትራንስፖርት ማህበራትና ድርጅቶች በዚህ አንቀጽ 5.5. ፊደል ሐ መሠረት የአውቶብስ ሥምሪት ያላገኙ መስመሮችን እንዲሸፍኑ ሲጠየቁ አውቶብስ በማቅረብ በመስመሮቹ የሕዝብ ማጓጓዝ አገልግሎት መስጠት አለባቸው፡፡

# ***ክፍል ስድስት***

## 6. በአገልግሎት አሰጣጥ የሚያስጠይቁ የሥነ-ሥርዓትና የሥነ-ምግባር ጉድለቶች

### 6.1. ፈቃድና ተጓዳኝ ጉዳዮችን በተመለከተ

ሀ. ማንኛውም ግለሰብ፣ ድርጅት ወይም ማኅበር በዚህ መመሪያ መሠረት የሕዝብ የመንገድ ትራንስፖርት የብቃት ማረጋገጫ ሳይኖረው የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ከሰጠ፣

ለ. ማንኛውም ኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫውን ወቅቱን ጠብቆ ካላሳደሰ፣

ሐ. ከዚህ መመሪያ ውጭ የብቃት ማረጋገጫ ይዞ ወይም የተጭበረበረ መረጃ ይዞ ከተገኘ፣

መ. ማንኛውም የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ማኅበር፣ ድርጅት ወይም ግለሰብ ፈቃዱን ለዕይታ በሚያመች መልኩ አስቀምጦ አስመገኘት፣ በፌዴራል ወይም ክልል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ወይም ቢሮዎች ወይም አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅም ለማሳየት ፈቃደኛ ካልሆነ፣

ሠ. ማንኛውም ኦፕሬተር ፈቃድ በተሰጠበት ወቅት ተሟልተዋል በሚል ያሳያቸው መመዘኛዎች በቁጥጥር ወቅት ተሟልተው ካልተገኙ፣

ረ. የስብሰባ ጥሪ ተደርጎለት ወይም እንዲደርሰው ተደርጎ ያለበቂ ምክንያት ካልተገኘ፣

ሰ. እንደፈቃዳቸው ደረጃና ዓይነት ለሕዝብ ጥቅም ሲባልና በመንግሥት ውሣኔ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ተመድበው አገልግሎት እንዲሰጡ ሲጠየቅ ተባባሪ ሆኖ ካልተገኘ፤

### 6.2. የቢሮና የሰው ኃይል አደረጃጀት በሚመለከት

ሀ. ፈቃድ የወሰደው የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ሰጪ ማኅበር፣ ድርጅት ወይም ግለሰብ በዚህ መመሪያና በሞዴል መተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የቢሮና የሰው ኃይል አደረጃጀቱን አሟልቶ አስመገኘት፣ አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅም መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ያለመሆን መረጃዎችን ያለማሳየት፣

ለ. ማንኛውም ኦፕሬተር በዚህ መመሪያ መሠረት ፈቃዱን ሲወስድ ከነበረው የቢሮ አደረጃጀት አንዳንድ ነገሮችን በመቀነስ ካለ ፈቃድ ደረጃውን ዝቅ እንዲል አድርጎ መገኘት፣

ሐ. በሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ እንዳይሠሩ የታገዱ ሠራተኞች ቀጥር ማሠራት፤

## 6.3. ሥምሪትና ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራት በሚመለከት

የሕዝብ ማመሳለሻ አገልግሎት ሰጪ ማኅበራት፣ ድርጅት ወይም ግለሰብ ከዚህ በታች የተመለከቱትን አገልግሎቶች አሟልቶ ተግባራዊ ለማድረግ፣

ሀ. የማኅበሩን ወይም የድርጅቱን ዓርማና ማንተም ሙሉ አድራሻ (ስልክና ፖስታ ወዘተ...) የያዘ ትኬቶች፣ ደረሰኞችና ታጎች አስማዘጋጀትና አስመጠቀም፣

ለ. ማኅበሩ፣ ድርጅቱ ወይም ግለሰቡ ቀጥር ለሚያሠራቸው ሠራተኞች፣ ሹፌሮች፣ ዕቃ ጫኝና አውራጅ፣ ገንዘብ ተቀባዮችና ረዳቶች በዚህ መመሪያ መሠረት ልዩ መታወቂያ፣ የደንብ ልብስ፣ ዓርማና ባጅ አስማዘጋጀትና እንዲጠቀሙ አስማድረግ፣

ሐ. በተሽከርካሪው ወይም አውቶቡሱ ላይ በዚህ መመሪያ በተሰጠው ደረጃ መሠረት ተሟልተው መገኘት ያለባቸው ፋሲሊቲዎችን አስማሟላት፣

መ. በፈቃዱ መሠረት ተሽከርካሪውን ለሥምሪት ዝግጁ አስማድረግ፣ ለጉዞ ከመሠማራቱም በፊት ደህንነ አስማረጋገጥ፣

ሠ. ተጓዥ ይዞት የሚጓዘውን ዕቃ በሕጉ መሠረት እንዲጫን አስማድረግ፣

ረ. በጉዞ ላይ የሚረሱ ወይም ጠፍተው የተገኙ ዕቃዎችን በአግባቡ እንዲያዙ አስማድረግና ለባለቤቱ በአግባቡ እንዲመለሱ አስማድረግ፣

### ሰ. የመንገደኞች ትኬት ሂሣብ አመሳለስ ሥርዓት

1. በፌዴራልም ሆነ በክልል አንድ ተጓዥ በተለያዩ ተጨባጭ ምክንያት ጉዞውን ከመጀመሩ በፊት ቢያንስ ከ1 ሰዓት በፊት ጉዞውን ቢሰርዝ (ሙሉ ገንዘቡን አስመመለስ)፣
2. ተሣፋሪውን ለምሣና ለቁርስ አውርዶ ጥሎ ከሄደ የተጓዘበት ኪሎ ሜትር ተቀንሶ ቀሪ ሂሣቡን አስመመለስ፣
3. አውቶብሶች የመናኸሪያ መውጫ ሰዓት ሳይደርስ መንገደኛውን ጥሎ ከሄደ ሙሉ የጉዞውን ዋጋ አስመመለስ::
4. ማኅበራት ወይም ባለንብረቶች ሕጉን መሠረት ባደረገ መልኩ ማሳሰቢያ በትኬቱ ጀርባ ላይ አስመፃፍ::

5. የተሽከርካሪዎችን የጉን ቀጥር በማቀያየርና በሌሎች መንገደኛው ከመረጃ እጦት የተነሳ አውቶብስ ቢያመልጠው ሙሉ ክፍያ አስመመለስ::

6. መንገደኛዉ በራሱ ችልተኝነተ ከጉዞው ከቀረ 10% ተቀናሽ ተደርጎ ይመለስለታል:: ሆኖም ጥፋቱ በአውቶብሱ ሠራተኞች ሳይ እንዲጠጡ ወይም ሰዓት አልደረሰም በሚል ቅስቀሳ ተደርጎ ከሆነ 10% ተቀናሽ ተፈፃሚ አይሆንም::

7. ከሦስት ቀናት በላይ ቀደተ ጥያቄ ለሚያቀርብ መንገደኛ 20% ተቀናሽ ተደርጎ ክፍያ ተመላሽ አስማደረግ::

ሽ. በተሰጠው ፈቃድ መሠረት ለተገልጋዩ በሚቀርቡ ቦታዎች የትኬት ቢሮ እንዲኖር በማድረግ ተገልጋዩ ሳይንገላታ ቀደም ብሎ ከደላላ የፀዳ የትኬት አገልግሎት እንዲያገኝ አስማድረግ፣

## 6.4. የመረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀትና ሥርጭት በሚመለከት

ሀ. በዚህ መመሪያ አባሪ የተደረጉና ሌሎች በፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ወይም በክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች የተዘጋጀ የመረጃ ማሰባሰቢያ ቅፃችና ፎርማቶችን አባዝቶ በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውሉ አስማድረግ፣

ለ. በተዘጋጁ ቅፃች መሠረት የሚሰበሰቡ መረጃዎች በአግባቡና ወቅቱን ጠብቆ ለሚመለከተው አካል አስማስተላለፍ፣

ሐ. ማንኛውም ማኅበር፣ ድርጅት ወይም ግለሰብ ወቅታዊና አጣዳፊ የሥራ ሪፖርቶችን በጊዜው ለፌዴራል ወይም ለክልል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ወይም ቢሮዎች አስማስተላለፍ፤

መ. በመናኸሪያ የመነሻና መድረሻ ቦታ በአገልግሎት ሂደትና በጉዞ ሳይ ለተሣፋሪዎች በቂ መረጃ አስመስጠት፣

## 6.5. <u>የተሽከርካሪውን ባለንብረት በሚመለከት</u>

ሀ. በምርት ሂደት ተሽከርካሪው በደረጃው ባገኘው መመዘኛ ነጥብ መሠረት አሟልቶ አገልግሎት አለመስጠት፣

ለ. ተሽከርካሪው ከተፈቀደለት የአገልግሎት ዓይነት ውጭ እንዲሠማራ በማድረግ የምርት አፈፃፀሙን ማዛባት፣

ሐ. ለአገልግሎት የቀጠራቸው ሠራተኞች (አሽከርካሪ፣ረዳት፣ ገንዘብ ተቀባይ) በዚህ መመሪያ የወጣውን መመዘኛ ያሳሟሉ ሆኖ መገኘት፣

መ. በሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ እንዳይሠማራ የታገደ አሽከርካሪ፣ ገንዘብ ተቀባይ፣ የአሽከርካሪ ረዳት ቀጥሮ ማሠራት፤

ሠ. በአውቶብሱ ላይ ተመድበው ለሚሠሩ ሠራተኞች የትራንስፖርት ሕግና ደንብ ጥሰት ምክንያት ሆኖ መገኘት ፣

## 6.6. <u>አሽከርካሪውን ወይም ሹፌሩን በሚመለከት</u>

ሀ. ተገቢውን የጉዞ ሠነድ እንደ ሕጋዊ መንጃ ፈቃድና የመሣሠሉት ሰነዶችን አሟልቶ አለመያዝ ወይም የተጭበረበረ የሕዝብ ማመላለሻ የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም መንጃ ፈቃድ ይዞ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ማሽከርከር፣

ለ. በዚህ መመሪያ ባለው የቅጣት ሪከርድ መሠረት የሕዝብ ትራንስፖርት ተሽከርካሪን ለመንዳት ለፈፀመው ጥፋት የተወሰነበትን ቅጣት በቅድሚያ መክፈል ወይም ተሽከርካሪ እንዳይነዳ ታግዶ እያለ መኪና ሲያሽከረክር መገኘት፣

ሐ. በማንኛውም የሕዝብ የመንገድ ማመላለሻ አገልግሎት በመስጠት ላይ እያለ በዚህ መመሪያ በተቀመጠው መሠረት የደንብ ልብሱን በአግባቡ ለብሶ አለመገኘት፣

መ. በሥራ ላይ እያለ አግባብ ባላቸው የክትትል፣ የድጋፍና ቁጥጥር ሠራተኞች ወይም ሌሎች ሕጋዊ አካላት ማንኛውም ዓይነት መረጃ ሲጠየቅ ለማሳየት ፈቃደኛ አለመሆን፣

ሠ. በጉዞ ላይ እያለ አልኮል መጠጥ መጠጣት፣ ጫት መቃምና አደንዛዥ እፆችን መጠቀም ወይም ሲጠቀም በተጨባጭ መገኘት፣

ረ. በዚህ መመሪያ መሠረት ከተሰጠው ፈቃድ ውጭ ወይም በደረጃ ተለይቶ ለአንድ አገልግሎት ብቻ ፈቃድ ተሰጥቶት በሌላ አገልግሎት ላይ ተሠማርቶ መገኘት፣

ሰ. ተገልጋዩ ኅብረተሰብ ንዙን (ዕቃውን) በአውቶቡስ ውስጥ ረስቶት ሲሄድ ለሚሠራበት ማኅበር፣ ድርጅት ወይም ግለሰብ ጽ/ቤት በወቅቱ አስማስረከብ፣

ሸ. በጉዞ ኘሮግራም መሠረት የሥምሪት እንቅስቃሴ በአግባቡ ተግባራዊ አስማድረግ፣

ቀ. በመናኸሪያ ውስጥም ሆነ በጉዞ ላይ ተሣፋሪውን ማንገላታት፣ ማንጓጠጥ ወይም የመጉተት ተግባር መፈፀም፤

በ. ስተሣፋሪው መረጃ አስመስጠት ወይም እንዲሰጥ አስማድረግ ከመንግስት የትራንስፖርት ታሪፍ በላይ ተሣፋሪውን በማስከፈል ሂደት ተባባሪ ሆኖ መገኘት፣ ተሣፋሪው ከመነሻው በወንበር ቁጥር መቀመጡን አረጋግጦ ጉዞ ያስመጀመር፣

## 6.7. ገንዘብ ተቀባይ

ሀ. ጉዞ ከመጀመሩና በጉዞ ላይ እያስ አስፈላጊ የሆኑ ትኬቶች፣ ደረሰኞችንና ዕቃ ማስጫኛ ታጎችን በበቂ ሁኔታ አስመያዝና በአግባቡ አስመጠቀም፣

ለ. በተሣፋሪም ይሁን በተቀጣጣሪ አካላት መረጃ ሲጠየቅ ተገቢውን መረጃ ስመስጠት ፈቃደኛ አስመሆን፣

ሐ. ከመነሻ - መድረሻ ያሰው ርቀት ቢያንስ ከ50 ኪ.ሜ በላይ በሆነ የጉዞ ትኬት በወንበር ቁጥር በቅደም ተከተል አስመቁረጥ፣ በወንበር ልክ ተሣፋሪዎች እንዲቀመጡ አስማድረግ፣ እንዲሁም በጉዞ ትኬቶች ላይ የተሣፋሪውን ወይም የተጓዡን ስም ያስመፃፍ፣

መ. ከሴሎች የሥራ ባልደረቦች ጋር በመሆን ስተሣፋሪዎች ተገቢውን እንክብካቤ አስማድረግ፣

ሠ. መናኸሪያ ውስጥም ይሁን ውጭ ተሣፋሪውን መጉተት ማንገላታት መዝለፍና ማንጓጠጥ፣

ረ. ተሽከርካሪው ሳይቆም ተሣፋሪውን ለአደጋ በሚያጋልጥ ሁኔታ በር መክፈትና እንዲወርድ ማድረግ፣

ሰ. ተሽከርካሪው የሚሰራበትን ማኅበር ወይም ድርጅትና ግለሰብ ሕጋዊ መታወቂያ እና የደንብ ልብስ ባጅ በአግባቡ አስመጠቀም፣ አስመያዝ፣

ሸ. ተሣፋሪው ስከፈስው የትራንስፖርት ዋጋ ደረሰኝ አስመስጠት፣

ቀ. ዕቃ ላይ ታግ አስማሠር፣

በ. የጉዞ አቅጣጫ ለተሣፋሪ አለመንገርና በጉዞ ወቅት የማረፊያ፣ የመመገቢያና የማደሪያ ቦታዎችን አስቀድሞ ወይም ከጉዞ በፊት አለመግለጽ፣

ተ. የመደበኛ ጉዞም ሆነ የኳንትራታዊ ጉዞዎች አስፈላጊ ሰነዶችን ሳያሟላ በተጭበረበረ መታወቂያ፣ ባጅና ከሥራው ጋር አግባብ በሌላቸው ባልተፈቀዱ የመውጫና ሌሎች ሠነዶች መጠቀም ወይም ለማጭበርበር መሞከር፣

ቸ. በዚህ መመሪያ መሠረት ባለው የቅጣት ሪከርድ ምክንያት ታግዶ እያለ አገልግሎት ሲሰጥ ከተገኘ፣

ኀ. ተቀጣጣይነት ያላቸው ለተሣፋሪ ምቾት የማይሰጡ እንደበርበሬ፣ እንስሣት. . በተሽከርካሪው ውስጥ እንዲጫኑና እንዲጓጓዙ መፍቀድ፣

ነ. የመናኸሪያ አገልግሎት ሳይከፍል መገኘት፤

ኘ. ከተወሰነው ታሪፍ በላይ ተሣፋሪውን አስከፍሎ መገኘት::

አ. ከሕጋዊ መናኸሪያ ውጪ ተሣፋሪ ማሰባሰብና ማሣፈር፣

## 6.8. የአሽከርካሪ ረዳት

ሀ. በሥራ ላይ እያለ በዚህ መመሪያ መሠረት የተወሰነውን የተሟላ የደንብ ልብስ አለመልበስ፣

ለ. ተሽከርካሪው የሚሠራበትን ማኀበር ወይም ድርጅትና ግለሰብ ሕጋዊ መታወቂያና ባጅ በአግባቡ ካልተጠቀመ ወይም ሥራ ላይ ካላዋለ፣

ሐ. የተጭበረበረ መታወቂያ፣ ባጅና ከሥራ ጋር አግባብ በሌላቸው ሠነዶች መጠቀም ወይም ለማጭበርበር ሲሞክር ከተገኘ፣

መ. በዚህ መመሪያ መሠረት ባለው የቅጣት ሪከርድ ምክንያት ታግዶ እያለ አገልግሎት ሲሰጥ ከተገኘ፣

ሠ. በተሣፋሪም ይሁን በተቆጣጣሪ ወይም ሌሎች አግባብነት ባላቸው አካላት መረጃ ሲጠየቅ ለመስጠት ፈቃደኛ ሳይሆን ከቀረ፣

ረ. ከሌሎች የሥራ ባልደረቦች ጋር በመሆን ለተሣፋሪዎች ተገቢውን እንክብካቤ ካላደረገ፣

ሰ. መናኸሪያ ውስጥም ይሁን ውጭ ተሣፋሪውን የመገተት፣ ማንገላታት፣ የመዝለፍና ማንጓጠጥ ተግባር ፈጽሞ ከተገኘ፣

ሸ. ተሽከርካሪው ሳይቆም ተሣፋሪውን ለአደጋ በሚያጋልጥ ሁኔታ በር ከከፈተና እንዲወርዱ ካደረገ፣

ቀ. የተሽከርካሪውን ንጽሕና አለመጠበቅ፣

በ. የተሽከርካሪውን የቴክኒክ ብቃትና ለጉዞ ዝግጁነት እየተከታተለ ማረጋገጥና ችግር ካለም ማሳወቅ ሲገባው ይህንን አለመፈፀም፤

ተ. ረዳቱ እንደገንዘብ ተቀባይ ሆና የሚሠራ ከሆነም በክፍል 6 አንቀጽ 6.7. መሠረት ለገንዘብ ያዥ የተከለከሉ ተግባራትን መፈጸም የለበትም።

## *ክፍል ሰባት*

## 7. ፍራንቻይዚንግ (በጨረታ አግባብ መሥመርችን ማስሸፈን)

### 7.1 ለፍራንቻይዚንግ ተፈላጊ መመዘኛዎች (Requirements)

አንዳንድ የሥምሪት መሥመርች በማይሸፈኑበት ጊዜ በጥናት በመደገፍ በፍራንቻይዚንግ እንዲሸፈኑ መደረግ ይኖርበታል። አፈፃፀሙም በፌዴራል ደረጃ ከሆነ በፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን በክልሎች ውስጥ ለሚደረግ  የሥምሪት እንቅስቃሴ ደግሞ በክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች ተግባራዊ ይደረጋል። ለውድድር አሠራር የተዘረዘሩት መመዘኛዎች ተዘጋጅተዋል።

ሀ. ማንኛውም አመልካች በመሥፈርቱ መሠረት ብቃታቸው ተረጋግጦ ደረጃቸው የታወቀ ተሽከርካሪዎች ያሉትና የትራንስፖርት ኦኘሬተርነት ፈቃድ ያለውና በፌዴራል ወይም የክልል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ወይም ትራንስፖርት ቢሮዎች የተመዘገበ፣

ለ. በተዘጋጀው ዝርዝር መሥፈርት መሠረት በዘርፉ የሚፈለጉ ግዴታዎችን ለመወጣት ፈቃደኛ የሆነ፣

ሐ. በቂ የካፒታል መጠን ያለው፣

መ. የዓመቱን የመንግሥት ግብርና ሌሎች ክፍያዎች ያጠናቀቀና የንግድ ፈቃዱ የታደሰበት፣

ሠ. የሠለጠኑ ሠራተኞች (አሽከርካሪ፣ ረዳት፣ የሥምሪት ሠራተኞች . . .) ያሉት ዝርዝር ያያይዛል፣

ረ. የአጠቃላይ መድንን ዋስትና ማስረጃ የሚያቀርብ፣

ሰ. የሚሠራበትን ታሪፍ የሚያቀርብ፣

ሸ. የተሽከርካሪዎች ቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ፣ ዋና ዋናዎች ሲሆኑ፣ አገልግሎቱ በሚሰጥበት ወቅት የአገልግሎት ጥራት ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ የሚያስችል፡

- በመሥመሩ ለማሠማራት የታሰበ ተሽከርካሪ ብዛትና የመጫን አቅም ግልጽ በሆነ መንገድ ማቅረብ፣
- ሠራተኞችን የመከታተያና የመቆጣጠሪያ የሥራ ኘሮግራም፣
- የተገልጋዩን ሕዝብ አስተያየት ለማሰባሰብና የአገልግሎት አሰጣጡን ብቃት ለመወሰን የሚያስችሉ ሥልቶች (የህዝብ መስጫ ሣጥኖች፣ የመረጃ መሰብሰቢያና ማሠራጫ ሥልቶች)፣

- የሾፌርች፣ የገንዘብ ተቀባይና ረዳቶች የተሟላ ዩኒፎርም እና ባጅ፣
- የቢሮ አደረጃጀትና አጠቃቀም ሥርዓት ዝርዝር መረጃ፣
- የተሽከርካሪ ጥገናና የፅዳት አጠባበቅ ናቸው

ከላይ የተዘረዘሩትን ለመነሻ የተዘጋጁ መሥፈርቶች መሠረት በማድረግ አጠቃላይ የብቃት ደረጃ ግምገማ ተደርጐ በፍራንቻይዚንግ (በጨረታ አገባብ) ሥምሪት መሥመሮችን ማስሸፈን ያስፈልጋል።

# ክፍል ስምንት

## 8. ልዩ ልዩ

### 8.1. ስለ ፈቃድ አሰጣጥ

8.1.1 በአዋጅ ቁጥር 468/97 ክፍል ሁለት አንቀጽ 2/ሰ መሠረት የሚቀርብ የሙያ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ምሥክር ወረቀትም ሆነ የመደራጀት ጥያቄ ሁለትና ከሁለት ክልሎች በላይ የሚካሄድ አገልግሎት ከሆነ በፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን የሚሰጥ ይሆናል። ሆኖም ግን የመጫን አቅማቸው 46 እና ከዚያ በታች የመጫን አቅም ያላቸው በአብዛኛው አገልግሎት በሚሰጡበት የክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች እንዲመዘገቡ የሚደረግ ሲሆን፣ 46 እና ከዚያ በላይ የመጫን አቅም ያላቸው ደግሞ በፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ይመዘገባሉ።

8.2. አሽከርካሪውን ሳይጨምር የመቀመጫ ልካቸው ከ11 እስከ 23 ሰው የሆኑ ሚኒባሶች የሥምሪት ፈቃድ የሚሰጣቸውና ፈቃድ ካወጡበት ቦታ እስከ 150 ኪ.ሜ ርቀት ብቻ ነው።

### 8.3. ስለውድድር

8.3.1. በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ አገልግሎት ሥራ ውድድር የሚካሄደው በደረጃዎች መካከል እና በመጫን አቅም መሠረት ነው ይኸውም:-

በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ አገልግሎት ሥራ ውድድር የሚካሄደው በደረጃዎች መካከል እና በመጫን አቅም መሠረት ነው ይኸውም:-

- ➢ አነስተኛ ደረጃ 1፣2 እና 3 ከ11-23 መቀመጫ 150 ኪሎ ሜትር ርቀት፣
- ➢ መለስተኛ ደረጃ 1፣2 እና 3 ከ24-44 መቀመጫ 250 ኪሎ ሜትር ርቀት፣
- ➢ ከፍተኛ ደረጃ 1፣2 እና 3 ከ46-62 መቀመጫ ሁለትና ከሁለት ክልሎች በላይ የሚጓዙ ከሆነ ደግሞ በደረጃቸው መሠረት ይወዳደራሉ፡፡ተመሳሳይ ደረጃ ያላቸው ከሆነ ግን በቅድም ተከተል እንደአመዘጋገባቸው ይስተናገዳሉ፡፡

በመመሪያው በተቀመጠው የተሽከርካሪዎቹ የጉዞ ርቀት መጠን መሰረት የጉዞ ሥምሪት በማድረግ ከመናኻሪያ ተነሽ የሆነ መኪና ወደ ጉዞ መድረሻ ጣቢያው ሲጓዝ የተፈቀደለት የጉዞ ርቀት ከመድረሻው ቦታ (የአገልግሎት መስጫ መነኻሪያ) ሳይደርስ የሚያበቃ ከሆነ ተሽከርካሪው ፊት ለፊቱ ካለው መነኻሪያ ደርሶ የያዛቸውን መንገደኞች ማውረድ እንዲችል እስከ መናኻሪያው ደረስ ያለውን ርቀት እንዲገለገልበት ይደረጋል፣ ሁሉም አካላትም ድጋፍ ይሰጣሉ፣

8.3.2. በኦፕሬተሮች መካከል የሚደረግ ማንኛውም ውድድር የትራንስፖርት ሕግና ደንብን በጠበቀ አግባብ መፈፀም ይኖርበታል፡፡ ውድድሩም በአገልግሎት ጥራት፣ በዋጋና በሌሎች ተሣፋሪውን በሚስቡ ተግባራት የታገዘ እንዲሆን በዘርፉ የተሠማሩ ሁሉ ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡

## 8.4. የተሣፋሪዎች መብት

8.4.1 ማንኛውም 7 ዓመት ያልሞላው ሕፃን በነፃ የመጓዝ፣ ከ7-12 ዓመት ከሆነ ደግሞ ግማሽ ዋጋ ከፍሎ ከሞግዚቶቹ ጋር በመቀመጥ መጓዝ አለበት፣

8.4.2 እስከ 25 ኪ.ግ ሰራሱ ጠቀሚታ የሚውል ዕቃ (ቅያሪ ልብስ፣ ለስንቅ የሚሆኑ ምግቦች፣ ለቤተሰብ የስጦታና የፍጆታ ዕቃዎች፣ ሌሎችም ለንግድ የማይውሉ ዕቃዎች) በነፃ የማጓጓዝ፣

8.4.3 ለከፈለው ገንዘብ ደረሰኝ የማግኘት፣

8.4.4 በዕኩል የመጓዝና ያስጫነውን ዕቃ በትክክል የመረከብ መብት አለው፤

## 8.5. ክክልል ክልልና በፌዴራል መናኸሪያዎች ስለመገልገል

8.5.1 ክክልል ክልልም ሆነ በፌዴራል ደረጃ ከመነሻ ሕጋዊ ሥምሪት ተሰጥቷቸው የተሠማሩ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች በየትኛውም ክልል ወይም የፌዴራል መናኸሪያ በሕጋዊ አግባብ ተቀባይነት ኖሯቸው መገልገል ይችላሉ:: ሆኖም በክልል ደረጃም ሆነ በፌዴራል የሚሰጥ ሥምሪት መሥመር ፈቃድንና የሥምሪት አገልግሎት ደረጃዎችን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት::

8.5.2 ማንኛውም ኦፕሬተር በመርሀ-ግብር የተመራ ሕጋዊ የሥምሪት አሠራርን የተከተለ ሆኖ እስከተንቀሳቀሰ ድረስ በየትኛውም የትራንስፖርት አካል ድጋፍና ዕገዛ ይደረግለታል::

## 8.6. የመናኸሪያ አጠቃቀም

- በመናኸሪያ አስተዳደርና የባለቤትነት ሁኔታ መመሪያ ላይ የተዘረዘሩት አሠራሮች እንደተጠበቁ ሆኖ በሥምሪት ሂደት መንገደኞችን ወይም ተጓዦችን በመሣፈርና ከአውቶቡስ በመውረድ ሂደት ውስጥ ተሣፋሪው በተፈቀደለት የመናኸሪያ መግቢያ እንዲገባና የመውጫ በርችን ተጠቅሞ እንዲወጣ ይደረጋል፣
- ማንኛውም ተገልጋይ፣ ተሣፋሪ ከመናኸሪያ የመረጃ መስጫ አገልግሎትና ክትትል ሠራተኛ እንዲሁም የመረጃ ሠሌዳዎች አስፈላጊውን መረጃ እንዲያገኝ መደረግ አለበት፣
- ማንኛውም ተጓዥ ከቀረቡት ደረጃዎች የሚፈልገውን የአገልግሎት ዓይነት በመምረጥና ትኬት ቆርጦ የመንጓዝ መብቱ ተግባራዊ እንዲሆን የመናኸሪያ ውስጥ ሠራተኞች ክትትልና ድጋፍ ያደርጋሉ::
- መናኸሪያዎች ከሽኚዎች ንክኪ የተጠበቀ ሆነው ለተጓዦች አገልግሎት እንዲሰጡ መደረግ አለበት፣
- በመናኸሪያ ውስጥም ሆነ በጉዞ ላይ ለአቅመደካሞች፣ ለአካል ጉዳተኞች ልዩ እንክብካቤ መደረግ አለበት፣
- ተጓዡ መንገደኛ ጓዙን በማስመዘን ክፍያ ከፈፀመ በኋላ ዕቃውን ለአውቶብስ ሠራተኞች በማስረከብ የተሰጠውን የዕቃ ታግ በመያዝ መናኸሪያ ውስጥ ማረፊያ

ክፍል በመሄድ ጉዞውን ይጠባበቃል:: ሆኖም እድገ ቢዘገይ በ60 ደቂቃ ውስጥ ጉዞው መጀመር አለበት፣ (አውቶቡስ ከመናኸሪያ ሲወጣ ይገባል)

- ሰቃ ተጭና እንደተጠናቀቀ ተሣፋሪዎች ለጉዞ በተዘጋጀው አውቶቡስ በመግባት በትኬት ቁጥሩ መሠረትበመቀመጥ ይጓዛሉ:: ይህ ሥራ በእያንዳንዱ ኦፕሬተር በተመደቡ ሠራተኞች ተገባራዊ ይደረጋል::
- የፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን እና በየደረጃው ያሉ የክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች በየዕለቱ አፈጻጸሙን መከታተልና ጉድለት ሲኖር ተገቢ የእርምት እርምጃ መውሰድ አለባቸው::

## 8.7. የሌሊት ጉዞ ስለመከልከል፣

በሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ መናኸሪያዎች መደበኛ አገልግሎት የሚሰጠው ከመናኸሪያ መናኸሪያ በቀን ውስጥ በመሆኑና ለዚህም በተሻሻለው የመናኸሪያ ባለቤትነት ግንባታና አስተዳደር አጠቃቀም አገር አቀፍ መመሪያ ክፍል ሁለት አንቀጽ 7 ንኡስ አንቀጽ 7.1 ተራ ቁጥር 2 መሠረት በየዕለቱ በቀን ክፍለ ጊዜ የሚሰጥ በመሆኑ ከዚህ ውጭ በሌሊት የሚሰጥ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በዚህ መመሪያ መሠረት የተከለከለ ተግባር ነው:: ይሁንና በአዲስ አበባ ከተማና በኦሮሚያ ልዩ ዞኖች ከአዲስ አበባ ናዝሬት፣ ሞጆ፣ ደብረዘይት በመደበኛ መርሐ ግብር መሰረት ከመናኸሪያ ግቢ እስከ ምሽቱ 2.00 ሰዓት ድረስ ለተገልጋዩ ሕዝብ በሚሰጣቸው የሥምሪት ፈቃድ ማረጋገጫ መሰረት መመሪያውን በማይጻረር መልኩ እንዲሰሩ ይደረጋል::

## 8.8 የሥምሪት ዓይነት አፈፃፀም

8.8.1 በፌዴራል ደረጃም ሆነ በክልል የመሥመሮች አሸፋፈን በነፃ ሥምሪት ይሆናል::

8.8.2 በነፃ ሥምሪት እንዲሸፈኑ የሚደረጉ መሥመሮች በሥራ መርሀ-ግብር በተደገፈ አሠራር ተገባራዊ መደረግ አለባቸው::

8.8.1 የነፃ ሥምሪት አሠራርን ተገባራዊ በማድረግ ሂደት ተሣፋሪውን መጉተት፣ ማዋከብ፣ ማደናገር ካሰበው ቦታ ሳይደርስ እንዲወርድ ማስገደድ ፈጽሞ የተከለከለ ነው፣

## 8.9 ስለኩታ-ገጠም ክልሎች ሥምሪት አፈፃፀምና የክፍያ ታሪፍ

8.9.1 በአንደኛ ክልል የፀደቀ የሥምሪት የሥራ መርሀ-ግብር በሌላኛው ኩታ-ገጠም ክልል ተግባራዊ ይደረጋል፣ የተዘጋጀው የሥምሪት መርሐ-ግብር ግን አስቀድሞ ለሌላኛዉ ክልል እንዲደርስ መደረግ አለበት፣

8.9.1 በኩታ-ገጠም ክልሎች በተመሣሣይ መሥመሮች የሚሠራበት ታሪፍ ሁኔታ አዋሣኝ ክልሎች በጋራ የሥምሪት መሥመርችን በመለየት ትራንስፖርት ቢሮዎቹ በሚስማሙበት ታሪፍ መሠረት ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

8.9.2 የሕዝብ ማመላለሻ አውቶብሶች የክፍያ ታሪፍ በልዩ ልዩ ምክንያት ሲጨምር ወይም ሲቀንስ ክልሎች ወዲያውኑ እንዲያውቁት የማድረግ ሥራ በፌዳራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን ክልሎች ደግሞ የአካባቢያቸውን ወቅተዊ የሕዝብ ትራንስፖርት ታሪፍ ለማዘጋጀት እንዲያስችላቸው በአገር አቀፍ ደረጃ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ ሲኖር ወዲያውኑ ከየክልላቸው የንግድ ቢሮዎች ሲያውቁ የሚችሉበትን ሁኔታ በማመቻቸት ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡

8.9.3 ለደረጃ ውድድር በመንግስት ተወስኖ ከተቀመጠው የታሪፍ ጣሪያ በታች ቀንሶ መወዳደር ይቻላል፡፡

## *8.10 ለለአሽከርካሪዎች ረዳቶች ገንዘብ ተቀባዮችና ሌሎች በሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሥራ ላይ ለተሠማሩ ሰዎች የብቃት ማረጋገጫ:-*

8.10.1 በዚህ መመሪያ ክፍል አንድ አንቀጽ 1.3 "ሠ" መሠረት በተሰጠው ትርጉም መሠረት በዘርፉ የተሠማሩ ሠራተኞች የኦኘሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ምሥክር ወረቀት (Competence of certificate) ከፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ወይም ከክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች ማውጣት ይችላሉ፡፡

8.10.2 የብቃት ማረጋገጫ ጥያቄ ሳቀረቡ አሽከርካሪዎች፣ ረዳቶች፣ ገንዘብ ተቀባዮችና ሌሎች በሕዝብ ማመላለሻ ሥራ የሚሠማሩ ሰዎች የምሥክር ወረቀት ማረጋገጫ ከመውሰዳቸው በፊት ስለትራንስፖርት ሕግና ደንብ ስለተገልጋዩ ሕዝብ መብት በፌዳራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ወይም በትራንስፖርት ቢሮዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

# ***ክፍል ዘጠኝ***

## ***የሕዝብ ትራንስፖርት የሥነ-ሥርዓት መቆጣጠሪያ መመሪያ***

አዲሱን የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ስምሪትና አፈፃፀም የመናኸሪያ አስተዳደር መመሪያ ተግባራዊ በማድረግና አገልግሎት በመስጠት ሂደት የሚፈፀሙ የዲሲኘሊን ግድፈቶችን ለመቆጣጠር የሚረዱ ወጥ የሆኑ ዝርዝር የዲስፒሊን መቆጣጠሪያ የቅጣት አፈፃፀም ማዘጋጀት አስፈሳጊ በመሆኑ ይህ የትራንስፖርት ድርጅቶች ማኅበራት፣ አሽከርካሪዎች፣ ረዳቶችና ባለንብረቶች የሚጠየቁበት የጥፋት ዓይነትና ዝርዝር የቅጣት መጠን ሪኮርድ በደረጃ ተሰይቶ ተዘጋጅቷል፡፡

### 9.1. <u>የቅጣት አወሳሰንን በተመለከተ፣</u>

- የመጀመሪያ ጥፋት እንደ ጥፋቱ ክብደት በገንዘብ ይቀጣል፡፡
- ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት የፈፀመ በጥፋት ደረጀው የተወሰነው የቅጣት ገንዘብ ሲባዛ በሁለት፡፡
- ለሶስተኛ ጊዜ የጥፋት ደረጃው ሲባዛ በሶስት፡፡
- አራተኛ ጊዜ ጥፋት የፈፀመ የጥፋት ደረጃው ሲባዛ በአራት ይሆናል፡፡
- ለአምስተኛ ጊዜ የተፈፀመ የጥፋት ደረጃቸው ሲበዛ በአምስት እየተባዛ ይወሰናል፡፡
- ጥፋቱ እየተደጋገመ ከቀጠለ በዚሁ ዓይነት እየተባዛ ይወሰናል፡፡ ሆኖም በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ ከሆነ ከፍተኛ ጥፋት በሆነው ገንዘብ መጠን ተባዝቶ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

### 9.2. <u>የጥፋት ሪኮርድ አያያዝ፣</u>

- ማንኛውም የጥፋት ሪኮርድ ተይዞ የሚቆየው ጥፋቱ ከተፈጸመበት ጊዜ አንስቶ ለአንድ ዓመት ብቻ ይሆናል፡፡

### 9.3 <u>ቅጣት፣</u>

#### 9.3.1 <u>አሽከርካሪዎችን የሚያስቀጣ:-</u>

**<u>የጥፋት ዓይነት፣ ደረጃና የቅጣት መጠን ( ከብር 50 -3000)</u>**

***<u>ደረጃ 1 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት(ብር 50)</u>***

1. በአደራ የተቀበለውን መልዕክት፣ ፖስታ፣ ጋዜጣ፣ ወዘተ... ለሚመለከተው አካል ያላስረከበ፣

## ደረጃ 1 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት/ብር 80/

1. ተቀያሪ ጐማና ተፈላጊ መፍቻ ሳይዝ ያሽከረከረ፣

## ደረጃ 1 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት/ብር 100/

1. የሹፌሩን እይታ የሚከላከሉ መጋረጃዎች፣ ተለጣፊ ላስቲኮች የለጠፈ፣
2. የተሽከርካሪውን የውስጥና የውጭ ንፅሕና በሚገባ ያልጠበቀ፣
3. በሥምሪት መርሀ-ግብሩ መሠረት የጉዞ እንቅስቃሴውን ተግባራዊ ያላደረገ፣
4. የተበላሸ ተሽከርካሪ ወይም በቀልፍ የማይነሣ ተሽከርካሪ ለሥምሪት ያቀረበ እንዲሁም ሆን ብሎ ተሽከርካሪን ለአገልግሎት ሳይከፍት በመናኸሪያ ውስጥ ከሁለት ሰዓት በላይ አቁሞ የሄደ፣
5. ተሣፋሪን ያለአግባብ የጉተተ፣ ያንገላታና ያንጓጠጠ፣
6. በተሽከርካሪዎች መሀከል ያለውን ርቀት ጠብቆ ያላሽከረከረ፣
7. የቀለት አቅጣጫን ጠብቆ ያላሽከረከረ፣
8. በምሽት ባልተሟላ መብራት ያሽከረከረ፣
9. በባቡር ሃዲድ አጠገብ ተገቢውን ጥንቃቄ ያላደረገ፣
10. በመናኸሪያ ውስጥ ሁከት የፈጠረ፣
11. የለማጅ ምልክት ሳይለጥፍ፣ ወይም በተከለከለ ቦታ ዕጩ አሽከርካሪዎችን ያለማመደ፣
12. የድንገተኛ የቴክኒክ ምርመራን እንዲያደርግ ሲጠየቅ ፈቃደኛ ያልሆነ፣
13. ከተፈቀደው የመጫን ልክ በላይ ትርፍ ተሳፋሪ የጫነ በየእንዳንዱ ተሣፋሪ 100 ብር ይቀጣል::
14. ለእረፍት በተመረጡ ቦታዎች /ለቁርስ፣ ለምሣ/ ተገቢውን እረፍት ያላደረገ፣
15. የኦኘሬተርነት ፍቃድ ማረጋገጫ ፍቃድ /ፎቶ ኮፒ/ እና ሌሎች የጉዞ ሰነዶችን አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ ይዞ ያልተገኘ፣
16. በመንገድ ላይ ለእግረኞች ቅድሚያ ያልሰጠ፣

17. መንገድ ላይ ተሽከርካሪ ደርቦ ያቆመ፣ ወይም የተሣሰጠ የጉዞ እንቅስቃሴ እንዳይኖር እንቅፋት የሆነ፣

18. በትራፊክ መብራትና አካባቢ መከበር የሚገባውን ሕግ ያላከበረ፣

## ደረጃ 1 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት/ብር 120/

1. ከተፈቀደው በላይ ከባድ መብራት /ፓውዛ/ የተጠቀመ፣
2. ያለአንፀባራቂ ምልክት የተበላሸን ተሽከርካሪ መንገድ ላይ ያቆመ፣
3. ከተፈቀደለት ጊዜ በላይ ተሽከርካሪን መንገድ ላይ ያቆመ፣
4. ለአሳፊ ተሽከርካሪ ቅድሚያ የከለከለ፣
5. በእግረኞች መንገድና በከተማ አውቶብስ ማቆሚያ በተከለለ ቦታ ላይ ተሽከርካሪ ያቆመ፣

## ደረጃ 1 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት/ብር 140/

1. መስቀለኛ መንገድ ላይ ቅድሚያ ያልሰጠ ተሽከርካሪ፣
2. ከተፈቀደ ፍጥነት በታች ተሽከርካሪ ያሽከረከረ፣

## ደረጃ 1 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት/ብር 150/

1. የእድሳት ጊዜ አሳልፎ የብቃት ማረጋገጫ  ፍቃዱን ለማሳደስ የቀረበ አሽከርካሪ፣

## ደረጃ 1 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት/ብር 160/

1. አንፀባራቂ ምልክት የሌለውን ተሽከርካሪ ያሽከረከረ፣

## ደረጃ 1 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት/ብር 200/

1. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፍቃዱን ሳያሳድስ ተሽከርካሪ ያሽከረከረ፣
2. በመንገድ ላይ ተሽከርካሪ ያጠበ፣
3. አእምሮ የሚያውክ ድምፅ /ጡሩንባ/ ወይም ጢስ ያለው ተሽከርካሪ ሲያሽከረክር የተገኘ፣
4. በሕዝብ መጓጓዣ ተሽከርካሪ ላይ ወደ ጉን ወደፊት ኋላ የተንጠለጠለ ትርፍ እቃን ጭኖ ማሽከርከር፣

5. በሕዝብ ማጓጓዣ ተሽከርካሪ እንስሳ ወይም ለጤንነት፣ ለምቾት ተስማሚ ያልሆነ ዕቃ ጭኖ መገኘት፣
6. ለአምቡላንስ፣ እሳት አደጋ ተሽከርካሪ ቅድሚያ አለመስጠት፣
7. በመታጠፊያ መንገድ፣ ድልድይ ጠባብ መንገድ፣ በርቀት ለዕይታ በሚጋርድ ቦታ ተሽከርካሪን መቅደም /ለመቅደም መሞከር/፣
8. ተሳፋሪዎችን ጭኖ መጓዝ ከጀመረ በኋላና በተሽከርካሪ ውስጥ እያሉ ነዳጅ መሙላት፣
9. በከተማ ክልል ውስጥ ከገራዥ ገቢ ውጪ በመንገድ ላይ ቀላል ወይም ከባድ ጥገናና ሌሎች የጉሚስታ ሥራዎች ለመሥራት ተሣፋሪ ጭኖ ለረዥም ጊዜ ተሽከርካሪ ማቆም፣
10. በመናኸሪያ ውስጥ ጉማን ከመቀየር የዘለለ የተሽከርካሪ ጥገና ማካሄድ፣
11. በቀኝ በኩል ከፊት ያለን ተሽከርካሪ መቅደም ወይም ለመቅደም መሞከር፣
12. ተገቢውን የጉዞ ሰነድና ሕጋዊ መንጃ ፈቃድ ሳይዝ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ሲያሽከረክር መገኘት፣
13. በመመሪያው የተለየውን ባጅ አድርጉ፣ የደንብ ልብስ ለብሶ ሥራ ላይ አለመገኘት፣
14. አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ መረጃ አለመስጠት፣
15. በተፈቀደለት የጉዞ መርሐ ግብር መሠረት ተግባራዊ አለማድግ፣
16. ተሳፋሪን ማንገላታት፣ ማንጓጠጥ፣ መጉተት፣
17. መነሻና መድረሻን፣ ታሪፍ፣ ርቀት በኪሎ ሜትር የሚገልፅ ታፔላ ያለመለጠፍ፣
18. ለተንዠም ሆነ ለዕቃ የሚከፈል ክፍያ ሕጋዊ ደረሰኝ አለመሥራት የዕቃ ታግ አዘጋጅቶ ሥራ ላይ አለማዋል፣
19. በምሽት ወይም መብራት በሚያስፈልግበት ጊዜ መብራት ሳያበራ ያሽከረከረ፣

## ***ደረጃ 1 የቅጣት ዓይነት (ብር 500)***

1. በትራንስፖርት እጥረት የሕዝብ ክምችን ለማንሳት የወጣን መርሐ ግብር ለመፈፀም ፈቃደኛ አለመሆን፤

2. የሕዘብ ክምችትና የትራንስፖርት እጥረት የሚፈጠርባቸውን ጊዜያት ጠብቀ የወጣስትን መደበኛ የተሽከርካሪ ሥምሪት ፕሮግራም አስመሽፈን ወይም ሳስመሽፈን ሕገወጥ ተግባር መፈፀም፤

3. ከመደበኛ የሥምሪት ፕሮግራም በተጨማሪ የተሰጠውን የልዩ ጉዞ መርሐ ግብር ከመመሪያው ውጪ በሆነ መልኩ በተገልጋዩ ላይ ጫና ለመፍጠር ያልተፈቀደ ተግባር መፈፀም፤

4. ተገልጋዩን ሕዝብ በተገቢ ሁኔታ አገልግሎት አለመስጠት፤

5. ሕጋዊ የልዩ ጉዞ መውጫ ፈቃድና ስለጉዞው ትክክለኛነት ከአስፈፃሚው አካል ማረጋገጫ ባለመያዝ ሥምሪት ሲፈፅም ከተገኘ፤

## ደረጃ 1 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት /1000 ብር/

1. ለሚሰጠው አገልግሎት ከሚሰራበት ተሽከርካሪ ባለንብረት ጋር የሥራ ውል ሳይፈጽም ሲሰራ ከተገኘ፣

2. ከሕጋዊ የአሰራር ሥርዓት ውጭ በመሆን የወጣለትን መርሐ ግብር አለመሸፈን፣

3. ከመናኻሪያ ውጭ ለሚደረግ ሕገወጥ ጉዞ ተገልጋዩን በወያላና ደላሎች በመጠቀም ጥሪ በማስደረግና በማጉላላት ተገቢ ያልሆነ ተግባር ሲፈጽም ከተገኘ፣

4. ተሽከርካሪው ለዘርፉ አገልግሎት የተደራጀበትን ማሕበር (ድርጅት) የሚገልጽ የተሟላ መረጃ ሳይኖረው ለሥራ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ፣

## የጥፋት ዓይነት፣ ደረጃና የቅጣት መጠን/ ከብር 300-1000/ ወይም (ከብር 1000 ከአንድ በወር ሥራ ዕገዳ ጋር)

## ደረጃ 2 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት (ብር 300)

1. ሕዝብና እንስሣት በሚጠቀሙበት ወንዞች፣ ኩሬዎች፣ ጉድጓዶች ተሽከርካሪን ማጠብ ወይም እንዲታጠብ ማድረግ፣

2. የተሽከርካሪው በር መዝጊያ ሳይዘጋ ማሽከርከር፣

3. የተጓዦች (የመንገደኞች) ንብረት በጥንቃቄ ባለመያዝ እንዲበላሽ ወይም እንዲሰበር ማድረግ፣

4. ለአደጋ በማያጋልጥ ሁኔታ በሕግ ከተፈቀደው የፍጥነት ወሰን በላይ ማሽከርከር፣

5. በማንኛውም ወቅት የመንገድ ተቆጣጣሪዎች ለቁጥጥር እንዲቆም ታዞ ያለመቆም ወይም ማምለጥ፣ ጥሶ መሄድ፣

6. በመንገድ ላይ ተቆጣጣሪዎች ተጠይቆ መንጃ ፈቃድና አስፈላጊ መረጃዎችን ለማሳየት ወይም ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ፣

7. በማንኛውም ወቅትና ቦታ ቀኝ ጠርዝ ሳይዙ በመንገድ ላይ ተሣፋሪ ማውረድ ወይም ዕቃን መጫን ወይም ማራገፍ፣

8. የትራፊክ አደጋ በተከሰተበት ወቅት በአደጋው ለተጎዱ ሰዎች የአስቸኳይ ዕርዳ እንዲያገኙ ወደሕክምና ቦታ ለመንንዝ በመንገድ ላይ ትራፊክ ደኅንነት ተቆጣጣሪዎች ትብብር ተጠይቆ ፈቃደኛ ያለመሆን፣

9. የመንገድ ላይ ተቆጣጣሪዎች ለሚጠይቁት የተለያዩ መረጃዎች ለመስጠት ፈቃደኛ ያለመሆን ወይም የተሣሣተ መረጃ መስጠት፣

10. በጉዞ ላይ እያለ ተሽከርካሪው በቴክኒክ ችግር ምክንያት ሲቆም ተሣፋሪዎች በፈለጉት መንገድ ለመሄድና ለመንንዝ ከከፈሉት ብር ውስጥ የተጓዙትን ርቀት አስልቶ ያልተጠቀሙበት ገንዘብ አለመመለስ ወይም በአንድ ሰዓት ውስጥ ምትክ ተሽከርካሪ መድቦ እንዲጓጓዙ አለማድረግ፣

11. በተለያዩ ምክንያት አስገዳጅነት መደበኛ ባልሆኑ ሁኔታዎች ሕዝብ ለመንንዝ ብዛት ያላቸው የተሽከርካሪዎች በሚፈልጉበት ወቅት ተሽከርካሪን ለማቅረብ ተጠይቀው ለመሄድ ፈቃደኛ አለመሆን፣

12. አልኮል መጠጥና አደንዛዥ ዕፅ ወስዶ ሲያሽከረክሩ መገኘት፣

13. ከተፈቀደለት መሥመር /ኪሎ ሜትር ገደብ/ ውጭ ሲያሽከረክር መገኘት፣

14. የጠፋ ወይንም የተረሱ ዕቃዎች በአግባቡ ጠብቆ ለሚመለከተው አለማስረከብ፣

15. ሌሎች በሥምሪት አፈፃፀምና በመናኸሪያ አስተዳደር የተዘረዘሩ ተግባራትን አክብሮ አለመሥራት፣

16. ተጓዥ መድረሻዉ ብሎ ከተሣፈረበት ሥፍራ አሣልፎ ማውረድ፤

17. የተቆጣጣሪን የቁም ምልክት ጥሶ የሄደ፣

18. የሚከለክል ወይም የሚያስገድድ ምልክት የጣሰ፣

19. በጠባብ መንገድ ላይ፣ ድልድይ ላይ፣ ወይም መታጠፊያ መንገድ ላይ መኪና ያቆመ፣

20. የተከለከለ መንገድ አካፋይ ደሴት /መስመር/ ያቋረጠ፣

21. ምልክት ሳያሳይ ተሽከርካሪን ከቆመበት ቦታ ያንቀሳቀሰ ወይም ያቆመ፣

22. የዕለትና የተሳሳፊ ሰሌዳ ከተፈቀደለት ጉዜና ቦታ ውጭ የተጠቀመ፣

23. የስአግባብ የፍሬቻ መብራት ያሳየ፣

24. የመናኸሪያ መግቢያና መውጫ በር ዘግቶ የትራፊክ ፍሰቱን ያስተጓጐለ እንዲሁም በሆስፒታልና እሳት አደጋ በሮች ላይ ተሽከርካሪ ያቆመ፣

25. በዚህ መመሪያና ሕግ ከተቀመጠው የዕድሜ ገደብ በታች ካሉ ሕፃናት ክፍያ የተቀበለ፣

26. የሚሸፈን ሥምሪት መሥመር እያለ ሕጋዊ ፍቃድ ሳይወስድ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪን በማሸሽ ጋራዥ ወስዶ ያቆመ፣

27. ለስምሪት በሕጋዊ አካል ሲጠየቅ ፈቃደኛ ያልሆነ፣

28. በተደመሰሰ፣ በተቆረጠ፣ በተሸፈነ ወይም በሕገ ወጥ ሰሌዳ የተጠቀመ፣ ወይም ሰሌዳ ሳይኖረው ያሽከረከረ፣

29. ከተፈቀደለት አገልግሎት ውጭ ተሽከርካሪን የተጠቀመ /ያስማራ/፣

30. መንጃ ፈቃድ ሳይኖረው ሲያስማምድ የተገኘ፣

31. የሚታጠፍበትን አቅጣጫ ሳይዝ ያሽከረከረ፣

32. Belt /ቀበቶ/ ሳያስር ያሽከረከረ፣

33. የተሽከርከሪ ሰሌዳ በተገቢው ቦታ ያላሰረ ወይም እንዳይፈታ አድርጐ የበየደ፣

34. የቴክኒክ ብቃቱ ያልተሟላ ተሽከርካሪ ሲያሽከረክር የተገኘ፣

35. የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ያለሕጋዊ ፈቃድ ሆን ብሎ ከስምሪት አሸሽቶ የደበቀ፣

## ደረጃ 2 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት (ብር 400)

1. በተሽከርካሪው ላይ ተገቢ ያልሆነ አካል የጨመረ፣

## ደረጃ 2 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት (ብር 500)

1. ሕገወጥ በሆነ መንገድ ነፃ ስምሪት ተቃውሞ ማፍረስ፣ ወይም ሌሎችን በአድማ መልክ ማነሣሣት፣
2. ከተፈቀደለት የስምሪት መስመር /ኪሎ ሜትር ገደብ / ውጪ ሲያሽከረክር መገኘት፣
3. የተሽከርካሪ መናኸሪያ ባላቸው ከተሞች ውጪና በመናኸያ ውስጥ በሕገ-ወጥ መንገድ ተሣፋሪ ያስፈቃድ የጫነ፣
4. በማናቸውም ምክንያት ተሳፋሪዎች በመንገድ ላይ በማይፈልጉበት ቦታ አውርዶ ትቶ መሄድ፣
5. ከተወሰነው ታሪፍ በላይ ማስከፈል፣
6. ከሚመለከተው አካል ሕጋዊ ፈቃድ ውጪ በጭነት ተሽከርካሪ ሰው መጫን፣
7. በሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ በውጭ አካል ሰው መጫን፣
8. የሊሳን ተሽከርካሪ ሠሌዳ ቁጥር ወይም ዓመታዊ ተሰጣፊ /ቦሎ/ ስጥፎ ማሽከርከር፣
9. በማንኛውም ቦታና ወቅት ተሽከርካሪ በእንቅስቃሴ ላይ እያለ በተንቀሳቃሽ ስልክ /ሞባይል/ እያነጋገሩ ማሽከርከር፣
10. ተሽከርካሪ በጉዞ ላይ እያለ ወይንም ሳይቆም ሰውን መጫን ወይም ማውረድ፣
11. ተሣፋሪው ከመነሻው መድረሻዬ ብሎ የተነሣበትን የጉዞ መድረሻ መሰረዝ ወይም ወደ ሌላ ተሽከርካሪ መሸጋገር፣
12. በተለያዩ ምክንያቶች በሚመለከተው አካል ተሽከርካሪ እንዳያሽከረክር መንጃ ፈቃድ ታግዶበት እያለ በመንገድ ላይ ማሽከርከር፣
13. ከአገልግሎት መስጫ መናኸሪያ የአገልግሎት ቅፅ ሳይዝ የወጣ አሽከርካሪ፣
14. የትራፊክ አደጋ አድርሶ ቦታው ላይ ተሽከርካሪ ያሳቆመ፣ ለማምለጥ የሞከረ፣
15. 5 ሰውና ትርፍ የጫነ፣
16. የሌላን ተሽከርካሪ ሠሌደ ቁጥር ወይም ዓመታዊ ተሰጣፊ (ቦሎ) ስጥፎ ማሽከርከር፣
17. የሚያሰክር መጠጥ ጠጥቶ መንዳት፣
18. በማንኛውም ወቅት ጫት እየቃሙ ተሽከርካሪ ማሽከርከር፣
19. በማንኛውም ቦታና ወቅት ተሽከርካሪ በእንቅስቃሴ ላይ እያለ ተንቀሳቃሽ ስልክ (ሞባይል) በእጅ ይዞ ማነጋገር፣

20. ተሽከርካሪ በጉዞ ላይ እያለ ወይም ሳይቆም ሰውን መጫን ወይም ማውረድ፣

21. ተሳፋሪው ከመነሻው መድረሻዉ ብሎ ከተነሳበት ቦታ ውጭ በመንገድ አቋርጦ መመለስ ወይም ተጓዦች ወደ ሌላ ተሽከርካሪ በማሸጋገር እንዲሄድ በማድረግ መመለስ፣

## <u>ደረጃ 2 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት (ብር 1000)</u>

1. የሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ኖርት ከምድቡ ውጪ የሆነ ተሽከርካሪ ማሽከርከር፣

## <u>ደረጃ 2 የቅጣት ዓይነት (ብር 1000 የ1ወር የሥራ ዕገዳ)</u>

1. በሕዝብ ክምችትና ትራንስፖርት እጥረት በሚታይባቸው ጊዜያቶች የወጣውን የአሠራር መመሪያ የሚያደናቅፍ ተግባር ፈፅሞ መገኘት፤
2. የትራንስፖርት እጥረትን ተከትሎ የተቀመጠውን የአሠራር መመሪያ ባልጠበቀ አግባብ ለጥቅም ብቻ በማሰብ ሕገወጥ ሥምሪት ለመፈፀም መሞከር፤
3. ለሚሰጠው አገልግሎት የተሟላ የሙያ ማረጋገጫ ፈቃድ (ደረጃውን የጠበቀ መንጃ ፈቃድ) ሳይዝ ሲሠራ ከተገኘ፤

## <u>ደረጃ 2 የጥፋት ዓይነት /2000 ብር/</u>

1. ከመደበኛ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ መናኸሪያ ውጪ ሲሠራ ከተገኘ፤
2. በተሰጠው የሥምሪት መርሐ-ግብር መሰረት መስጠት ከሚገባው የአገልግሎት ርቀት ወሰን ውጭ ለመንቀሳቀስ ሲሞክር ከተገኘ፣

## <u>*ደረጃ 3 የጥፋት አይነትና ቅጣት (ብር 2500 ከ2 ወር የመንጃ ፈቃድ ዕገዳ ጋር )*</u>

1. የሕዝብ ክምችትና የትራንስፖርት እጥረት መፈጠሩን ምክንያት በማድረግ መደበኛም ሆነ በልዩ የተሰጠን መርሐ ግብር ለመፈፀም ፈቃደኛ አለመሆን፤
2. የሕዝብ ጥቅምን በሚጐዳ መልኩ አሳፌ ጥቅምን ለማግኘት ሲባል በሕዝብ ክምችትና ትራንስፖርት እጥረት ወቅት ሕገወጥ የሥምሪት እንቅስቃሴ ለማድረግ መሞከርና ተገልጋዩን ማንገላታት፤

3. ሕጋዊ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ (ደረጃውን የጠበቀ መንጃ ፈቃድ) ሳይዝ አገልግሎት መስጠት፤

4. ከሕገወጥ ተግባር ባሻገር በተቀጣጣሪ በሚጠየቅበት ድርጊት ፈቃደኝነት አለማሳየትና ጉዳት ለማድረስ ወይም አምልጦ ለመሰወር ሙከራ ማድረግ፤

5. በማንኛውም ወቅት የሚሰጥ መደበኛ አገልግሎትን ከአሠራር መመሪያ ውጪ በተገልጋዮች ላይ ጫና በመፍጠር አሳፊ ተጠቃሚ ለመሆን መሞከር ወይም ይኸን ከሚያደርጉ ደላሳና ወያሉች ጋር ተመሳጥሮ ሕገወጥ አገልግሎት ሲሰጥ ከተገኘ፤

## ደረጃ 3 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት(ብር 3000)

1. የአሽከርካሪ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወስዶ የተሰጠውንና የሚያሽከረክረውን ተሽከርካሪ ፈቃድ ለሌላ ሰው አሳልፎ የሰጠ፣

## ደረጃ 3 የጥፋት ዓይነት /4000 ብር/እና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ስለመሰረዝ፣

1. ከጉዞ ርቀት ወሰኑ ውጭ የተጭበረበረ ሰነድ በመያዝና እና በመርሐ-ግብር ያልተደገፈ ሥምሪት ሲፈጽም ከተገኘ፣

2. በማናቸውም ሕጋዊ አካል የሚጠየቀውን የሥራ መረጃና ሰነድ ለማሳየት ያልፈቀደ ወይም አምባጓሮ በማስነሳት የአሰራር ችግር ከፈጠረና ከዛተ፣ወይም ከዘለፈና ካንቋሸሸ፣

3. የተሽከርካውን የፊትና የኃላ ሰሌዳ በራሱ ፈቃድ በመፍታት ወይም ለዕይታ እንዳያመች ያደረገ እንዲሁም በጥቃና ሌሎች መከለያዎች በመጠቀም ሲንቀሳቀስ ከተገኘ፣

4. የተሽከርካው የኃላ ሰሌዳ በሚመለከተው አካል ከተፈታ በኃላ ቅጣቱን ሳይፈጽም በያዘው የቅጣት ሰነድ (የቁጥጥር ክስ ወረቀት) ብቻ ሲሰራ ከተገኘ፣

## ደረጃ 3 የጥፋት‹ ዓይነትና ቅጣት(ብር 5000)

1. መንጃ ፈቃድ ሳይኖረው ተሽከርካሪ ማሽከርከር፣

## *ደረጃ 4 የጥፋት ዐይነትና ቅጣት (ብር* 4000 እና የዘርፉን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ስለመሰረዝ*)*

1. ከጉዞ ርቀት ወሰኑ ውጭ የተጭበረበረ ሰነድ በመያዝና እና በመርሐ-ግብር ያልተደገፈ ሥምሪት ሲፈጸም ከተገኘ፣
2. በማናቸውም ሕጋዊ አካል የሚጠየቀውን የሥራ መረጃና ሰነድ ለማሳየት ያልፈቀደ ወይም አምበናጋር በማስነሳት የአሰራር ችግር ከፈጠረ፣
3. የተሽከርካውን የፊትና የኃላ ሰሌዳ በመፍታት ወይም በተሳሰፈው ደንብ ሠሌዳው ተፈቶ ቅጣት ሳይፈጸም በያዘው የቅጣት ሰነድ (የቁጥጥር ክስ ወረቀት) ለመስራት ሲሞክር ከተገኘ፣
4. የተሽከርካውን የፊትና የኃላ ሰሌዳ በመፍታት ወይም ሰይታ እንዳይኖር በጭቃና ሌሎች መከለያዎች በመጠቀም ሲንቀሳቀስ ከተገኘ፣

## <u>ደረጃ 4 የጥፋት ዓይነት /5000 ብር/ እና የዘርፍ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ መንጃ ፈቃድ መሠረዝ፣</u>

1. ከመደበኛ አገልግሎት ውጭ በሕገወጥነት ያለሥምሪት ፈቃድና ደረጃውን የጠበቀ መንጃ ፈቃድ ሳይዝ ሲሠራ ከተገኘ፤
2. የተሽከርካውን የፊትና የኃላ ሰሌዳ በመፍታት ቁጥጥር እንዳይደረግበት በማሰብ በኬላ ሳይ (በማንኛውም ቦታ ሳይ በሚደረግ ቁጥጥር) ፍጥነትን ከሚገባው በሳይ በመጨመር ለማምለጥ የሞከረ (ያስመለጠ) ወይም በተቆጣጣሪ አካላት ሳይ ጉዳት ለማድረስ የሞከረ፣
3. መደበኛ አገልግሎት እደሚሰጥ በማስመሰል በሐሰተኛ ሰነድ አዘጋጅቶ ሲሰራ ከተገኘ፣
4. ከመደበኛ የትራንስፖርት አገልግሎት የሥምሪት አፈጻጸም መመሪያ እና መርሐ ግብር ውጭ ለመሠማራት ወይም ሳልተፈቀደ ጉዞ ለማድረግ ሲሞክር ከተገኘ፣

## 9.3.2 <u>የተሽከርካሪ ባለንብረት የሚያስደቁ:-</u>

### <u>የጥፋት ዓይነት፣ ደረጃና ቅጣት መጠን/ ከብር 300 እስከ 3000/</u>

### <u>ደረጃ 1 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት (ብር 300)</u>

1. የሕዝብ ማመሳለሻ ተሽከርካሪ ያለ ሕጋዊ ፈቃድ ከስምሪት አገልግሎት ውጪ ማድረግ /መደበቅ/፣

2. የኦኘሬተርነት ፈቃድ በተሰጠው ወቅት ተሟልተዋል ተብለው የተገለፁት በቁጥጥር ወቅት አንደሎ መገኘት፣

3. በተዘጋጁ ቅጾች መሰረት የሚዘጋጁ መረጃዎች በአግባቡና በወቅቱን ጠብቆ አለማስተላለፍ፣

4. በተሰጠው የኦኘሬተርነት ፈቃድ ብቃት ማረጋገጫ መሰረት በተሽከርካሪው ላይ በሁለቱም ጎኖች ከፊትና ከኋላ በመመሪያው መሠረት የደረጃ መለያ ቁጥር፣ የደረጃ መለያ ቀለም ያሟሉ አውቶቡሶችን ለሥምሪት ያላቀረበ፣

5. በፀደቀ የሥራ ወይም የጉዞ መርሀ-ግብር መሠረት አገልግሎት ያልሰጠ፣

6. የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ተለጣፊ ምልክት /ቦሎ/ ያለጠፈ ወይም ህገ-ወጥ ቦሎ ያደረገ፣

7. የደንብ ልብስ፣ ባጅ፣ መተወቂያ ለሠራተኞች ያላሟላ፣

8. ከሚመለከተው አካል ከተሰጠው ሕጋዊ ፈቃድ እና ከተፈቀደለት መደበኛ ሥራ ውጭ መሥራት፣

9. በከፊል የተቀረጠ /በገልፅ የማይታይ ወይም የፊት /የኋላ ሠሌዳ ብቻ ያለው /ያለጠፈ/ ተሽከርካሪ ይዞ መስራት፣

10. ተሽከርካሪን ለመንዳት ፈቃድ ሌላው ሰው እንዲያስተምርበት መፍቀድ፣

11. የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ እንዳይነዳ ታግዶ እያለ ሲያሽከረክሩ መገኘት ወይንም የታገደ ሰው እንዲያሽከረክር መኪናውን አሳልፎ መስጠት፣

12. የኦኘሬተርነት ፈቃድ ሲጠየቅ ለማሳየት ፈቃደኛ አለመሆን፡፡

13. ለሕዝብ መጓጓዣ ተሽከርካሪዎች ለተሣፋሪዎችም ሆነ ለዕቃ የሚከፈለውን ገንዘብ መጠን የሚገልፅ ህጋዊ ደረሰኝ በማዘጋጀት ሥራ ላይ አለማዋል፣

14. ሌሎች በሥምሪት አፈፃፀምና በመናኸሪያ አስተዳደር መመሪያዎች የተዘረዘሩትን አለመሥራት፣

## <u>ደረጃ 1 የጥፋት አይነትና ቅጣት (ብር 500 ከ15 ተከታታይ ቀናት የመስመር ውድድር መታገድ)</u>

1. በመመሪያው በተገለጹት ወቅቶች በመርሐ ግብር የወጣለትን መደበኛ የሥምሪት ፕሮግራም ካልሸፈነ፤
2. ከመደበኛ አገልግሎት ውጪ ያለውን የሕዝብ ክምችት የትራንስፖርት እጥረት ለመፍታት በመመሪያው መሰረት ስልዩ ጉዞ መርሐ ግብር የወጣለትን የሥምሪት ፕሮግራም አክብሮ አገልግሎት ካልሰጠ፤
3. የሕዝብ ክምችት በሚኖርባቸውና በመመሪያው በተገለጹ ጊዜያቶች ተሽከርካሪውን ለሥምሪት ካላቀረበ፣ ወይም የተለያዩ ምክንያት በማቅረብ ከአገልግሎት ተሳትፎ ውጭ ከሆነ ፤

## ደረጃ 1 የጥፋት ዓይነት /3000/

1. ተሽከርካሪውን ለሥራ ከሰጠው አሽከርካሪ ጋር የሥራ ውል ሳይፈጽም ለጥቶ ከተገኘ፣
2. አሽከርካሪው ከሕጋዊ የአሰራር ሥርዓት ውጭ እንዲሰራና የወጣለትን መር ግብር እንዳይሸፍን ካደረገ፣
3. የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎትን ባልተፈቀደ መልኩ ከመናኸሪ ውጭ እንዲሰራ ካደረገ ወይም ትዕዛዝ ከሰጠ፣
4. ከመናኃሪያ ውጭ ለሚደረግ ሕገወጥ ጉዞና በተገልጋዩ ላይ በወያላና ደላሎች ለሚደርስ ጥቃት ከተባበረ ወይም ካልተቆጣጠረ፣
5. ተሽከርካሪው የተደራጀበትን ማሕበር (ድርጅት) የሚገልጽ የተሟላ መረጃ እንዲኖረው ካላደረገ፣

## ደረጃ 2 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት (ብር 400)

1. መጠባበቂያ (ስኮርት) ትርፍ ጉማ ከነመፍቻው ሳይኖረው ወይም ሳይዝ የሕዝብ የንገድ መንንዣ ተሽከርካሪ ላይ ሰው አሣፍሮ መንዝ፣
2. ከሚመለከተው አካል ህጋዊ ፈቃድ ውጭ በዕለት ሠሌዳ የንገድ ሥራን መሥራት፣
3. የዕለት ሠሌዳ ከተፈቀደለት የአገልግሎት ጊዜ ውጭ መጠቀም፣
4. የመረጃ መስጫ መሣሪያዎችን በመኪናው ውስጥ አሟልቶ አለመገኘትና መረጃዎች ለተሣፋሪው እንዲሰጡ አለማድረግ፤



Republic of Ethiopia Transport Authority No. 1

## ደረጃ 2 የቅጣት ዓይነት (ብር 700 እና 1 መደበኛ መስመር ስስመታገድ)

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 9.3 የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት መወጣት ካልቻሉ፤
2. በሕገወጥ መንገድ ተሽከርካሪን ለማሠማራት መሞከር ወይም የሕዝብን የመገልገል ፍላጐት ላይ ዕጥረት ከፈጠረ፣
3. በመመሪያው ከተለዩት ጊዜያቶች ውጪ አላፊ ተጠቃሚ ለመሆን የልዩ ጉዞ ታሪፍ መጠየቅ ወይም በዚህ መልኩ አገልግሎት ለመስጠት ከሞከረ፣
4. በዚህ መመሪያ የሕዝብ ክምችትና የትራንስፖርት እጥረትን ችግር ለመፍታት ራሱን ችሉ ከመደበኛ አገልግሎት በመቀጠል በመርሃ-ግብር ለሚሰጥ ልዩ ጉዞ የተቀመጠ የከፍያ ታሪፍን በመደበኛነት መስጠት ለሚገባውና ስተመደበበት ጉዞ መስመር ተገልጋዩን ለማስከፈል ከሞከረ ወይም ሲያስከፍል ከተገኘ፣

## ደረጃ 2 የጥፋት ዓይነት /4000 ብር/

1. ከመደበኛ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ውጭ ባልተፈቀደ ሁኔታ በሕገወጥነት ከመናኻሪ ውጭ እንዲሰራ ፈቃድ የሰጠና የተባበረ፣
2. ከተሰጠው የድርጊት መርሐ- ግብርና መስጠት ከሚገባው ርቀት ወሰን ውጭ ተሽከርካሪው እንዲንቀሳቀስ ካደረገ፣

## ደረጃ 3 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት (ከብር 500 እስከ ብር 5000 እና ከዘርፉ ሥራ ማገድ/)

## ደረጃ 3 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት (ከብር 500)

1. ለሰውም ሆነ ለዕቃ ከተፈቀደው ታሪፍ (የአገልግሎት ዋጋ) በላይ በመጨመር እንዲከፍል ማድረግ ወይም እንዲከፍል መጠየቅ፣
2. የሬት ለሬት ግንባር መስታወት ሁኔታ ለዕይታን የሚከለክል ወይም ስንጥቅ ያለውና ነፋስና አቧራ የሚያስገባ፣ የዕይታ መቆጣጠሪያ መስታወቶች የግራና የቀኝ የኋላ

ማሳያዎች (ስፖኪዮ) የሌለው፣ ሙሉ ሲሾ ጐማ የተገጠመለት ወይም ያበጠና የተሰነጠቀ ጐማ የመሣሰሉ ጉድለቶች ያለው ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ ማንቀሳቀስ፣

3. ሕጋዊ መንጃ ፈቃድ ለሌለው ሰው ወይም ደረጃው በማይፈቅድለት መንጃ ፈቃድ እንዲያሽከረክር ተሽከርካሪን መስጠት ወይም መፍቀድ፣

4. ከሚመለከተው ህጋዊ አካል (ሠራተኛ) ፈቃድ ውጭ በማናቸውም ተሽከርካሪ ላይ በፋብሪካው ከተገጠመለት ውጭ ማናቸውም አካል በተሽከርካሪ ላይ መጨመር፣

5. በንግድ ያልተመዘገበና ያልተፈቀደለትን ተሽከርካሪ ወደ ንግድ ሥራ ወይም ወደ ኪራይ ማሠማራት፣

## ደረጃ 3 የቅጣት ዓይነት (ብር 800 እና 2 መደበኛ መስመር መታገድ)

1. የመመሪያውን አፈፃፀም ሥርዓት በማዛባት በአገልግሎት ተጠቃሚው የመገልገል መብት ላይ ተፅና ማድረግ ወይም መገደብ፤

2. አሳስፈሳጊ እጥረት እንዲኖርና እንዲባባስ ለማድረግ ተሽከርካሪውን በመርሐ ግብር መሠረት አለማቅረብና አገልግሎት አለመስጠት፤

3. በመመሪያው መሠረት ለሕዝብ ከምችት የትራንስፖርት እጥረት የወጣውን መርሐ ግብር ለማስፈፀም ከተመደበበት መስመር ወደ ሌሳ መስመር (ከምችት ወደበዛበት) አገልግሎት እንዲሰጥ ሲደረግ ፈቃደኛ ባለመሆን ወይም ችግር በመፍጠር በተገልጋዩ ላይ መጉሳሳት ካደረሰ፤

## ደረጃ 3 የጥፋት ዓይነት /5000 ብር/ እና ከዘርፉ ሥራ ስለመታገድ)

1. ተሽከርካሪው ከጉዞ ርቀት ወሰኑ ውጭ በተጭበረበረና በመርሐ-ግብር ባልተደገፈ የሥምሪት ሰነድ እንዲሰራ ካስደረገ፣

2. የተሽከርካውን የፊትና የኃላ ሰሌዳ በመፍታት ወይም በተሳሰፈው ደንብ ሠሌዳው ተፈቶ ቅጣት ሳይፈጸም በያዘው የቅጣት ሰነድ (የቁጥጥር ክስ ወረቀት) እንዲሰራ ካደረገና ይህንንም በአሳማኝ ሁኔታ ከተረጋገጠ፣

3. የተሽከርካውን የፊትና የኃላ ሰሌዳ እንዲፈታ ወይም ዕይታ እንዳይኖር በጭቃና ሌሎች መከለያዎች በመጠቀም እንዲንቀሳቀስ ካደረገ ወይም ከተባበረ፣

## ደረጃ 4 የጥፋት ዓይነት /6000 ብር/ እና ከዘርፉ አገልግሎት ማገድና የምዝገባ ሠሌዳው እንዲሰረዝ ስለማድረግ፣)

1. ከመደበኛ አገልግሎት ውጭ በሕገወጥነት ያለሥምሪት መረጃና ፈቃድ እንዲንቀሳቀስ ካደረገ፣

2. የተሽከርካሪውን የሬትና የጋላ ሰሌዳ በመፍታት የቁጥጥር ሥርዓት እንዳይኖር ለመከላከል ሲል በኬላ ላይ ፍጥነትን ጨምሮ ሕገወጥ ጥሰት እንዲፈጸም ለድርጊቱ ተባባሪ ሆኖ ከተገኘ፣

3. ከመደበኛ የአገልግሎት አሰጣጥ ሰነድ ውጭ የሐሰተኛ ሰነድ አሽከርካሪው እንዲጠቀምና እንዲሰራ ካደረገ ወይም ካልተቀጣጠረ፣ ወይም በዚህ ድርጊት ራሱ ፈጻሚ ሆኖ ከተገኘ፣

4. በመደበኛ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሥምሪት አፈጻጸም መመሪያ መሰረት መርሐ ግብርን ያልጠበቀና ባልተመደበበት ቦታ አገልግሎት እንዲሰጥ ካደረገ፣

## 9.3.3 የአሽከርካሪ ረዳትን የሚያስጠይቁ:-

## የጥፋት ደረጃና ዓይነት ( ከብር 50-100)

## ደረጃ 1 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት (ብር 50)

1. ለተሣፋሪዎች በጉዞ ላይ ከተስማሙበት የገንዘብ መጠን ውጪ እንዲጨምሩ ማድረግ፣
2. ተሣፋሪ ቀደም ሲል የተጠቀመበትን የጉዞ ትኬት ተቀብሎ ለሌላ ተሣፋሪ መልሶ መስጠት፣
3. ተሽከርካሪ በጉዞ ላይ እያለ በተለያዩ ምክንያቶች ሲቆም ለምልክት ብለው ድንጋይ መንገድ ላይ ማስቀመጥና የተቀመጠውንም ከመንገዱ ላይ አለማስወገድ፣
4. ተሽከርካሪ ሳይቆም በር መክፈት፣
5. ተሽከርካሪ ሳይቆም ሰው ማውረድ ወይም ማሳፈር፣
6. የደንብ ልብሱን በአግባቡ አለመልበስ፣
7. ሕጋዊ መታወቂያና ባጅ ይዞ አለመገኘት፣
8. ለተሣፋሪው ተገቢ እንክብካቤ አለማድረግ፣
9. የተሽከርካሪውን ንጽሕና ያለመጠበቅ /የውጭና የውስጥ/፣
10. ሰዎችና እንስሳት ለመጠጥና ለአትክልት የሚጠቀሙበት ኩሬ፣ ወንዝ፣ ጉድጓዶች ላይ ተሽከርካሪን ማጠብ፣
11. በተሽከርካሪ ውስጥ የቀየውን ቆሻሻ በመናኸሪያ ውስጥ መጣል፣

## ደረጃ 2 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት (ብር 100)

1. የተሣፋሪዎች ንብረት በአያያዝ ጉድለት እንዲሰበር ወይም እንዲበላሽ ማድረግ፣
2. በጉዞ ላይ ተሣፋሪዎችን ማንቋሸሽ፣ መሳደብ፣ መማታትና ስመማታት መሞከር፣
3. በማናቸውም ቦታ ወደእኔ በማለት ሰውን መጐተት ወይም ከፍላጐት ውጭ ወደ መኪና ማውጣት፣
4. የጉዞ ቲኬት ሽያጭ ላይ በወንበር ቀጥር በቅድም ተከተል አስመሸጥና በወንበር ልክና ቀጥር ተሣፋሪዎች አስማስቀመጥ፣
5. የጫነው ሰቃ በዝናብ በፀሐይ በአቧራ ምክንያት ለብልሽት የዳረገ ወይም በቸልተኝነት ምክንያት ሰቃ ያጠፋ /የጣለ/፣
6. በማናቸውም ቦታ ከተሣፋሪዎች የሰቃ መጫኛ ወይም ማውረጃ በማለት ገንዘብ መቀበል፣ ወይም ክፍያ መጠየቅ፣
7. መረጃ ሲጠየቅ ለመስጠት ፈቃደኛ አስመሆን፣
8. ተሣፋሪውን ማንገላታት፣ መዝለፍ፣ ማንጓጠጥ፣
9. የተሽከርካሪውን የቴክኒክ ብቃትና የጉዞ ዝግጁነት እየተከታተለ ለሚመለከተው አስማሳወቅ፣
10. ከተጓዥ ተመላሽ የሆነ የመንገደኞች ትኬት መልሶ ለሌላ መስጠት፣
11. ተጓዥ ለከፈለው ገንዘብ ማስረጃ (ፋክቱር) በሚጠየቅበት ሰዓት በወቅቱ አስመስጠት፣
12. ተጓዥ ከከፈለው የገንዘብ መጠን በላይ ቀሪ ተመላሽ ሲኖረው በቀጥታ መልሶ አስመስጠት ወይም አስመመለስ፣

## 9.3.4 የገንዘብ ተቀባዮችን የሚያስጠይቁ:-

## የጥፋት ደረጃና ዓይነት (ከብር150 እና ከሥራ ስስመታገድ)

## ደረጃ 1 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት (ብር 150)

1. ስጉዞ አስፈላጊ የሆኑ ደረሰኞችን፣ የሰቃ ታግና ሴሎች ሠነዶችን በበቂ አስመያዝ አስመጠቀም፣
2. መረጃ አስማሳየት፣ ሲጠየቅም አስመስጠት፣

3. ተሣፋሪውን በወንበር ቁጥር አለማስቀመጥ፣

4. ለተሣፋሪው ተገቢውን እንክብካቤ አለማድረግ፣

5. ተሣፋሪውን ማንገላታት፣ መጉተትና መዝለፍ፣

6. ተሽከርካሪ ሳይቆም ተሣፋሪ ማውረድ፣

7. ለተከፈለ ገንዘብ ደረሰኝ አለመስጠት፣

8. የደንብ ልብሱን አለመልበስና የተዘጋጀለትን ባጅ አለመስጠፍ፤

9. ለሰውም ሆነ ለዕቃ ከተፈቀደው የትራንስፖርት ታሪፍ ዋጋ በላይ ማስከፈል።

## ደረጃ 2 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት (ብር 200)

1. በተጭበረበረ ሠነድ ሲሠራ መገኘት፣

2. ለተሣፋሪ ምቾት የማይሰጡ ነገሮችን ጭኖ መገኘት፣

3. በሚመለከተው አካል ከፀደቀው ታሪፍ በላይ ማስከፈል፣

## ደረኛ 3 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት (ብር 250)

1. በህገ አግባብ ታግዶ እያለ ለሥራ ተሠማርቶ መገኘት፣

2. ሌሎች በሥምሪት አፈፃፀም መመሪያናና በመናኸሪያ መመሪያ የተጠቀሱትን አክብሮ አለመሥራት፣

3. መንገደኛው ያልተጓዘበትን ክፍያ ለተሣፋሪው አለቦ ወዲያውኑ አለመመለስ፤

4. ከ25 ኪሎ ግራም በታች ለሆነ የተሳፋሪ ዕቃ አስከፍሎ ያጓጓዘና ከታሪፍ በላይ አስከፍሎ የጫነ፣

5. ከ7 ዓመት በታች ላሉ ህፃናት ክፍያ የጠየቀና ያስከፈለ፣ ከ8-12 ዓመት ዕድሜ ላላቸው ሕፃናት በግማሽ ክፍያ ያልጫነ፣

6. ሌሎች በሥምሪት አፈፃፀምና በመናኸሪያ መመሪያዎች የተዘረዘሩትን አክብሮ ያልሠራ፤

## 9.3.5 ተቀጣሪ የማሕበር /ድርጅት/ ሠራተኞችን የሚያስጠይቁ የዲስፕሊን ጥፋቶች፣

### ደረጃ 1 የጥፋት አይነትና ቅጣት (ብር 500 እና የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ)

1. በመደበኛ አገልግሎትም ሆነ በልዩ ጉዞ የወጡ መርሐ ግብርችን አፈፃፀም በአግባቡ አለመከታተልና ንዝላልነትን ማሳየት፤
2. በሕዝብ ክምችት የትራንስፖርት እጥረትን ለመቅረፍ የወጣን መደበኛና የልዩ መርሐ ግብርን የሥምሪት አፈፃፀም ተከታትሎ በትክክል መፈፀሙን አለማረጋገጥ፤
3. በመደበኛና በሕዘብ ክምችት ወቅት በመርሐ ግብር የተሰጠን የሥምሪት አገልግሎት ያልፈፀሙ ተሽከርካሪዎችን ተቀጣጥር በጥፋተኝነት እንዲጠየቁ አለማድረግ፤

### ደረጃ 2 የጥፋት አይነትና ቅጣት (ብር 600 እና ከመናኻሪያ ሥራ እገዳ)

1. በሕዝብ ክምችትና በትራንስፖርት እጥረት ጊዜያቶች መፈፀም ያለባቸውን መደበኛ አገልግሎቶችና የልዩ ጉዞ መርሐ ግብርች ከማስፈፀም ውጪ ለሕገወጥ ድርጊት ተባባሪ ሆኖ መገኘትና በተገልጋይ ሕዝብ ላይ አሳስፈላጊ ጫና እንዲፈጠር ማድረግ፤
2. ሕጋዊ የአገልግሎት መስጫ ቦታዎች ላይ ሲሰጥ የሚገባውን መደበኛም ሆነ የልዩ ጉዞ መርሐ ግብር ወደ ጉን በማድረግ ለሕገጥ ሥምሪት የመውጫ ፈቃድ መስጠት፣ ፈቃዱን ሕጋዊ አድርጉ በማረጋገጥ ማስረጃ መስጠት፤
3. በመደበኛ እና በልዩ ጉዞ መርሐ ግብር መፈፀም የሚገባቸውን የጉዞ ሥምሪት ለማድረግ መናኸሪያ ገብተው በተገልጋዩ ላይ ከመመሪያ ውጪ የሆኑ የአገልግሎት ጫናዎች የሚፈጥሩ አገልግሎት ሰጪዎችን በዝምታ ማለፍ ወይም ለጥቅም ሲሉ የሕዝብን መብት አለማስከበር፤
4. መደበኛ የስምሪት ሂደትን ማዛባት፣ ሁከት መፍጠር፣ አሳስፈላጊ ጸብና ብጥብጥ ለማድረግ መሞከር፣አድማ በማነሳሳት የሥምሪት አገልግሎቱን ማወክ፣ የሥምሪት መርሃ-ግብርን ማዛባት፣

### ደረጃ 3 ጥፋትና ቅጣት (ከሥራ ስስመታገድ)

1. ለሕገወጥ ሥምሪት የሥራ ድጋፍ ማድረግ፣
2. የቅድሚያ ትኬት ደብቀ ለመሸጥና የተለየ ጥቅም ለማግኘት መሞከር፣
3. የቅድሚያ ትኬትን ለማይመለከተው አሳልፎ በመስጠት የግል ጥቅም ለማግኘት መሞከር፣

## 9.3.6 የሥነ-ሥርዓት ወይም የሥነ ምግባር ጉድለቶች በግል፣ በድርጅት፣ በአክሲዮን ወይም ማኅበር የሚጠየቅበት ጥፋት (ከብር 500 እስከ 5000)፣

### ደረጃ 1 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት (ብር 500)

1. የምዝገባ ፈቃዱን በየዓመቱ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት አስፈላጊውን አሟልቶ በወቅቱ ያላሣደሰ፣
2. ይህንኑ የምዝገባ ፈቃዱን ለዕይታ በማያመች መልኩ አስማስቀመጥ፣ ወይም ሲጠየቅ ለማሣየት ፈቃደኛ ያልሆነ፣
3. በሕግ ውሳኔ በትራንስፖርት አገልግሎት እንዳይሰማሩ የታገዱ ሠራተኞችን ሲያሰራ ከተገኘ፣ ህጋዊ የስብሰባ ጥሪ ተደርጉለት ያለ በቂ ምክንያት ከቀረ፣
4. ለሚሰጠው የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በሥምሪት አፈጻጸም መመሪያ መሰረት የሠራተኞችን የሥራ ዩኒፎርምና ባጅ፣ የአባል ተሽከርካሪውን የሥራ ደረጃው የጠበቀ የቀለም ቅብ አሟልቶ ሥራ ላይ ያላዋለ።
5. ከመደበኛ አገልግሎት ውጭ ሕገወጥ ለሆነ ሕገወጥ ሥምሪት የሚውል የሥራ ፈቃድ (መውጫ) ከሰጠና ይህው ፈቃድ በሥራ ማሕተም ተረጋግጦ ከተገኘ፣
6. በመደበኛ መርሐ ግብር የሚሸፈኑ ጉዞ መስመሮችን ተሽከለርካሪ ባለመመደብ አገልግሎት እንስተጓጎልና ተገልጋዩ እንዲጉላላ ያደረገ፣
7. ሥራ ላይ የሌሉ ተሽከርካሪዎችን በመርሐ ግብር እንዲካተቱ ያደረገ፣
8. ለሚሰጠው አገልግሎት የመደበውን ሠራተኛ የሥራ ድርሻ ኃላፊነት ለይቶ በመስጠት የማያሰራና ከተመደቡበት ሥራ ውጭ በመንቀሳቀስ የአሰራር ሥርዓት ሲያዛቡ አይቶ የእርምት እርምጃ የማይወስድ ከሆነ፣

## ደረጃ 1 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት (ብር 700 )

1. በመርሐ ግብር የወጣውን መደበኛ የሥምሪት አገልግሎት ፕሮግራም አስተባብር ማሸፈን ካልቻለ፣
2. በልዩ ጉዞ መርሐ ግብር መሠረት ፕሮግራም አለማዘጋጀት፣
3. የሕዝብ ክምችት በመኖሩ ምክንያት መደበኛ ሥምሪት ሳይሸፈን ለልዩ መርሐ ግብር ብቻ ተሽከርካሪ በመመደብ አገልግሎቱን ማዛባትና ዕጥረት መፍጠር፤
4. በሕዝብ ክምችት ወቅት የአባል ተሽከርካሪዎችን ከሥምሪት ላይ ሳይገኙ ሲቀሩ አለመቆጣጠር ወይም በሌላ የሥምሪት ሥራ እንዲሠማሩ ማድረግና መተባበር፤

## ደረጃ1 የጥፋት ዓይነት /3500 ብር/

1. አባል ተሽከርካሪዎችን በተሟላ መረጃ መዝግቦ ካልያዘ፣
2. አባል ተሽከርካሪዎቹ በሕጋዊ የአሰራር ሥርዓት በመርሐ ግብር እንዲካተቱና የሥራ መብትና ጥቅማቸው ተጠብቆ እንዲሰሩ ካላደረገ፣ ወይም በመርሐ ግብራቸው መሰረት አገልግሎት ስለመስጠታቸው ካልተቆጣጠረ፣
3. የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎትን ባልተፈቀደ መልኩ ከመናኻሪ ውጭ እንዲሰሩ ለአባል ተሽከርካሪዎቹ ሕገወጥ የሆነ የጉዞ መውጫ ፈቃድ ሰጥቶ ከተገኘ፣ ወይም ካልተቆጣጠረ፣
4. አባል ተሽከርካሪዎቹ የተደራጀበትን ማሕበር (ድርጅት) የሚገልጽ የተሟላ መረጃ እንዲኖራቸው ካላደረገና ተቆጣጥር ካላስፈጸመ፣
5. ከመናኸሪያ ውጭ ለሚደረግ ሕገወጥ ጉዞና በተገልጋዩ ላይ በአባል ተሽከርካሪዎቹ አማካይነት በወያላና ደላሎች በተገልጋይ ላይ ለሚሰደርስ ወከባ ከተባበረ ወይም ካልተቆጣጠረ፣

## ደረጃ 2 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት (ብር 1000 እስከ 6000)

## ደረጃ 2 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት (ብር 1000 )

1. የሥራ ደረጃ ብቃት ማረጋገጫ የሌለውን ተሽከርካሪ እንዲሰራ ያደረገ ወይም ያሠራ፣
2. በቁጥጥር ወቅት የሥራ ደረጃ መሥፈርት ያሳሟላ አባል ተሽከርካሪ አገልግሎት እንዲሰጥ ያደረገና ሕዝብ አሣፍሮ ከተገኘ ፣

3. ማንኛውም ገለሰብ ድርጅት፣ ባለአክሲዮን ወይም ማኅበር ፈቃድ በተሰጠበት ወቅት ተሟልተዋል በሚል ያሳያቸውን መመዘኛዎች በቁጥጥር ወቅት ተሟልተው ካልተገኙ፣

4. ከመናኸሪያ አጠቃቀምና የሥምሪት አፈጻጸም አንጻር የአሠራር መመሪያዎችን ባልጠበቀ ሁኔታ ሲሰራ የተገኘ፣

5. የተሟሳ የሥራ መረጃ ያሳደራጀና ሲጠየቅም በተሟሳ መልኩ የተጣራ መረጃ ለመስጠት ያልቻለ ወይም ፈቃደኛ ያልሆነ፣

6. በቁጥጥር ወቅት በሥራ አደረጃጀት መስፈርቱ መሰረት የተሟሳ የሠራተኛ ኃይል ይዞ ለመስራት አስመቻሉ ከተረጋገጠ፣

7. ለዘርፉ የሚወጡ ሕግ፣ደንብና መመሪያዎችን ተቀብሎ ያስመተግበር፣

8. ከተገልጋዮች ለሚቀርቡ ቅሬታና አቤቱታዎች ተገቢ ምሳሽ አስመስጠትና ለዚሁ የአሰራር ሥርዓት እንዲኖር አለማድረግ፣

9. በሚሰጡ አገልግሎቶች ለተጋዥ የግል መጠቀሚያና ሴሎች ዕቃዎች የሚያገለግሉ:-

   9.1 የዕቃ ሚዛን ካሳቀረበ፣

   9.2 የሚጫን ዕቃ ሳይ የሚታሰር ታግ እንዲታሰር ካሳደረገ፣

   9.3 ለተጓጓዘው ዕቃ የተጠየቀ ክፍያን የሚገልጽ ሕጋዊ ደረሰኝ ካልሰጠ፣

   9.4 ኪሎ ግራም ለማይሞሳ የተጓዥ መንገደኛ የግል መጠቀሚያ ዕቃ ክፍያ ያስከፈለ፣

10. በሥምሪት አገልግሎት አሰጣጥ በጉዞ ሳይ ብልሽት ገጥሞ ተገልጋዩ እንዳይጉሳሳ ችግሩን ሳያሳውቅ ከቀረ ወይም ምትክ እንዲሳክ ፈጣን ምሳሽ ካልሰጠ፣

11. በአገልግሎት አሰጣጥ በሥምሪት አፈጻጸም መመሪያው ስለ መናኸሪያ አጠቃቀም የወጡ መመሪያዎችን አክብሮ አለመሥራት፤

12. በአባል ተሽከርካሪዎች ከመርሐ ግብር ውጭ ባልተመደቡበት ጉዞ መስመር አጭበርብረው ለመጫኝ የሚደረግ ሙከራን ተከታትሎ ካልገታና ይህን በሚፈጽም ሳይ የእርምት እርምጃ ካልወሰደ፣

13. ማሕበሩን ከተቋቋመበት ሕግ፣ ደንብና መመሪያ አኳያ በመተዳደሪያ ደንቡ( መቋቋሚያ ሕጉ) መሰረት የሚጠበቅበትን ሁሉ በአግባቡ ካልፈጸመ፣ ወይም ለመፈጸም ፈቃደኛ ካልሆነ፣

14. መደበኛ መርሐ ግብር ያልሸፈኑና የልዩ ጉዞ ፕሮግራም ሥምሪት ያልፈፀሙ ተሽከርካሪዎችን መረጃ አለማቅረብ፣ ወይም በጥፋታቸው የዲስፕሊን ቅጣት እንዲቀጡ አለማድረግ ወይም ቅጣት እንዳይፈፀም የመከሳከል ሙከራ ማድረግ፣

15. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 9.2. የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት መወጣት ካልቻሉ፤

16. በሕገወጥ መንገድ ተሽከርካሪን ለማሠማራት መሞከር ወይም የሕዝብን የመገልገል ፍላጐት ለመገደብ ዕጥረት መፍጠር፣

17. በመመሪያው ከተሰየት ጊዜያቶች ውጪ አሳፊ ተጠቃሚ ለመሆን የልዩ ጉዞ ታሪፍ መጠየቅ ወይም በዚህ መልክ አገልግሎት ለመስጠት መሞከር።

## ደረጃ 2 የጥፋት አይነትና ቅጣት (ብር 4000)

1. መደበኛ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሥርዓትን ባልጠበቀ ሁኔታ በሕገወጥነት ለሚደረግ አገልግሎት ተባባሪ ሆኖ ከተገኘ፣
2. ከተሰጠው የድርጊት መርሐ- ግብርና መስጠት ከሚገባው የአገልግሎት ርቀት ወሰን ለአባል ተሽከርካሪው የሥራ መንቀሳቀሻ ፈቃድ ከሰጠ ወይም በማቀራረፕ የጉዞ ፈቃድ በመስጠት (ከሁለት በላይ መውጫ ፈቃድ አዘጋጅቶ መስጠት)፣
3. የማሕበሩ አባላት ከመደበኛ አገልግሎት ውጭ በሕገወጥ ሥምሪት ላይ ከፍተኛ ተሳትፎ እንዳደናራቸው ያደረገና የተባበረ፣
4. በመደበኛ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሥምሪት አፈጻጸም መመሪያ መሰረት ለአባላቱ የወጣውን የሥምሪት መርሐ ግብ በአግባቡ እንዲፈጸም ካላደረገ ወይም ለዚህ ተባባሪ ሆኖ አለመገኘት፣

## ደረጃ 3 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት (ብር 1500 እስከ 2000)

## ደረጃ 3 የጥፋት አይነትና ቅጣት (ብር 1500)

1. የዚህን መመሪያ አፈፃፀም ሥርዓት በማዛባት ያሉትን አባል ተሽከርካሪዎች በሙሉ ለአገልግሎት ባለማቅረብ የተጠቃሚው የመገልገል መብት የሚገድብ ከሆነ፤
2. አላስፈላጊ እጥረት እንዲኖርና እንዲባባስ መሥራት የሚችሉ ተሽከርካሪዎችን በመርሐ ግብር መሠረት አለማሰማራት፤

3. በመመሪያው መሠረት ለሕዝብ ክምችት የትራንስፖርት እጥረት እንዲደናር ያሉትን አባል ተሽከርካሪዎች በሙሉ በሁሉም አቅጣጫ አገልግሎት እንዲሰጡ አለማድረግ ወይም ለማሰማራት ፈቃደኛ አለመሆን፤

4. የሕዝብ ክምችትና የትራንስፖርት እጥረት መኖሩን እያወቀ በተገልጋዩ ላይ አላስፈላጊ ጫና ለመፍጠር መሞከርና ሕገወጥ ሥምሪትን ለማስፈፀም መሞከር ወይም የሥምሪት ፈቃድ አላግባብ መስጠት፤

5. የሕዝብ ክምችት ወቅቶችን የአገልግሎት አሰጣጥ ዝርዝር የሥራ መረጃ አገልግሎቱ በተሰጠ 15 ቀናት ውስጥ በሪፖርት አለማቅረብ ወይም ለማቅረብ ፈቃደኛ ሳይሆን ከቀረ፤

## ደረጃ 3 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት (ብር 2000)

1. የተጭበረበረ መረጃ ይዞ መገኘት ወይም የድርጅቱን /የማህበሩን ሕትመቶች በህገ ወጥ ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣

1. ትራንስፖርተሩ ቀጥር ለሚያሠራቸው ሠራተኞች፣ ሾፌሮች፣ የገንዘብ ተቀባዮችና ረዳቶችን የደንብ ልብስ ዓርማና ባጅ አሟልቶ እንዲሰሩ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ካላስፈጠመ፣

2. በተሳፋሪ መንገደኞች በተሽከርካሪ ላይ የሚረሱ ዕቃዎችን ተቆጣጥሮ በማስቀመጥ ለባለንብረቱ እንዲመለስ ያላደረገ ወይም የጠፋውን ዕቃ ለሚመለከተው ክፍል ያልሰጠ ወይም እንዲመለስ ያላደረገ፣

3. ቅድሚያ ትኬት ገዝተው በተለያዩ ምክንያቶች ከጉዞ የሚቀሩ ተሳፋሪ መንገደኞችን ክፍያ ከከትኬቱ የአገልግሎት ታሳቢ (10% ከማይበልጥ ) ተቀናሽ ውጭ በወቅቱ ለተገልጋዩ ተመላሽ አለማድረግ፣

4. በጉዞ ወቅት ስተጋዥ መንገደኛ የተሰጠን የጉዞ ትኬት የያዘ መንገደኛ ከተሰጠው ትኬት ምዝገባ ውጭ የሆነ ተሽከርካሪ በማቅረብ ወይም ምትክ እንዲሄድበት በመደረጉ የቀረን መንገደኛ ሙሉ ክፍያ በወቅቱ ተመላሽ አለማድረግ፣ ወይም ለመመለስ መጉላላት እንዲገጥመው ካደረገ፣

## ደረጃ 4 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት (ብር 2000 እና የምዝገባ ፈቃድ መሰረዝ)፣

## ደረጃ 4 የጥፋት ዓይነትና ቅጣት (ብር 2000 እና የምዝገባ ፈቃድ መሰረዝ፣)

1. መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በመተዳደሪያ ደንብ ወይም መመስረቻ ጽሁፍ መሰረት ያለማድረግ፣
2. የማሕበሩን የንብረትና ገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም በውጭ ኦዲተር ያለማስመርመርና ለጠቅላላ ጉባኤው በመተዳደሪያ ደንቡ ወይም መመስረቻ ጽሁፍ መሰረት ለአባላት ሪፖርት ያለማቅረብ ፣
3. የሥራ ቢሮና የሙያተኞች ቅጥር ፈጽሞ የተሟላ ሥራ ያለማከናወን፣
4. ከተሰጠው የምዝገባ ፈቃድ ውጭ ከሌላ ጋር ተጣምሮ ሲሰራ ከተገኘ፣
5. የማሕበር ገንዘብን ከደንብና መመሪያ ውጭ አከፋፍሎ ለመስጠት የሞከረ ወይም ይህንኑ የፈጸመ፣
6. ከተሰጠው የሥራ ውክልናና ከተፈቀደለት የሥራ በጀት ውጭ የማሕበርን ገንዘብ ከአባላት ዕውቅና ውጭ እንዲባክን ካደረገ ወይም ከባከነ፣
7. ለዘርፉ የሚወጡና ሥራ ላይ ያሉ ሕግ፣ ደንብና መመሪያዎችን ተቀብሎ ያለመተግበር፣
8. ከማሕበር ወደ ማሕበር በሚደረግ የአባላት ዝውውር አዲስ ለሚገባ አባል መደለያ (ስጦታ) በሚል ተገቢ ያልሆነ ክፍያ ፈጽሞ ከተገኘ፣

## 9.3.8 የትራንስፖርት ማሕበራትና ድርጅቶችን በተመለከተ:-

### ደረጃ 1 የጥፋት ዓይነት /3500 ብር/

6. አባል ተሽከርካሪዎችን በተሟላ መረጃ መዝገቦ ካልያዘ፣
7. አባል ተሽከርካሪዎቹ በሕጋዊ የአሰራር ሥርዓት በመርሐ ግብር እንዲካተቱና የሥራ መብትና ጥቅማቸው ተጠብቀ እንዲሰሩ ካላደረገ፣ ወይም በመርሐ ግብራቸው መሰረት አገልግሎት ስለመስጠታቸው ካልተቆጣጠረ፣

8. የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎትን ባልተፈቀደ መልኩ ከመናኻሪ ውጭ እንዲሰሩ ለአባል ተሽከርካሪዎች ሕገወጥ የሆነ የጉዞ መውጫ ፈቃድ ሰጥቶ ከተገኘ፣ ወይም ካልተቀጣጠረ፣

9. አባል ተሽከርካሪዎች የተደራጀበትን ማሕበር (ድርጅት) የሚገልጽ የተሟላ መረጃ እንዲኖራቸው ካላደረገና ተቆጣጥሮ ካላስፈጸመ፣

10. ከመናኸሪያ ውጭ ለሚደረግ ሕገወጥ ጉዞና በተገልጋዩ ላይ በአባል ተሽከርካሪዎቹ አማካይነት በወያላና ደላሎች በተገልጋይ ላይ ለሚሰደርስ ወከባ ከተባበረ ወይም ካልተቆጣጠረ፣

## <u>ደረጃ 2 የጥፋት ዓይነት /4000 ብር/</u>

5. መደበኛ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሥርዓትን ባልጠበቀ ሁኔታ በሕገወጥነት ለሚደረግ አገልግሎት ተባባሪ ሆኖ ከተገኘ፣

6. ከተሰጠው የድርጊት መርሐ- ግብርና መስጠት ከሚገባው የአገልግሎት ርቀት ወሰን ለአባል ተሽከርካሪው የሥራ መንቀሳቀሻ ፈቃድ ከሰጠ ወይም በማቀራረጥ የጉዞ ፈቃድ በመስጠት (ከሁለት በላይ መውጫ ፈቃድ አዘጋጅቶ መስጠት)፣

7. የማሕበሩ አባላት ከመደበኛ አገልግሎት ውጭ በሕገወጥ ሥምሪት ላይ ከፍተኛ ተሳትፎ እንዳደናራቸው ያደረገና የተባበረ፣

8. በመደበኛ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሥምሪት አፈጻጸም መመሪያ መሰረት ለአባላቱ የወጣውን የሥምሪት መርሐ ግብ በአግባቡ እንዲፈጸም ካላደረገ ወይም ለዚህ ተባባሪ ሆኖ አለመገኘት፣



# ክፍል አሥራ አንድ

## 11.1. ስለቁጥጥር

የሕዝብ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት መቆጣጠሪያ ደንብ (መመሪያ) ሲጣስ የሚቆጣጠሩ አካላት የመንገድ ላይ ትራፊክ ፖሊሶች እና የመናኸሪያና ሥምሪት አፈፃፀም ክትትልና ቁጥጥር ሠራተኞች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ኅብረተሰቡ የቁጥጥሩ አጋዥ ኃይል እንደመሆኑ አስተያየቶችና ጥቆማዎችን በመስጠት መሳተፍ ይችላል፡፡

## 11.2. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ የዲሲኘሊን ቅጣት መመሪያ በፌዴራል ደረጃና በክልሎች ተመዝግበው አገልግሎት በሚሰጡ የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመሳለሻ አሽከርካሪዎችና ተሽከርካሪዎች፣ ገንዘብ ተቀባዮች የግል ባለንብረቶች፣ ረዳቶች፣ ማኅበራትና ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 11.3. የመተባበር ግዴታ

ይህንን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ መንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የትራንስፖርት ድርጅቶች፣ ማኅበራትና ግለሰቦች የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## 11.4. የቁጥጥር አፈፃፀም ሂደት

- ለቁጥጥር የተሠማራው ሠራተኛ ራሱን የሚገልጽ መታወቂያ ይዞ በመናኸሪያ ውስጥና በሥምሪት መሥመሮች ላይ ለቁጥጥር አመቺ የሆነ ቦታ በመምረጥ ተሽከርካሪውን በታፔላ ማስቆምና ወደተሽከርካሪው ውስጥ ገብቶ ተገቢ መረጃ መጠየቅና መያዝ አለበት፣
- በቁጥጥር ሂደት ጥፋት ተፈጽሞ ከተገኘ ተቆጣጣሪው ወዲያውኑ የክስ ቻርጅ ወረቀት በመሙላት ዋናውን ለተከሣሹ አስፈርሞ መስጠት ወይም እንደየክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ተቆጣጣሪው የቅጣት ገንዘብ የመሰብሰብ ስልጣን የተሰጠው ከሆነ የጥፋቱን ዓይነትና እርከን መሠረት ያደረገውን ቅጣት ወዲያኑ መቀበልና ደረሰኝ መስጠት ይጠበቅበታል፣ እንዲሁም የተሰበሰበውን ገንዘብ ለፋይናንስ ክፍል በማስረከብ የሥራ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

### 11.5. ክልከላ

11.5.1. የሚያስከስሱ ጥፋቶች ተፈጽመው እስካልተገኙ ድረስ ወዲያውኑ በክስ ቻርጅ ሞልቶ መያዝ እንጂ የትራንስፖርት ሕግና ደንብ ጥሰቶችን በነጭ ወረቀት በማስታወሻ ይዞ ማቆየት አይፈቅድም፡፡

11.5.2. በቁጥጥር ሠራተኞቻቸው የቅጣት ገንዘብ የሚቀበሉ ክልሎች በጀመሩት አሠራር መቀጠል የሚችሉ ሲሆን፣ በፌዴራል ደረጃ ግን የቅጣት ገንዘብ የሚሰበሰበው ለዚህ ሥራ በተመደቡ ገንዘብ ተቀባዮች ብቻ ነው፡፡

11.5.3. በዚህ መመሪያ የተካተቱ ነገር ግን በሌላ የትራንስፖርት አዋጅ ወይም ደንብ የተሸፈኑ የቅጣት ዓይነቶች ካሉ በወጡበት አዋጅ ወይም ደንብ መሠረት በዚያው በኩል ተግባራዊ መደረግ አለባቸው፡፡

## 12. የማሻሻል ወይም የመሻር ሥልጣን

ይህን መመሪያ ለማሻሻል ይሁን ለመሻር ሥልጣን ያለው የፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ሲሆን ተግባራዊ የሚደረገውም ከክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች ጋር በጉባዔ የጋራ መስማማት ላይ በመድረስ ነው፡፡

## 13. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

*ይህ የተሻሻለው አፈፃፀም መመሪያ ከጥር 2005 ዓ.ም. ጀምሮ ሥራ ላይ ውሏል፡፡*

*መጋቢት 2005 ዓ.ም.*

*ትራንስፖርት ባለሥልጣን*

*አዲስ አበባ፡፡*

